- ይህ የቅዳሴ “አቀራረብ” (presentation) ቀላል ነገር ሊመስል ይችላል። እንደ ቤተ ክርስቲያን ማዳመቂያ ተደርጎ ሲታይ ይስተዋላል።  ነገር ግን ሥርዓተ ቅዳሴውና ፍሬ ቅዳሴው በካህናትና በዲያቆናት ሲጸለይ ምእመናኑን በማንበብና ተሰጥኦን በመመለስ በጸሎት እንዲሳተፉ ያደርጋል። እንዲሁም ስለቅዳሴ ዕለት በዕለት ምእማናኑ ግንዛቤን እንዲጨምሩና የተሰጥኦ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚረዳ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ታላቅ አገልግሎትም ነው። አንዳንድ ጊዜ ኃላፊነቱን ወስደው ገጾችን የሚያንሸራሽሩት አገልጋዮች ኃሣባቸው ወይም ትኩረታቸው ወደ ሌላ ሲሄድባቸው ወይም በዚህ አገልሎት መሐከል ሌላ ተጨማሪ አገልግሎት ለመስጠት ሲንቀሳቀሱ የገጾቹ (ተንሸራታች ትዕይንት) slideshow መቆም ምእመኑ ቅዳሴውን በአንክሮ ከመከታተል ይልቅ ስለገጾቹ መቃወስ እንዲያሰላስልና ኃሣቡ ከቅዳሴው ውጭ  እንዲሆን ያደርገዋል። ታዲያ ሆን ብለን ባይሆንም ለቅዳሴው መካሄድ እንቅፋት ሆነናል ማለት ነው። ስለዚህ ኮምፒዩተሩ ከተከፈተበት ጀምሮ እስከቅዳሴ ፍጻሜ ድረስ ሙሉ ትኩረታችንን ቅዳሴው ላይ ብቻ በማዋል አገልግሎታችንን መስጠት ይኖርብናል ማለት ነው።

- ይህ የቅዳሴ “አቀራረብ” (presentation) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በተቻለ መጠን የተሟላ ለማድረግ ተሞካሯል። ስሕተቶች የሉበት ማለት ግን አይቻልም። በዚህ ዝግጅት ላይ የሠፈሩትን ሁሉ ካህናት በታላቅ ድምጽ ያሰሙታል ማለት አይደለም። በለሆሳስ የሚሏቸውም ይኖራሉ። ያለ ዜማም በንባብ የሚወጡበትም ጊዜ አለ። ይህ ደግሞ “በእይታ መስኮት” (screen) የሚያገለግለው ሰው ተጨማሪ ነገር የተጻፈ ወይም የጎደለ ሊመስለው ይችል ይሆናል። ይህንን ክፍል በማሳለፍ  ወደ  አሁናዊ የቅዳሴ ክፍል መሻገር ይችላል። ትልቁ ቁምነገር ግን አእምሮ ሰብሰብ አድርጎ ቅዳሴውን በሚገባ መከታተልና እራስን ከቅዳሴው ጋራ አዋህዶ መጓዝ ነው።

- አንዳንድ ጊዜ ቆራቢዎች በዛ ሲሉ ረዥም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያን የተገኘው ልምድ ፤ ጊዜውን ለመግዛት ሲባል ስለቅዱስ ቁርባን የተዘጋጁ መዝሙሮች ሲዘመሩ ይታያል። ትክክል መሆንና አለመሆኑን ለአባቶቻችን ካህናት ብንተው ይሻላል። ይሁን እንጅ በዚህ “የቅዳሴ አቀራረብ” (presentation) ፍጻሜ ቀጥሎ በመጨረሻዎቹ ገጾች ላይ “ኑ እንቅረብ መከራ ሳይመጣ” እና “ይህ ቁርባን ክቡር ነው” የተባሉት መዝሙሮች ተቀምጠዋል። እንደ አስፈላጊነቱ ገጾቹጋ በመሄድ ለእይታ አቅርቦ ማሳተፍ እንድገናም ወደ ቅዳሴው መመለስ ይቻላል። በመጨረሻም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ መገልገያ ሆነው ለእይታ ቢቀርቡ ምእመኑን ይረዱታል ብለን የምናስባቸውን ሁሉ በየጊዘው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ መሪና አጋዥነት ከዚህ በታችህ በተጠቀሰው ድረ ገጽ ላይ ስለምናስቀምጥ በመጎብኘት የሚፈልጉትን አውርዶ መጠቀም ይቻላል።

ምስጋና ዘወትር ለእግዚአብሔር ይሁን።

https://www.mytewahdo.org

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፋይሎች - Facebook Gro


አጋእዝተ፡ዓለም፡ሥለሴ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ። አሜን።

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም። አሜን።

In the Name of the Father, the Son, and the Holy Spirit One GOD. Amen.

ካህን (Priest)

ሚመጠን ግርምት ዛቲ ዕለት ወዕፅብት ዛቲ ሰዓት እንተ ባቲ ይወርድ መንፈስ ቅዱስ እመልዕልተ ሰማያት ወይጼልሎ ለዝንቱ መሥዋዕት ወይቄድሶ።

ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት? ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት? መንፈስ ቅዱስ ከሰማያተ ሰማያት የሚወርድባት ፤ ይህን መሥዋዕቱን የሚሠውርባትና የሚያከብርባት።

How awful is this day and how marvelous this hour wherein the Holy Spirit will descend from Heaven and over-shadow and hallow this sacrifice.

በጽሙና ወበፍርሀት ቁሙ ወጸልዩ ከመ ሰላሙ ለእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌየ ወምስለ ኵልክሙ።

በጽሞናና በመፍራት ቁሙ ፤ የእግዚአብሔር ሰላም ከእኔና ከእናንተ ጋራ ይሆን ዘንድ ጸልዩ።

In quietness and in fear, stand up and pray that the peace of God be with me and with all of you.

ሕዝብ (People)

አሜን።

Amen.

## ዘወትር ከሰኞ እስከ ዓርብ

## On the days from Monday to Friday

እምነ በሀ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርጉት ዓረፋቲሃ ወስእልት በዕንቍ ጳዝዮን። እምነ በሀ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን።

እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም እንልሻለን። ግድግዳዎችዋ የተሸለሙና በጳዝዮን ዕንቍ ያጌጠች ናት። እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም እንልሻለን።

Peace be unto you, our mother, O honorable church. your walls are embroidered with Topaz. Peace be unto you, our mother, O honorable church.

## በዕለተ ቀዳሚት ሰንበት - On Saturdays

መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ እምኵሉሰ ፀሐየ አርአየ። መስቀል አብርሃ! በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ።

መስቀል አበራ ሰማይን በኮከቦች ሸለመ(አስጌጠ)። ከሁሉም ይልቅ ፀሐይን አሳየ። መስቀል አበራ። በኮከቦች ሰማይን ሸለመ።

The cross shined and had the heavens embroidered with stars. Of all the sun is seen. The cross shined and had the heavens embroidered with stars.

## በዕለተ እሑድ - On Sundays

ኵሉ ዘገብሩ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ ፤ ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ይፈልጠኒኑ እምሕዝቡ

በጎን የሚያደርግ ፣ ሰንበትንም የሚያከብር ሁሉ ጻድቅ ነው። "ወደ እግዚአብሔር አምልኮ የገባ መጻተኛ ከሕዝቡ ሁሉ ይለየኝ ይሆንን?" አይበል ፤

Blessed is he who does blessed deeds and honors the Sabbath. Let him not question whether he will be outcast from the multitudes if he was to enter into the worship of God.

ኵሉ ዘገብራ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ።

በጎ ያደረገ ሰንበትንም የሚያከብር ጻድቅ ነው።

Blessed is he who does blessed deeds and honors the Sabbath.

ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምዐ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ወኢተዐገሠ እስከ ይፌጽሙ ጸሎተ ወቅዳሴ ወኢተመጠወ እምቍርባን ይሰደድ እምቤተ

ሃሌ ሉያ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ ከቍርባኑም ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን

Halleluia! If there be anyone of the faithful that has entered the church the time of mass not heard the Holy Scriptures, and has not waited until they finish the prayer of the Mass, and has not received the Holy communion, let him be driven out of the church:

ክርስቲያን ፤ እስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር ወአስተሐቀረ ቊመተ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ ከመዝ መሀሩነ ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ።

ይለይ ፤ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና ፤ የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምን አቃሏልና ፤ ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን።

for he has violated the law of God and disdained to stand before the heavenly King, the King of Body and Spirit. The Apostles have taught us in their canons.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን እግዚእነ ዘሖርከ ውስተ ከብካብ አመ ጸውዑከ በቃና ዘገሊላ ወባረክሎሙ ወረሰይኮ ለማይ ወይነ ከማሁ ረስዮ ለዝንቱ ወይን ዘክቡር በቅድሜከ።

እውነተኛ አምላካችን ጌታችን ክርስቶስ ሆይ የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና በጠሩህ ጊዜ ወደ ሠርግ የሄድህ ውኃውንም ባርከህ ጠጅ ያደረግህላቸው ፤ በፊትህ የተቀመጠ ይህንን ወይን እንደርሱ አድርገው።

Christ our God, truly our Lord, Who went to the wedding when they invited You in Cana of Galilee, and did bless for them the water and changed it into wine, You do in like manner unto this wine which is set before You.

ወይዜኒ ባርኮ ወቀድሶ ወአንጽሖ ይኩን ለሕይወተ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ በኵሉ ጊዜ። ሀሉ ምስሌነ አብ ወወልድ ወመንፈስ

አሁንም ባርከው አክብረውም ፤ አንጻውም ሁልጊዜ የሥጋችንና የነፍሳችን የልቡናችንም ሕይወት ይሆን ዘንድ። አብ ወልድ

Now also please bless it, hallow it and purify it, so that it may become the life of our soul, body, and spirit at all times. Father, Son and Holy Spirit,

ቅዱስ ወምላእ ወይነ ትፍሥሕት ወኀሤት ለሠናይ ወለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ፤ ለልቡና ወለፈውስ

መንፈስ ቅዱስ ከኛ ጋር ኑር። ለተድላና ለደስታ የሚሆን ወይኑንም ለበጎ ነገር ምላው። ለሕይወትና ለመድኃኒት ፤ ለኃጢአትም ማስተሠረያ ፤ ለማስተዋል ፤

be with us; and fill the wine with joy and happiness, for goodness, for life, for salvation and for the remission of sin, for understanding,

ወለምክረ መንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም። አሜን።

ለደኅንነት ለመንፈስ ቅዱስም ምክር ዛሬ ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

for healing, for the counsel of the Holy Spirit, both now and ever and world with out end. Amen.

**ካህን (Priest)**

ንጹሕ ወጣዕም ወበረከት ለእለ ይሰትዩ እምደምከ ክቡር አላትየን በአማን።

በእውነት ሰው የሆንህ አምላክ ሆይ፤ ከክቡር ደምህ ለሚጠጡ ንጹሕ ጣዕም በረከትም ይሁን፤

Purity, sweetness and blessing be to them who honestly drink of Your precious blood.

**ሕዝብ (*People*)**

አሜን።

Amen.

ካህን(Priest)

ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ።

ዓለሙን ሁሉ የያዘ እግዚአብሔር አብ አምላካችን ቡሩክ ነው።

Blessed be the Lord, Almighty Father, our God.

ሕዝብ (People)

አሜን።

Amen.

ካህን (Priest)

ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋሕድም ቡሩክ ነው።

And blessed be the only Son, our Lord and our Savior Jesus Christ.

ሕዝብ (People)

አሜን።

Amen.

**ካህን (Priest)**

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሔ ኵልነ።

ሁላችንን የሚያነጻና የሚያጸና መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው።

And blessed be the Holy Spirit, the Paraclete, the comforter and cleanser of us all.

**ሕዝብ (People)**

አሜን።

Amen.

**ካህን(Priest)**

ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ።

ዓለሙን ሁሉ የያዘ እግዚአብሔር አብ አምላካችን ቡሩክ ነው።

Blessed be the Lord, Almighty Father, our God.

**ሕዝብ (People)**

አሜን።

Amen.

ካህን (Priest)

ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋሕድም ቡሩክ ነው።

And blessed be the only Son, our Lord and our Savior Jesus Christ.

ሕዝብ (People)

አሜን።

Amen.

**ካህን (Priest)**

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሔ ኵልነ።

ሁላችንን የሚያነጻና የሚያጸና መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው።

And blessed be the Holy Spirit, the Paraclete, the comforter and cleanser of us all.

**ሕዝብ (*People*)**

አሜን።

Amen.

ካህን(Priest)

**ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ።**

**ዓለሙን ሁሉ የያዘ እግዚአብሔር አብ አምላካችን ቡሩክ ነው።**

Blessed be the Lord, Almighty Father, our God.

ሕዝብ (*People*)

**አሜን።**

Amen.

ካህን (Priest)

ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋሕድም ቡሩክ ነው።

And blessed be the only Son, our Lord and our Savior Jesus Christ.

ሕዝብ (People)

አሜን።

Amen.

**ካህን (Priest)**

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሔ ኵልነ።

ሁላችንን የሚያነጻና የሚያጸና መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው።

And blessed be the Holy Spirit, the Paraclete, the comforter and cleanser of us all.

**ሕዝብ (*People*)**

አሜን።

Amen.

ካህን (Priest)

ስብሐት ወክብር ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ ፤ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዕሩይ ኵሎ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም።

ልዩ ሦስት ለሚሆኑ ሁልጊዜም ለተካከሉ ለአብ ፣ ለወልድ ፣ ለመንፈስ ቅዱስም ክብር ምሥጋና ይገባል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ።

Glory and honour are due to the Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit always coequal, both now and ever and world with out end.

**ሕዝብ (*People*)**

ኣሜን።

Amen.

ካህን (Priest)

ጸልዩ አበውየ ወአኃውየ ላዕሌየ ወላዕለ ዝንቱ መሥዋዕት።

አባቶቼና ወንድሞቼ በእኔ ላይ በመሥዋዕቱም ላይ ጸልዩ።

My fathers and my brothers, pray for me and for this sacrifice.

## ንፍቅ ካህን (Ass't Priest)

እግዚአብሔር ይስማዕከ ኵሎ ዘሰአልከ ፤ ወይትወከፍ መሥዋዕተከ ወቍርባነከ ከመ መሥዋዕተ መልከ ጼዴቅ ፣ ወአሮን ወዘካርያስ ካህናተ ቤተ ክርስቲያኑ ለበኵር።

እግዚአብሔር የለመንከውን ሁሉ ይስማህ። የበኵር የቤተ ክርስቲያኑ ካህናቱ የሚሆኑ የመልከ ጼዴቅንና የአሮንን ፣ የዘካርያስንም መሥዋዕት እንደተቀበለ መሥዋዕትህን ቍርባንህንም ይቀበልልህ።

May God hear you in all that you have asked and accept your sacrifice and offering like the sacrifice of Melchisedec and Aaron and Zacharias, the priests of the church of the first-born.

ቡራኬ።

Benediction

## ካህን (Priest)

ተዘከረኒ ኦ አቡየ ቀሲስ በጸሎትከ ቅድስት።

ቄሱ አባቴ ሆይ ክብርት በምትሆን በጸሎትህ አስበኝ።

Remember me, my father priest, in your Holy prayers.

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ይዕቀባ ለክህነትከ ወይትወከፍ መሥዋዕተከ ወቍርባነከ በብሩህ ገጽ። ሥመር እግዚኦ ከመ ታድኅነኒ።

እግዚአብሔር ክህነትህን ይጠብቃት። መሥዋዕትህንና ቍርባንህንም በቡሩህ ገጽ ይቀበልልህ። አቤቱ እኔን ታድነኝ ዘንድ ማዳንን ውደድ።

The Lord keep your priesthood and accept your sacrifice and offering with a cheerful countenance. Be pleased, Lord, to save me.

**ካህን (Priest)**

፩ዱ አብ ቅዱስ።
፩ዱ ወልድ ቅዱስ።
፩ዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

አንዱ አብ ቅዱስ ነው።
አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው።
አንዱ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው።

One is the Holy Father,
One is the Holy Son,
One is the Holy Spirit.

ሕዝብ (People)

በአማን አብ ቅዱስ።
በአማን ወልድ ቅዱስ።
በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

አብ በእውነት ቅዱስ ነው።
ወልድም በእውነት ቅዱስ ነው።
መንፈስ ቅዱስም በእውነት ቅዱስ ነው።

Truly the Father is Holy,
Truly the Son is Holy,
Truly the Holy Spirit is Holy.

**ካህን (Priest)**

ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ አሕዛብ።

ሁላችሁም ምዕመናን እግዚአብሔርን አመስግኑት።

Praise The Lord, all you nations.

**ሕዝብ (*People*)**

ወሴብሕዎ ኵሎሙ ሕዝብ።

ሕዝብ ሁሉ ያመሰግኑታል።

And praise Him, all you people.

## ካህን (Priest)

እስመ ጸንዐት ምሕረቱ ላዕሌነ።

ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና።

For His merciful kindness is great toward us.

## ሕዝብ (People)

ጽድቁሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም።

የእግዚአብሔርስ ቸርነት ለዘለዓለም ይኖራል።

And the Truth of the Lord endures for ever.

*ካህኑን በመከተል እንበል - repeat after priest.*

ስብሐት ለአብ ፤ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ሃሌ ሉያ።

ለአብ ፤ ለወልድ ፤ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል። ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን ሃሌሉያ።

Glory be to the Father and to the Son and to the Holy Spirit. Both now and world without end. Amen.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

ዲይቆን (Deacon)

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

ሕዝብ (*People*)

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

## ካህን (Priest)

ሰላም ለኲልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

## ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with your spirit.

ጸሎተ አኰቴት ዘቅዱስ ባስልዮስ።

የቅዱስ ባስልዮስ የምስጋና ጸሎት።

The “Prayer of Thanksgiving” of St. Basil.

ካህን (Priest)

ነአኵቶ ለገባሬ ሠናያት ላዕሌነ እግዚአብሔር መሐሪ አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ ሠወረነ

ለእኛ በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ይቅር ባይ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሠውሮናልና ፤

We give thanks unto the doer of good things unto us, the merciful God, the Father of our Lord and our God and our Savior Jesus Christ: for He has covered us

ወረድአነ ዐቀበነ ወአቅረበነ ወተወክፈነ ኀቤሁ። ወተማኀፀነነ ፤ ወአጽንዐነ ፤ ወአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት።

ረድቶናልና ፤ ጠብቆ አቅርቦናልና ፤ ወደ እርሱም ተቀብሎናልና አጽንቶ ጠብቆናልና ፤ እስከዚህም ሰዓት አድርሶናልና።

and succored us, He has kept us and brought us nigh and received us unto Himself, and undertaken our defense, and strengthened us, and brought us unto this hour.

ንስአሎ እንከ ከመ ይዕቀበነ በዛቲ ዕለት ቅድስት ኵሎ መዋዕለ ሕይወትነ ወበኵሉ ሰላም አኃዜ ኵሉ እግዚአብሔር አምላክነ።

አሁንም ክብርት በምትሆን በዚህች ዕለት በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ይጠብቀን ዘንድ እንለምነው።

Let us therefore pray unto Him that the Almighty Lord our God keep us in this Holy day and all the days of our life in all peace.

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ።

You, pray.

ካህን (Priest)

እግዚእ እግዚኦ እግዚአብሔር አኃዜ ኵሉ አቡሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ። ነአኵተከ ላዕለ ኵሉ ግብር በእንተ ኵሉ ግብር ወውስተ ኵሉ ግብር።

ሁሉን የያዝህ ጌታችን እግዚአብሔር የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በሥራው ሁሉ ላይ ፤ ስለ ሥራው ሁሉ ፤ በሥራውም ሁሉ ውስጥ እናመሰግንሃለን።

Master, Lord God Almighty, the Father of our Lord and our God and our Savior Jesus Christ, we render You thanks upon everything, for everything and in everything,

እስመ ሠወርከነ ወረዳእከነ ፤ ዐቀብከነ ወአቅረብከነ ፤ ወተወከፍከነ ኀቤከ ወተማኅፀንከነ ወአጽናዕከነ ፤ ወአብጻሕከነ እስከ ዛቲ ሰዓት።

ሠውረኸናልና ፤ ረድተኸናልና ፤ ጠብቀኸናልና ፤ ወዳንተ አቅርበህ ጠብቀኸናልና ፤ አጽንተህ ጠብቀኸናልና እስከዚህችም ሰዓት አድርሰኸናልና።

for You have covered us and succoured us, have kept us and brought us nigh, and received us unto Yourself, and undertaken our defense, and strengthened us and brought us unto this hour.

**ዲያቆን (Deacon)**

ኀሡ ወአስተብቍዑ ከመ ይምሐረነ እግዚአብሔር ወይሣሀል ላዕሌነ።

እግዚአብሔር ይምረን ዘንድ በእኛም ላይ ይቅር ይል ዘንድ እሹ ፤ ለምኑ።

You entreat and beseech that the Lord have pity upon us and be merciful to us,

ወይትወከፍ ጸሎተ ወስእለተ እምነ ቅዱሳኒሁ በእንቲአነ በዘይሤኒ ኵሎ ጊዜ ይረስየነ ድልዋነ ከመንንሣእ እምሱታፌ ምሥጢር ቡሩክ ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ስለእኛ ከቅዱሳን ጸሎትን ልመናን ይቀበል ዘንድ ፤ ሁልጊዜ ባማረ ነገር ቡሩክ ከሚሆን ምሥጢር አንድነት እንድንቀበል የበቃን ያደርገን ዘንድ።

receive prayer and supplication from His saints on our behalf, according to what is expedient at all times, so that He may make us meet to partake of the communion of the blessed sacrament and forgive us our sins.

**ሕዝብ (*People*)**

ኪርያላይሶን።

አቤቱ ይቅር በለን።

Kyrie eleison.

ካህን (Priest)

በእንተ ዝንቱ ንስእለከ። ወነኀሥሥ እምነ ኂሩትከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ ሀበነ ከመ ንፈጽም ዛተ ዕለተ ቅድስተ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትነ ወበኵሉ ሰላም ምስለ ፈሪሆትከ ኵሎ ቅንዓተ

ስለዚህ እንለምንሃለን። ከቸርነትህም እንሻለን። ሰውን የምትወድ ሆይ ክብርት የምትሆን ይህችን ዕለት እንድንፈጽም ስጠን ፤ የሕይወታችንን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም አንተን ከመፍራት ጋራ።

For this cause we pray and entreat of Your goodness, O lover of man, grant us to complete this Holy day and all the days of our life in all peace along with Your fear.

ወኵሎ መከራ ወኵሎ ግብረ ሰይጣን ወምክረ ሰብእ እኩያን ወእትንሣኤ ፀር ዘኅቡእ ወዘገሃድ። አርኅቅ እግዚኦ እምኔየ ወእምነ ኵሉ ሕዝብከ ወእምዝቱ መካን ቅዱስ ዘዚአከ።

ቅንዓትን ሁሉ ፥ መከራውንም ሁሉ ፤ የሰይጣንንም ሥራ ሁሉ ፥ የክፉዎች ሰዎችንም ምክር ፥ የጠላትንም መነሣት የተሠወረውንና የተገለጸውን አቤቱ ከእኔ ፤ ከሕዝቡም ሁሉ ፤ የአንተ ከሚሆን ከዚህም ቅዱስ ቦታ አርቅ።

All envy, all trial, all the working of Satan, the counsel of evil, and all the uprisings of adversaries, secret and open, remove far from me, and from all Your people and from this Your Holy place. All good things,

ኵሎ ሠናያተ ዘይሤኒ ወዘይኄይስ አዝዝ ለነ እስመ አንተ ዘወሀብከነ ሥልጣነ ከመ ንኪድ ከይሴ ወአቃርብተ ወዲበ ኵሉ ኃይለ ጸላዒ።

በጎውን ነገር ሁሉ ፤ ያማረውንና የሚሻለውን እዘዝልን። እባቡን ጊንጡንም የጠላትንም ኃይል ሁሉ እንረግጥ ዘንድ ሥልጣንን የሰጠኸን አንተ ነህና።

that are expedient and excellent, command You for us, for You are He who has given us power to tread upon serpents and upon all the power of the enemy.

ኢታብአነ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ በጸጋ ወሣህል ዘለፍቅረ ሰብእ ዘበወልድከ ዋሕድ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ

ወደ መከራ አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ። አንድ ልጅህ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ፍቅር ብሎ ባደረገው ቸርነትና ይቅርታ በእርሱ ያለ ምስጋና

Lead us not into temptation, but deliver us and rescue us from all evil in the grace and loving- kindness, which were shown by the love towards mankind of Your only-begotten Son, our Lord, God, and our Saviour Jesus

ስብሐት ወክብር ወእዘዝ ይደሉ ምስሌሁ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ዘዕሩይ ምስሌከ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ክብር ጽንዕ ከእርሱ ጋር ለአንተ ይገባል ፤ ከአንተ ጋራ ትክክል ማኅየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላላሙ አሜን።

Christ, through whom to You with Him and with the Holy Spirit, the life-giver, who is coequal with You are fitting glory, honour, and dominion, both now and ever, and world without end. Amen.

**ንፍቅ ዲያቆን (Ass't *Deacon)***

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

***ሕዝብ (People)***

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

**ንፍቅ ካህን (Ass't Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with your spirit.

ጸሎተ መባእ ዘሐዋርያት

የሐዋርያት የመባ ጸሎት

“The prayer of Oblation” of the Apostles.

## ንፍቅ ካህን (Ass't Priest)

ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ በውስተ ቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተ ክርሲቲያን ፤

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን። ከሁሉ በላይ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን መባ ስለሚያስገቡ መስዋዕቱን ቀዳምያቱን ከአሥር አንዱን

And again let us beseech the Almighty Lord, the Father of the Lord our Savior Jesus Christ, on behalf of those who bring an oblation within the one Holy universal church,

መስዋዕተ ቀዳማያተ ዐሥራተ አኰቴተ ተዝካር ዘብዙኀ ወዘኅዳጥ ዘኅቡእ ወዘገሃድ። ወለእለሂ ይፈቅዱ የሀቡ አልቦሙ ዘይሁቡ

የመታሰቢያ ምሥጋና ብዙውንና ጥቂቱን ፤ የተሠወረውንና የተገለጸውን ይሰጡ ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ፤ ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጥ ዘንድ

a sacrifice, first-fruits, tithes, a thank-offering, a memorial, whether much or little, in secret or openly, and of those who wish to give and have not wherewith to give,

ይትወከፍ ፍትወቶሙ ዘበሰማያት መንግሥተ ይጸጉ ዘለኵሉ ግብረ በረከት ሥልጣን ቦቱ እግዚአብሔር አምላክነ።

ለሁሉ በረከትን የሚያድልበት ሥልጣን ገንዘቡ የሚሆን አምላካችን እግዚአብሔር።

that He accept their ready mind, that He vouchsafe to them the heavenly kingdom; power over all works of blessing belongs to the Lord our God.

ንፍቅ ዲያቆን (Ass't Deacon)

ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ።

መባ ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ።

Pray for them who bring an oblation.

## ሕዝብ (People)

ተወከፍ መባአሙ ለአኃው ፤ ወተወከፍ መባኦን ለአኃት ለነኒ ተወከፍ መባአነ ወቍርባነነ።

የወንዶችን መባ ተቀበል። የሴቶችን መባ ተቀበል ፤ የእኛንም መባችንንና ቍርባናችንን ተቀበል።

Accept the oblation of our brothers, accept the oblation of our sisters, and ours also, accept our oblation and our offering.

## ንፍቅ ካህን (Asst Priest)

እግዚአብሔር አምላክነ ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ በውስተ ቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተ ክርስቲያን።

ሁሉን የምትገዛ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን ፤ እንማልድሃለንም። ከሁሉ በላይ የምትሆን በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መባ ስለሚያገቡ ሰዎች።

Lord our God who are Almighty, we pray You and beseech You for them that bring an oblation within the one Holy universal church,

መሥዋዕተ ቀዳምያተ ዐሥራተ አኰቴተ ተዝካር ዘብዙኀ ወዘኀዳጥ ዘኅቡእ ወዘገሃድ ወለእለሂ ይፈቅዱ የሀቡ አልቦሙ ዘይሁቡ ተወኪፈከ ፍትወቶሙ ሀብ ለኵሎሙ ዐስበ በረከት ክፍለ ትኩን።

መሥዋዕቱን መጀመሪያውን ፤ ከዐሥር አንዱን የመታሰቢያ ምስጋናን ብዙውንና ጥቂቱን የተሰወረውንና የተገለጸውን ይሰጡም ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብለህ ለሁሉም የበረከት ዋጋን ስጥ ዕድል ፈንታ ትሆን ዘንድ።

a sacrifice, first-fruits, tithes, a thank-offering, a memorial, whether much or little, in secret or openly, and have not wherewith to give. Your acceptance of their ready mind grant you unto every one: let the recompense of blessing be a portion to all of them:

በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል፤ ከርሱም ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

through Your only-begotten Son, through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

**ንፍቅ ዲያቆን (Ass't *Deacon*)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

***ሕዝብ (People)***

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

ንፍቅ ካህን (Ass't Priest)

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with your spirit.

ጸሎተ እንፎራ

የኅብስት ጸሎት

The prayer of Oblation.

ካህን(priest)

ኦ ሊቅየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሱታፌ ቀዳማዊ ቃለ አብ ንጹሐ ወቃለ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ አንተ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረድከ እምሰማያት፤

መምህሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከቀዳማዊ አብ ጋር አንድ የምትሆን ንፁሕ የሚሆን የአብ ቃል ፤ የማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ቃል ፤ ከሰማያት የወረድህ፤

O my Master, Jesus Christ, coeternal pure Word of the Father, and Word of the Holy Spirit, the life giver, You are the bread of life which did come down from heaven,

ወአቅደምከ ነጊረ ከመ ትከውን በግዐ ዘአልቦ ነውር በእንተ ሕይወተ ዓለም ወይእዜኒ ንስእል ወናስተበቊዕ እምኔ ኂሩተ ሠናይቲከ።

የሕይወት ኀብስት አንተ ነህ ስለ ዓለሙ መዳን ነውር የሌለበት መሥዋዕት እንድትሆን መናገርን አስቀደምህ። አሁንም ከበጎነትህ ቸርነት እንለምናለን እንማልዳለንም።

and did foretell that You would be the Lamb without spot for the life of the world: We now pray and beseech of Your excellent goodness,

ኦ መፍቀሬ ሰብእ አርኢ ገጸከ ላዕለ ዝንቱ ኅብስት ወዲበ ዝንቱ ጽዋዕ ዘአንበርነ ላዕለ ዝንቱ ታቦት መንፈሳዊ ዘለከ፤

ሰው ወዳጅ ሆይ ያንተ በሚሆን በዚህ በመንፈሳዊ ታቦት ላይ ባኖርነው በዚህ ኅብስት ላይና በዚህ ጽዋ ላይ ፊትህን ግለጽ።

O lover of man, make Your face to shine upon this bread, and upon this cup, which we have set upon this spiritual ark of Yours:

ባርኮ ለዝንቱ ኅብስት። ወቀድሶ ለዝንቱ ጽዋዕ። ወአንጽሖሙ ለ፪ሆሙ። ወሚጠ ለዝንቱ ኅብስት ይኩን ሥጋከ ንጹሐ ወዘተደመረ ውስተ ዝንቱ ጽዋዕ ደመከ ክቡረ ወይኩን ለኵልነ

ይህን ኅብስት ባርከው። ይህንንም ጽዋ አክብረው። ሁለቱን አንጻቸው። ሥጋህን ይሆን ዘንድ ለውጠው በዚህ ጽዋ ውስጥ የተቀዳውም ወይን የከበረ ደምህን ይሁን ለሁላችንም

Bless this bread and hallow this cup and cleanse them both, And change this bread to become Your pure Body, and what is mingled in this cup to become Your precious Blood;

ዕሩገ ወፈውሰ ለመድኃኒተ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ። አንተ ውእቱ ንጉሠ ኵልነ ክርስቶስ አምላክነ ወለከ ንፌኑ ልዑለ ውዳሴ ወስብሐተ ወስግደተ

ይህ ንጹሕ ያረገ ለነፍሳችንና ለሥጋችን ለልቡናችንም ፈውስ ይሆን ዘንድ። አምላካችን ክርስቶስ የሁላችን ንጉሥ አንተ ነህ ከፍ ያለ ምስጋናንና ክብርን ስግደትንም ላንተ እንልካለን ፤

let them be offered for us all for healing and for the salvation of our soul and our body and our spirit. You are the King us all, Christ our God, and to You we send up high praise and glory and worship, with Your

ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ዘዕሩይ ምስሌከ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ ጋራ ፤ ካንተ ጋራ ከሚተካከል ከማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን።

good heavenly Father and the Holy Spirit, the life giver, who is coequal with You, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን

ትእዛዘ አበዊነ ሐዋርያት ኢያንብር ብእሲ ውስተ ልቡ ቂመ ወበቀለ ወቅንዓተ ወጽልአ ላዕለ ቢጹ ወኢላዕለ መኑሂ።

ይህ የአባቶቻችን የሐዋርያት ትእዛዝ ነው። ሰው በልቡናው ቂምና በቀልን ፤ ቅንዓትንና ጠብን በባልንጀራው ላይ በማንም ላይ ቢሆን አይያዝ።

This is the order of our fathers the Apostles: Let none keep in his heart rancour or revenge or envy or hatred towards his neighbor, or towards any other body.

**ዲያቆን (Deacon)**

ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሀት።

በፍርሃት ለእግዚአብሔር ስገዱ።

Worship the Lord with fear.

**ሕዝብ (People)**

ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ።

አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን ፤ እናመሰግንሃለንም።

Before You, Lord, we worship, and we do glorify You.

## ፍትሐት ዘወልድ (The Absolution of the Son.)

ካህን(priest)

እግዚእ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር አብ ዘበተከ እምኔነ ኵሉ ማእሠረ ኃጣውኢነ በሕማማቲከ ማሕየዊት ወመድኀኒት ፧

አቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋሕድ የእግዚአብሔር አብ ቃል ማሕየዊት መድኃኒትም በምትሆን በሕማምህ ከእኛ የኃጢአታችንን ሁሉ ማሠሪያ ያጠፋህ።

Master, Lord Jesus Christ, the only begotten Son, the word of God the Father, who have broken off from us all the bonds of our sins through Your life-giving and saving sufferings,

ዘነፋሕከ ውስተ ገጸ አርዳኢከ ቅዱሳን ወላእካኒከ ንጹሐን ወትቤሎሙ ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ ለእለ ኀደግሙ ኃጢአተ ይትኀደግሎሙ ወለእለ ኢኀደግሙ ኃጢአተ ኢይትኀደግሎሙ።

ንጹሐን በሚሆኑ ደቀመዛሙርትህና በንጹሓን አገልጋዮችህ ፊት እፍ ያልህባቸው "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ይቅር ላላችኋቸው ኃጢአታቸው ይቀርላቸዋል ይቅርም ላላችኋቸው ኃጢአታቸው አይቀርላቸውም" ያልካቸው።

who did breathe upon the face of Your Holy disciples and pure ministers saying to them: "Receive the Holy Spirit: whatsoever men's sins you remit they are remitted unto them, and whatsoever sins you retain they are retained:"

አንተ ኦ እግዚኦ ይእዜኒ ጸጎከ ክህነተ ለላእካኒከ ንጹሓን ለእለ ይገብሩ ግብረ ክህነት ኵሎ ጊዜ በቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት ከመ ይኅድጉ ኃጢአተ በዲበ ምድር ይእሥሩ ወይፍትሑ ኵሎ ማእሠረ ዐመፃ።

አሁንም በክብርት ቤተ ክርስቲያንህ ሁልጊዜ የክህነት ሥራ ለሚሠሩ ለንጹሐን አገልጋዮችህ አቤቱ አንተ ክህነትን ሰጠህ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር ይሉ ዘንድ ያሥሩም ዘንድ የበደልንም ማሠሪያ ሁሉ ይፈቱ ዘንድ።

You, therefore, O Lord, have now granted the priesthood to Your pure ministers that do the priests' office at all times in Your Holy church that they may remit sin on earth, may bind and loosen all the bonds of iniquity.

ወይእዜኒ ካዕበ ንስእል ወናኀሥሥ እምነ ኂሩትከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ ፤ በእንተ እሉ አግብርቲከ ወአእማቲከ አበውየ ወአኀውየ ወአኃትየ ወበእንቲአየሂ አነ ገብርከ ድኩም ፤

አሁንም አቤቱ ሰው ወዳጅ ሆይ ዳግመኛ ከቸርነትህ እንለምናለን ፤ እንሻለን። ስለነዚህ ስለወንዶችም ስለ ሴቶችም አገልጋዮችህ አባቶቼና ወንድሞቼ እህቶቼም ደካማ ስለምሆን ስለእኔም ስለ ባርያህ፤

Now again we pray and entreat of Your goodness, O lover of man, on behalf of these Your servants and hand-maids, my fathers and my brothers and my sisters, and also on my own behalf, on me Your feeble servant,

ወበእንተ እለ አድነኑ አርእስቲሆሙ ቅድመ ምሥዋዒከ ቅዱስ ጺሕለነ ፍኖተ ምሕረትከ ብትክ ወምትር ኵሎ ማእሠረ ኃጣውኢነ። ለእመ አበስነ ለከ እግዚኦ በአእምሮ አው ዘእንበለ አእምሮ አው በጽልሑት፤

በቅዱስ መሠዊያህ ፊት ራሳቸውን ዝቅ ስላደረጉ ሰዎች የምሕረትን ጎዳና ጥረግልን ፤ የኃጢአታችንን ማሠሪያም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋልን። አቤቱ አንተን ብንበድል በማወቅ ወይም ባለማወቅ በተንኰልም ቢሆን፤

and on behalf of them that bow their heads before Your Holy altar: prepare for us the way of Your mercy, break and sever all the bonds of our sins. Whether we have trespassed against You, O Lord, wittingly or unwittingly

አው በእከየ ልብ አው በገቢር አው በተናግሮ አው በናእሰ ልብ እስመ አንተ ተአምር ድካሞ ለሰብእ ፤ ኦ ኄር ወመፍቀሬ ዕጓለ እመሕያው ወእግዚአ ኵሉ ፍጥረት ጸግወነ ለነ እግዚኦ ሥርየተ ኃጣውኢነ።

በልቦና ክፋትም ቢሆን ፤ በመሥራትም ቢሆን ፤ በመናገርም ቢሆን ፤ በዕውቀት ማነስም ቢሆን የሰውን ድካሙን አንተ ታውቃለህና ፤ ቸር ሰው ወዳጅ ሆይ የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ አቤቱ የኃጢአታችንን ሥርየት ስጠን።

or in deceit or in evilness of heart, whether in deed or in word or through smallness of understanding, for You know the feebleness of man. O good lover of man and Lord of all creation, grant us, O Lord, forgiveness of our sins,

ባርከነ ወቀድሰነ ወአግዕዘነ ወአንጽሐነ ወረስየነ ፍቱሐነ ወግእዛነ ወለኵሉ ሕዝብከ ፍትሐሙ ፤ ወምላዕ ላዕሌነ ፈሪሆተ ስምከ ወአቁመነ ኀበ ገቢረ ፈቃድከ ቅዱስ።

ባርከን አክብረንም ነጻም አድርገን ፤ አንጻን የተፈታን ነጻም የወጣን አድርገን ፤ ሕዝቡንም ሁሉ ፍታቸው ስምህን መፍራትንም የተመላን አድርገን ቅዱስ ፈቃድህንም በመፍራት አጽናን።

bless us and purify us and set us free and absolve all Your people and fill us with the fear of Your name, and establish us in the doing of Your Holy will.

ኦ ኄር እስመ አንተ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወለከ ንፌኑ ስብሐተ ወክብረ ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ዘዕሩይ ምስሌከ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ቸር ሆይ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን አንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ነህና ምስጋናንና ክብር ላንተ እናቀርባለን ፤ ሰማያዊ ከሚሆን ከቸር አባትህ ጋራ ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ትክክል የሚሆን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

O Good, for You are our Lord and our God and our Saviour Jesus Christ, to You we send glory and honour with Your good heavenly Father, and the Holy Spirit, the life-giver, who is coequal with You, both now and ever and world without end. Amen.

በየምዕራፉ "አሜን ኪርያላይሶን አቤቱ ይቅር በለን" እንበል።

We shall say after each clause: "Amen Kyrie eleison, Lord have mercy upon us"

**ዲያቆን (Deacon)**

በእንተ ቅድሳት ሰላማዊት ሰላመ ናስተበቊዕ ከመ እግዚአብሔር ያስተሳልመነ በሣህለ ዚአሁ።

አንድ ስለምታደርግ ሥጋውና ደሙ እግዚአብሔር በይቅርታው አንድ ያደርገን ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን።

For the peaceful Holy things we beseech, that God may grant us peace through His Mercy.

በእንተ ሃይማኖትነ ናስተበቊዕ ከመ እግዚአብሔር የሀበነ እንቲአሁ ሃይማኖተ በንጹሕ ንዕቀብ።

እግዚአብሔር የእርሱን ሃይማኖት በንጹሕ እንድንጠብቅ ይሰጠን ዘንድ ስለ ሃይማኖታችን እንማልዳለን።

For our Faith we beseech, that God may grant us to keep the faith in purity.

በእንተ ማኅበረነ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር እስከ ፍጻሜነ በኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ይዕቀበነ።

እስከ ፍጻሜያችን ድረስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አንድነት ይጠብቀን ዘንድ ስለ አንድነታችን እንማልዳለን።

For our congregation we beseech, that God may keep us unto the end in the communion of the Holy Spirit.

በእንተ ትዕግሥታተ ነፍሳት ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር በኵሉ ምንዳቤነ ፍጻሜ ትዕግሥት ይጸግወነ።

በመከራችን ሁሉ እግዚአብሔር የትዕግሥትን ፍጻሜ ይሰጠን ዘንድ ፤ ስለ ነፍሳችን ትዕግሥት እንማልዳለን።

For patience of soul we beseech, that God may vouchsafe us perfect patience in all our tribulation.

በእንተ ነቢያት ቅዱሳን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ምስሌሆሙ ይኈልቈነ።

ቅዱሳን ስለሚሆኑ ነቢያት ከሳቸው ጋራ እግዚአብሔር ይቈጥረን ዘንድ እንማልዳለን።

For the Holy prophets we beseech, that God may number us with them.

በእንተ ሐዋርያት ላዕካን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀበነ ናሥምር በከመ እሙንቱ አሥመርዎ ወመክፈልቶሙ ይክፍለነ።

እነሱ ደስ እንዳሰኙት ደስ ልናሰኘው እግዚአብሔር ማግልገሉን ይሰጠን ዘንድ ፤ ዕድል ፈንታቸውንም ያድለን ዘንድ ፤ አገልጋዮች ስለሚሆኑ ሐዋርያት እንማልዳለን።

For the ministering Apostles we beseech, that God may grant us to be well pleasing even as they were well pleasing, and apportion unto us a lot with them.

በእንተ ቅዱሳን ሰማዕታት ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀበነ ንፈጽም ኪያሃ ግዕዘ።

እግዚአብሔር ለእኛ የሰማዕትነትን ሥራ ይሰጠን ዘንድ ፤ ቅዱሳን ስለሚሆኑ ሰማዕታት እንማልዳለን።

For the Holy martyrs we beseech, that God may grant us to perfect the same conversation.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

በእንተ ሊቀ ጳጳስነ አባ …… ወብጹዕ ጳጳስ አባ ……. ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀበነ ኪያሆሙ ለነዋህ መዋዕል በልቡና ያርትዑ ቃለ ሃይማኖት በንጹሕ ዘእንበለ ነውር እስመ

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እነሱ ናቸውና እግዚአብሔር እነሱን ለረዥም ወራት ይሰጠን ዘንድ ፤ ያለ ነውር በንጽሕና ሆነው በዕውቀት የሃይማኖትን ቃል ያቀኑ ዘንድ ፤ ስለ

For our Patriarch Abba …….and the blessed Archbishop Abba ……we beseech, that God may grant them length of days to be over us, that with understanding they may rightly speak the word of faith in purity without spot for

እሙንቱ ቀዋምያኒሃ ለቤተ ክርስቲያን።

ሊቀ ጳጳሳችን ስለ አባ ...... ብፁዕ ስለሚሆን ጳጳሳችንም ስለ አባ ......እንማልዳልን።

that they are the defenders of the church.

በእንተ ቀሳውስት ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ኢያሰስል እምኔሆሙ መንፈሰ ክህነት ጻሕቀ ወፍርሀተ ዚአሁ እስከ ፍጻሜ ይጸጉ ወፃማሆሙ ይትወከፍ።

የክህነትን ስልጣን ከእነርሱ እግዚአብሔር እንዳያርቅ መትጋትን ፣ እሱን መፍራትን እስከ ፍጻሜ ይሰጥልን ዘንድ ፤ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ፤ ስለ ቀሳውስት እንማልዳለን።

For the priests we beseech, that God may never take from them the spirit of priesthood, and may give them the grace of zeal and fear of Him unto the end and accept their labour.

በእንተ ዲያቆናት ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ ምርዋጸ ፍጹመ ይሩጹ ወበቅድስና ይቅረቡ ፃማሆሙ ወፍቅሮሙ ይዘከር።

ፈጽመው ሊፋጠኑ መፋጠንን እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ፤ በቅድስናም ይቀርቡ ዘንድ ፤ ድካማቸውንና ፍቅራቸውን ያስብ ዘንድ ፤ ስለዲያቆናት እንማልዳለን።

For the deacons we beseech, that God may grant them to run a perfect course, and draw them nigh unto Him in Holiness, and remember their labour and their love.

በእንተ ንፍቀ ዲያቆናት ወአናግንስጢስ ወመዘምራን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ ፃሕቀ ሃይማኖቶሙ ይፈጽሙ።

የሃይማኖታቸውን ትጋት ሊፈጽሙ እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ፤ ስለ ንፍቀ ዲያቆናት ፤ ስለ አንባቢዎችም ፤ ስለመዘምራንም እንማልዳለን።

For the assistant deacons and the Anagonists (readers) and the singers we beseech, that God may grant them to perfect the diligence of their faith.

በእንተ መበለታት ወመዓስባት ናስተበቊዕ ከመ እግዚአብሔር ይስማዕ ስእለቶን ወፈድፋደ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ይጸግዎን ውስተ አልባቢሆን ወይትወከፍ ፃማሆን።

ልመናቸውን ይሰማቸው ዘንድ ፤ ይልቁንም የመንፈስ ቅዱስን ሀብት በልቡናቸው ያሳድርባቸው ዘንድ ፤ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ፤ ስለ ባልቴቶች ፤ ረዳትም ስለሌላቸው እንማልዳለን።

For the widows and the bereaved we beseech, that God may hear their prayers and vouchsafe them abundantly in their hearts the grace of the Holy Spirit and accept their labour.

በእንተ ደናግል ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ አክሊለ ድንግልና ወይኩኑ ለእግዚአብሔር ውሉደ ወአዋልደ ወይትወከፍ ፃማሆሙ።

እግዚአብሔር የድንግልናቸውን ዋጋ (አክሊል) ይሰጣቸው ዘንድ ፤ ለእግዚአብሔርም ወንዶችም ሴቶችም ልጆች ይሆኑት ዘንድ ፤ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ፤ ስለ ደናግል እንማልዳለን።

For the virgins we beseech, that God may grant them the crown of virginity, and that they maybe unto God sons and daughters and that He may accept their labour.

በእንተ መስተዓግሣን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ አስቦሙ በትዕግሥት ይንሥኡ።

በመታገሣቸው ዋጋቸውን ይቀበሉ ዘንድ ፤ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ስለሚታገሡ ሰዎች እንማልዳለን።

For those who suffer patiently we beseech, that God may grant them to receive their rewards through patience.

በእንተ ሕዝባዊያን ወመሃይምናን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ ሃይማኖተ ፍጹመ በንጹሕ ይዕቀቡ።

በንጽሕና ሆነው ይጠብቁ ዘንድ ፤ እግዚአብሔር ሃይማኖትን እንዲሰጣቸው ስለ ሕዝባውያንና ስለ መሃይምናን እንማልዳለን።

For the laity and faithful we beseech, that God may grant them complete faith which they may keep in purity.

በእንተ ንዑሰ ክርስቲያን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ መክፈልተ ሠናየ ወሕፅበተ ዳግም ልደት ለሥርየተ ኃጢአት ወበማኅተመ ቅድስት ሥላሴ ይኅትሞሙ።

በጎውን ዕድል ኃጢአትን ለማስተሥረይ ሁለተኛ መወለድ የሚገኝበትን ሕፅበት እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ፤ በቅድስት ሥላሴም ማኅተም ያከብራቸው ፤ ያትማቸው ዘንድ ፤ ስለ ንዑሰ ክርስቲያን እንማልዳለን።

For the catechumens we beseech, that God may grant them a good portion and the washing of regeneration for the remission of sin, and seal them with the seal of the Holy Trinity.

በእንተ መፍቀሪተ እግዚአብሔር ሀገሪትነ ኢትዮጵያ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ብዙኃ ሰላመ ይጸጉ በማዕከሌሃ።

ዘወትር ፍጹም ሰላምን እግዚአብሔር ይሰጣት ዘንድ ፤ እግዚአብሔርን ስለምትወድ ስለ አገራችን ኢትዮጵያ እንማልዳለን።

For our country Ethiopia Lover of God we beseech, that God may grant her peace.

በእንተ መኳንንት ወእለ በሥልጣናት ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ጥበበ ወፍርሀተ ዚአሁ የሀቦሙ።

ዕውቀትን እርሱን መፍራትንም እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ፤ ስለ መኳንንትና ሥልጣን ስላላቸው እንማልዳለን።

For the rulers and those in authority we beseech, that God may grant them of His wisdom and His fear.

በእንተ ኵሉ ዓለም ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ያቅድም ሐልዮ ወየሐሊ ለለ፩ዱ ጻሕቀ ዘይሤኒ ወዘይኄይስ።

ስለ ዓለሙ ሁሉ እግዚአብሔር ማሰብን ያስቀድም ዘንድ ፤ ለእያንዳንዱም የሚያስፈልገውን ፣ ያማረውን የሚሻለውንም ያስብ ዘንድ ፤ ስለ ዓለም ሁሉ እንማልዳለን።

For the whole world we beseech, that God should hasten His purpose and put into the mind of all and each to desire that which is good and expedient.

በእንተ እለ ይነግዱ በባሕር ወበየብስ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር በየማኑ ሣህል ይምርሆሙ ወያግብኦሙ ኀበ ማኅደሪሆሙ በዳኅና ወበሰላም።

እግዚአብሔር ይቅርታ ባለው ቀኝ መርቶ በፍቅርና በደኅንነት ወደ ማደሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ ፤ በባሕርና በደረቅ ስለሚሄዱ ሰዎች እንማልዳለን።

For them that travel by sea and by land we beseech, that God should guide them with a merciful right hand and let them enter their home in safety and peace.

በእንተ ርኁባን ወጽሙዓን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ ሲሳዮሙ ዘለለዕለቱ፡

እግዚአብሔር የዕለት የዕለት ምግባቸውን ይሰጣቸው ዘንድ ፤ ስለ ተራቡና ስለ ተጠሙ ሰዎች እንማልዳለን።

For the hungry and the thirsty we beseech, that God should grant them their daily food.

በእንተ ኅዙናን ወትኩዛን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ይናዝዞሙ ፍጹመ።

እግዚአብሔር ፈጽሞ ያረጋጋቸው ዘንድ ፤ ስለ አዘኑና ስለ ተከዙ ሰዎች እንማልዳለን።

For the sad and the sorrowful we beseech, that God may give them perfect consolation

በእንተ ሙቁሓን ናስተበቊዕ ከመ እግዚአብሔር ይፍትሖሙ እማዕሠሪሆሙ።

እግዚአብሔር ከእሥራታቸው ይፈታቸው ዘንድ ፤ ስለታሠሩ ሰዎች እንማልዳለን።

For the prisoners we beseech, that God may loose them from their bonds.

በእንተ ፂዉዋን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ይሚጦሙ በሰላም ውስተ ብሔሮሙ።

እግዚአብሔር በሰላም ወደ አገራቸው ይመልሳቸው ዘንድ ፣ ስለ ተማረኩ ሰዎች እንማልዳለን።

For the captives we beseech, that God may restore them to their county in peace.

በእንተ ስዱዳን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ ትዕግሥተ ወትምህርተ ሠናየ ወይጸጉ ፃማሆሙ ፍጹመ።

እግዚአብሔር ትዕግሥትን ፤ በጎ ትምህርትንም ይሰጣቸው ዘንድ ፤ የድካማቸውንም ፍጹም ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ ፤ ስለ ተሰደዱ ሰዎች እንማልዳለን።

For those who were refugees we beseech, that God may grant them patience and good instruction, and give them complete reward for their labour.

በእንተ ሕሙማን ወድውያን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ፍጡነ ይፈውሶሙ ወይፈኑ ሣህለ ወምሕረተ ላዕሌሆሙ።

እግዚአብሔር ፈጥኖ ያድናቸው ዘንድ ፤ ይቅርታውንና ቸርነቱንም ይልክላቸው ዘንድ ፤ ስለ ታመሙትና ስለ ድውያኑ እንማልዳለን።

For the sick and the diseased we beseech, that God should heal them speedily and send upon them mercy and compassion.

በእንተ እለኖሙ እምቅድስት ቤተ ክርስቲያን ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ይጸግዎሙ መካነ ዕረፍት።

ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወገን ስለ ሞቱ ሰዎች እግዚአብሔር የዕረፍት ቦታ ይሰጣቸው ዘንድ እንማልዳለን።

For those who have fallen asleep in his holy church we beseech, that God may vouchsafe them a place to rest.

በእንተ እለ አበሱ አበዊነ ወአኀዊነ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ኢይትቀየሞሙ ናኁየ ወሣኅተ የሀቦሙ እመዓቱ።

እግዚአብሔር እንዳይቀየማቸው ከመዓትም ተመልሶ ፍጹም ዕረፍትን ይሰጣቸው ዘንድ ፤ ስለ በደሉ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን እንማልዳለን።

For those who have sinned, our fathers and our brothers we beseech, that God cherish not anger against them, but grant them rest and relief from His wrath.

በእንተ ዝናማት ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር ይፈኑ ዝናመ ኀበ ዘይትፈቀድ መካን።

በሚሻበት ቦታ እግዚአብሔር ዝናሙን ያዘንም ዘንድ ፤ ስለ ዝናም እንማልዳለን።

For the rains we beseech, that God may send rain on the place that needs it.

በእንተ ማያተ አፍላግ ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሐየር ይምላዕ ኪያሆን እስከ መስፈርት ወዓቅም።

የወንዞችን ውኃ ምላልን ብለን እግዚአብሔር እነሱን እስከ ልካቸውና እስከ ወሰናቸው ይመላ ዘንድ ፤ ስለ ወንዝ ውኃ እንማልዳለን።

For the water of the rivers we beseech, that God should fill them unto their due measure and bounds.

በእንተ ፍሬ ምድር ናስተበቍዕ ከመ እግዚአብሔር የሀባ ፍሬሃ ለምድር ለዘርዕ ወለማዕረር።

ለዘርና ለመከር ሊሆን እግዚአብሔር ለምድር ፍሬዋን ይሰጣት ዘንድ ፤ ስለ ምድር ፍሬ እንማልዳለን።

For the fruits of the earth we beseech, that God may grant to the earth her fruit for sowing and for harvest.

ወለኵልነ እለ በጸሎት ንስእል ወናስተበቍዕ በመንፈሰ ሰላም ይክድነነ ወይጸግወነ ወያብርህ አዕይንተ አልባቢነ።

በጸሎት የምንለምንና የምንማልድ ሁላችንን በሰላም በመንፈስ ይጠብቀን። ፍቅርንም ይስጠን። ዓይነ ልቡናችንንም ያብራልን።

And all of us who ask and beseech in prayer, may He cover us with the spirit of peace, and give us grace, and enlighten eyes of our hearts.

ንቅረብ ወንስአሎ ለእግዚአብሔር ከመ ተሠጢዎ ጸሎተነ ይትወከፍ ፤ ንትነሣእ እንከ በመንፈስ ቅዱስ ከመ ለቢወነ ንልሐቅ በጸጋሁ ወንትመካህ በስመ ዚአሁ።

ፈቃዱም ሆኖ ጸሎታችንን ይቀበል ዘንድ ቀርበን እግዚአብሔርን እንለምነው። አውቀን በኃብቱ እናድግ ዘንድ ፤ በእርሱም ስም እንመካ ዘንድ ፤

Let us draw high and ask God to accept our prayers according to His will. Let us therefore rise in the Holy Spirit, growing in His grace, with understanding, glorying in His name

ወንትሐነጽ ዲበ መሠረተ ነቢያት ወሐዋርያት ንቅረብ ወንስአሎ ለእግዚአብሔር አምላክነ ከመ ተሠጢዎ ጸሎተነ ይትወከፍ።

በነቢያት በሐዋርያትም መሠረት ላይ እንታነጽ ዘንድ ፤ እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ እንነሣ። ቀርበን አምላካችንን እግዚአብሔርን እንለምነው ወዶ ጸሎታችንን ይቀበል ዘንድ።

and built upon the foundation of the prophets and the apostles. Let us draw high and ask Lord God to accept our prayers according to His will.

**ዲያቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us. upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን (Priest)

**ንስግድ (፫ ጊዜ)**

እንስገድ

Let us worship (to be repeated thrice)

ሕዝብ (People)

ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ሠለስቱ አሐዱ።

ሦስት ሲሆኑ አንድ ለሚሆኑ ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም።

The Father and the Son and the Holy Spirit, three in one.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኪ።

ሰላም ላንቺ ይሁን።

Peace be unto You:

**ሕዝብ (People)**

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ መለኮት።

የመለኮት ማደሪያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን።

Holy church, dwelling-place of the Godhead.

ካህን (Priest)

ሰአሊ ለነ።

ለምኝልን።

Ask for us:

ሕዝብ (People)

ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ።

አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም።

Virgin Mary, mother of God,

## ካህን (Priest)

አንተ ውእቱ።

አንቺ ነሽ።

You are:

**ሕዝብ (People)**

ማዕጠንት ዘወርቅ አንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደስ።

ቡሩክ ከቤተ መቅደስ የተቀበላት የእሳትን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ።

The golden censer which did bear the coal of fire which the blessed took from the sanctuary,

ዘይሠሪ ኃጢአተ ወይደመስስ ጌጋየ ፤ ዝውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ እጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ።

ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ፤ በደልንም የሚያጠፋ ይኸውም ካንቺ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

and which forgives sin and blots out error, who is God’s Word that was made man from You, who offered Himself to His Father for incense and an acceptable sacrifice.

ንሰግድ ለከ ክርስቶስ ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ።

ክርስቶስ ሆይ ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ ጋራ ፤ መድኃኒት ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ እንሰግድልሃለን ፤ መጥተህ አድነኸናልና።

We worship You, Christ, with Your good heavenly Father and the Holy Spirit, the life-giver, for You did come and save us.

**ዲይቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us. upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

## ንፍቅ ካህን (Asst.Priest)

እግዚአ አእምሮ ወዜናዌ ጥበብ ዘከሠተ ለነ ዘኮነ ሥውረ ውስተ ማዕምቀ ጽልመት ወሃቤ ቃለ ትፍሥሕት ለእለ ይሰብኩ ዕበየ ኃይልከ።

የዕውቀት ባለቤት ጥበብን የሚያናግር በጥልቅ ጨለማ ውስጥ ተሠውሮ የነበረውን የገለጽክልን የኃይልህን ከፍታ ለሚሰብኩ የደስታ ቃልን የምትሰጥ።

Lord of knowledge, declarer of wisdom, who have revealed to us what was hidden in the depth of darkness, giver of a word of gladness to them that preach the greatness of Your power.

አንተ ውእቱ በብዙኀ ኂሩትከ ጸዋዕኮ ለጳውሎስ ዘኮነ ቀዲሙ ሰዳዴ ወረይሰኮ ንዋየ ኅሩየ። ወበዝንቱ ሠመርኮ ከመ ይኩን ሐዋርያ ወሰባኬ ወንጌል መንግሥትከ ጸዋዒ።

ቀድሞ ያሳድድ የነበረ ጳውሎስን በብዙ ቸርነትህ የጠራኸው የተመረጠ ዕቃም ያደረግኸው አንተ ነህ። በዚህም ወደድኸው ሐዋርያ ይሆን ዘንድ የምትጠራ የመንግሥትህንም ወንጌል የሚያስተምር ይሆን ዘንድ።

It was You that, after Your great goodness, did call Paul who was previously a persecutor, and did make him a chosen vessel, and were will-pleased with him that he should become a preacher of the Gospel of Your kingdom which called him to be an apostle.

ኦ ክርስቶስ አምላክነ አንተ ውእቱ መፍቀሬ ሰብእ። ኦ ኄር ጸግወነ ልቡና ዘእንበለ ግብር ወሕሊና ንጹሐ ዘኢይትአተት እምኀቤከ።

አምላካችን ክርስቶስ ሆይ ሰውን የምትወድ አንተ ነህ። ቸር ሆይ ያለ ሥራ ዕውቀትን ካንተ የማይለይ ንጹሕ ሕሊናን ስጠን።

O Christ our God. You are a lover of man. O Good, vouchsafe us a mind without distraction and a pure understanding that departs not from You,

ከመ ናእምር ወንለቡ ወንጠይቅ መጠነ ትምህርትከ ቅድስት ዘተነበት በላዕሌነ ይእዜኒ እምኀቤሁ። ወበከመ ተመሰለ ብከ ኦ ርእሰ ሕይወት ከማሁ ለነኒ ረስየነ ድልዋነ ንትመሰል ኪያሁ በምግባር ወበሃይማኖት፤

ዛሬም ከርሱ ዘንድ በኛ ላይ የተነበበች ክብርት የምትሆን የትምህርትን ልክ እናውቅ እናስተውል እንረዳ ዘንድ። የሕይወት ራስ ሆይ አንተን እንደመሰለ እኛም እንደሱ በምግባር በሃይማኖት እሱን እንመስል ዘንድ የበቃን አድርገን።

that we may both perceive and know how great is Your Holy teaching which is now read to us out of him, And as he imitated You, O Prince of life, so make us also meet to imitate him in deed and in faith,

ወንሰብሕ ለስምከ ቅዱስ ወንትመካህ በክቡር መስቀልከ ኵሎ ጊዜ፤ እስመ ለከ ይእቲ መንግሥት ወኃይል፤ ዕበይ ወሥልጣን ፤ ክብር ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።

ቅዱስ ለሚሆን ለስምህ ምስጋና እናቀርብ ዘንድ ፤ ክቡር በሚሆን በመስቀልህም እንመካ ዘንድ። መንግሥት ያንተ ናትና ከሃሊነት ገናንነትና ሥልጣን ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ።

and to glorify Your Holy name and glory in Your precious cross at all times: for Yours is the kingdom and might, majesty and sovereignty, honour and glory, world with out end.

ሕዝብ

አሜን

Amen

ካህናት (Priests) ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ።

ሕዝብ (People) ይደልዎሙ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

ካህናት (Priests) አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሥሉስ ዕሩይ ኵሎ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም።

ሕዝብ (People) አሜን።

ልዩ ሦስት ለሚሆኑ ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ሁልጊዜ ክብር ምስጋና ይገባቸዋል ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Glory and honor are meet to the Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit at all Both now and ever and world without end. Amen.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

ኵሉ ዘኢያፈቅሮ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዘኢየአምን ልደቶ እማርያም እምቅድስት ድንግል በ፪ኤ ታቦተ መንፈስ ቅዱስ እስከ ምጽአቱ ሐዳስ በከመ ይቤ ጳውሎስ ውጉዝ ለይኩን።

ጌታችንንና መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወደው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከቅድስት ማርያም መወለዱን የማያምን ሰው ሁሉ እንግዳ እስከሚሆን ምጽአቱ ድረስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ የተለየ ይሁን።

Every one that loves not our Lord and our Saviour Jesus Christ, and believes not in His birth from Holy Mary, of twofold virginity, the ark of the Holy Spirit, until His coming again, let him be anathema as Paul said.

የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት
እየተነበበ ነው።

Reading the Epistle of St. Paul.

ዲያቆን(deacon)

በረከተ አብ ወፍተ ወልድ ወሀብተ መንፈስ ቅዱስ ዘወረደ ላዕለ ሐዋርያት በጽርሐ ጽዮን ቅድስት ከማሁ ይረድ ወይትመከዐብ ላዕሌየ ወላዕለ ኵልክሙ።

ቅድስት በምትሆን በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት ላይ የወረደው የአብ በረከት የወልድም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ሀብት በሁላችሁም ላይ ይውረድ ዕፅፍ ድርብም ይሁን።

Holy Apostle The blessing of the Father and the lover of the Son and the gift of the Holy Spirit who come down upon the apostles in the upper room of holy Zion, in like sort come down and be multiplied upon me and all of you.

ሕዝብ (People)

ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሠናየ መልእክት ፈዋሴ ዱያን ዘነሣእከ አክሊለ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ ያድኅን ነፍሳተነ በብዝኁ ሣህሉ ወምሕረቱ በእንተ ስሙ ቅዱስ።

አክሊልን የተቀበልህ ፧ ድውያንን የምታድን ፧ መልእክትህ የበጀ ፧ ክቡር የምትሆን ጳውሎስ ሆይ ፧ በይቅርታውና ቸርነቱ ብዛት ስለቅዱስም ስሙ ሰውንታችንን ያድን ዘንድ ስለኛ ለምን ጸልይም።

Holy Apostle Paul, good messenger, healer of the sick, who have received the crown, ask and pray for us in order that He may save our souls in the multitude of His mercies and in His pity for His Holy name's sake.

**ዲይቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ(People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us. upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

## ካህን (Priest)

ኦ አምላክ ዘለዓለም ቀዳሚ ወደኃሪ ዘአልብከ ጥንት ወኢተፍጻሜት ዘዐቢይ በተኬንዎቱ ፤ ወኃያል በምግባሩ ፤ ወጠቢብ በምክሩ ፤ ወጽኑዕ በኃይሉ ፤ ዘህልው ውስተ ኵሉ።

የዘላለም አምላክ ሆይ ቀዳማዊ ደኃራዊ የምትሆን ጥንትም ፍጻሜም የሌለህ። በመፍጠሩ ገናና የሚሆን ፤ በሥራውም ኃያል የሚሆን በምክሩም ዐዋቂ ፤ በኃይሉም ጽኑ የሚሆን በሁሉ አድሮ

O eternal God, the first and the last, who has neither beginning nor end, He that is great in his construction and mighty in his work and wise in his counsel and firm

ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ተሀሉ ምስሌነ በዛቲ ሰዓት አርኢ ገጸከ ላዕሌነ ወንበር ምስሌነ በማእከሌነ። ወአንጽሕ አልባበነ ወቀድስ ነፍስተነ ወሥረይ ኃጢአተነ

የሚኖር። በዚች ሰዓት ከኛ ጋራ ትሆን ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም። ለኛ ፊትህን ግለጽልን። ከኛም ጋራ በመካከላችን ኑር። ልቦናችንንም አንጻ ሰውነታችንንም አክብር፤

in His power, who exists in all: We pray You and beseech You to be with us in this hour: make Your face to shine upon us, and abide with us in the midst of us: And purify our hearts, and sanctify our souls, and remit our sins,

ዘገበርነ በፈቃድነ ወዘእንበለ ፈቃደከ ረስየነ እግዚኦ ናቅርብ ኀቤከ መሥዋዕተ ንጹሐ ወቍርባነ ነባቤ ወዕጣነ መንፈሳዌ ይባእ ውስተ ጽርሐ ቅዱስ ቅዱሳቲከ በዋሕድ ወልድከ

ያለፈቃድህ በፈቃዳችን የሠራነውንም ኃጢአታችንን አስተሥርይ። ንጹሑን መሥዋዕት ነባቢውን ቍርባንና መንፈሳዊውን ዕጣን አቤቱ ወዳንተ እንድናቀርብ አድርገን። ወደ ልዩ ምስጋናህ አዳራሽ ይገባ ዘንድ፤

which we have done with our will against Your will: make us, Lord, to offer unto You a pure sacrifice, a reasonable offering and a spiritual incense: let it enter into the Holy temple of Your Holiness:

እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም።

በአንድ ልጅህ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።

through Your only-begotten Son, Our Lord Jesus Christ, and through the Holy Spirit.

## ዲያቆን ንፍቅ (Asst.Deacon)

ነገር ዘእመልእክተ........ ረድኡ ወሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው ረድኡ ከሚሆን.......... መልእክት የተገኘ ቃል ይህ ነው። ጸሎቱና በረከቱ በሁላችን ሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ይኑር ለዘ|ለዓለሙ አሜን።

The word from the Epistle of ........ disciple and apostle of our Lord Jesus Christ. His prayer and blessing be with us all for ever. Amen.

፪ኛ መልእክት እየተነበበ ነው።

Reading the 2nd Epistle.

## ዲያቆን ንፍቅ (Assistant *Deacon*)

ኦ አኃውየ ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢዘሀሎ ውስተ ዓለም። ዓለሙኒ ኃላፊ ፍትወቱኒ ኀላፊ እስመ ኵሉ ኀላፊ ውእቱ።

ወንድሞቼ ይህን ዓለም አትውደዱት በዓለሙ ውስጥ ያለውንም። ዓለሙም አላፊ ነው፤ ፈቃዱም አላፊ ነው፤ ሁሉም አላፊ ነውና።

O my brothers, love not the world neither the things that are in the world. The world passes away and the lust thereof, for all is passing.

**ሕዝብ (People)**

ቅዱስ ሥሉስ ዘኅቡር ህላዌከ ዕቀብ ማኅበረነ በእንተ ቅዱሳን ኅሩያን አርዳኢከ ናዝዘነ በሣህልከ በእንተ ቅዱስ ስምከ።

ባሕርይህ አንድ የሚሆን ልዩ ሦስት ሆይ አንድነታችንን ጠብቅ ፤ ስለተመረጡ ክቡራን ደቀ መዛሙርትህ በይቅርታህ አጽናናን ክቡር ስለሚሆን ስለ ስምህ ብለህ።

Holy consubstantial Trinity, preserve our congregation for Your Holy elect disciples' sake: comfort us in the mercy, for Your Holy name's sake.

**ዲይቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን (Priest)

እግዚእነ ወአምላክነ አንተ ውእቱ ለሐዋርያቲከ ቅዱሳን ከሠትከ ሎሙ ምሥጢረ ስብሐተ ወንጌለ መሢሕከ ፤ ወወሀብኮሙ ዐቢየ ሀብተ እንተ አልባቲ ኍልቍ።

ጌታችን አምላካችን ሆይ የመሢህን የወንጌል ክብር ምሥጢር ቅዱሳን ለሚሆኑ ለሐዋርያት የገለጽህላቸው አንተ ነህ። ከቸርነትህ የምትሆን ስፍር ቍጥር የሌላት ደገኛ ሀብትንም የሰጠሃቸው፡፡

Our Lord and Our God, it was You did reveal to Your Holy apostles the mystery of the glorious of Your Messiah, and did give them the great and immeasurable gift that is of Your grace,

እንተ ይእቲ እምጸጋከ ወፈነውኮሙ ይስብኩ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ብዕለ ጸጋከ ዘኢይትዐወቅ ምሕረትከ። ወንሕነኒ እግዚኦ ንስእለከ ወናስተበቊዐከ ከመ ትረስዮኑ ድልዋነ ለርስቶሙ ወለመክፈልቶሙ ፤

ይህችውም ከቸርነትህ የተገኘች ናት። የማይታወቅ የቸርነትህን ብዛት በዓለሙ ሁሉ ዳርቻ ያስተምሩ ዘንድ የሰደድሃቸው አቤቱ እኛም ለዕድላቸውና ለእርስታቸው የበቃን ታደርገን ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለን።

and did send them to proclaim to all the ends of the world the unsearchable riches of Your grace which is of the mercy: We pray You also and beseech You,

ንሐር በፍናዊሆሙ ወንትሉ በዐሠሮሙ ወጸግወነ በኵሉ ጊዜ ንትመሰል ኪያሆሙ ፤ ወንጽናዕ በፍቅሮሙ ወንኩን ክፍለ ምስሌሆሙ በውስተ ፃማሆሙ በሠናይ አምልኮ።

በመንገዳቸው እንሄድ ዘንድ ፍለጋቸውንም እንከተል ዘንድ ሁልጊዜም እነርሱን እንመስል ዘንድ መምሰሉን ስጠን። በፍቅራቸው እንጸና ዘንድ ባማረ አምልኮ በድካማቸው ከሳቸው ጋራ የታደልን እንሆን ዘንድ መሆኑን ስጠን።

O Lord that You would make us meet for an inheritance and a portion with them that we may walk in their ways and follow in their footsteps: and vouchsafe us at all times to imitate them and to continue in their love and to have fellowship with them in their labour in true godliness.

ወዕቀባ ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት እንተ ሣረርካ በእንቲአሆሙ። ወባርክ ላዕለ አባግዐ መርዔትከ። ወአብዝኃ ለዛቲ ዐፀደ ወይን እንተ ተከልካ በየማንከ ቅዱስ።

ስለነሱ የሠራሃትን ቤተ ክርስቲያንንም ጠብቃት። የመንጋህንም በጎች ባርክ። ጽኑ በሚሆን ቀኝህ የተከልካት ይህችንም የወይን ቦታ (ቀንድ) ባርክ።

And do You keep Your Holy church which You did found by their means and bless the sheep of Your flock and increase the vine which You did plant with Your Holy right hand:

በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ጽንዕ ያለህ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

through Jesus Christ our Lord, through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ንፍቅ ካህን (Asst.Priest)

ነቅዐ ንጹሕ ዘእምአንቅዕተ ሕግ ንጹሐን ዝውእቱ ዜና ግብሮሙ ለሐዋርያት በረከተ ጸሎቶሙ የሀሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

ንጹሐን ከሚሆኑ ከሕግ ምንጮች የተገኘ ጥሩ ምንጭ ይኸውም የሐዋርያት የሥራቸው ነገር ነው። የጸሎታቸው በረከት ከሁላችን ጋራ ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

A pure fountain which is from the pure fountains of the law, to wit the history of the acts of the apostles. The blessing of their prayer be with us all forever. Amen.

የሐዋርያት ሥራ እየተነበበ ነው።

Reading the Acts of the Apostles.

መልዐ ወዐብየ ወተለዓለ ቃለ እግዚአብሔር ወበዝኀ ወተወሰከ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት። ወበዝኁ ሕዝብ እለ አምኑ በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሎቱ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።

የእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ መላ። ከፍ ከፍ አለ። በቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በዝቶ ተጨመረ ፤ ምስጋና ገንዘቡ በሚሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ሕዝብም በዙ፤ ለዘለዓለሙ አሜን።

Full and great and exalted is the Word of God, and it has increased in the Holy church, and many are they that believe in our Lord Jesus Christ to whom be glory, world without end. Amen.

ሕዝብ(People)

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ አምላከ አብ አኃዜ ኵሉ። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ወልድ ዋሕድ ዘአንተ ቃለ አብ ሕያው። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ መንፈስ ቅዱስ ዘተአምር ኵሎ።

ሁሉን የያዝህ አብ ሆይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ። ሕያው የአብ ቃል የምትሆን ወልድ ዋሕድ ሆይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ። ሁሉን የምታውቅ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ።

Holy Holy Holy are You, Father Almighty. Holy Holy Holy are You, only-begotten who are the Word of the living Father. Holy Holy Holy are You, Holy Sprit who knows all things.

ካህን(Priest)

እግዚአብሔር አምላክነ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አቡነ አብርሃም ወህየንተ ይስሐቅ ወልዱ ዘአስተዳሎከ ወአውረድከ ሎቱ ቤዛሁ በግዐ ከማሁ ተወከፍ እግዚኦ መሥዋዕተነ

የአባታችን የአብርሃምን መሥዋዕት የተቀበልክ አምላካችን እግዚአብሔር ስለ ልጁ ስለ ይስሐቅም ፈንታ ቤዛ ሊሆነው በጉን አዘጋጅተህ ያወረድህለት፤

Lord our God, who did accept the sacrifice of our father Abraham, and instead of Isaac his son did prepare and send down to him a ram for his ransom

ወመዓዛ ዝንቱ ዕጣንነ ወፈኑ ለነ ህየንቴሁ እምላዕሉ ብዕለ ሣህልከ ወምሕረትከ ከመ ንኩን ንጹሓነ እምኵሉ ጌና ፂዓተ ኃጣውኢነ።

አቤቱ እንዲሁ መሥዋዕታችንና የዚህን የዕጣናችንን መዓዛ ተቀበል። በርሱም ፈንታ የይቅርታህንና የቸርነትህን ብዛት ከላይ ላክልን። ከክፉ ኃጢአታችን ሽታ ሁሉ ንጹሓን እንሆን ዘንድ።

even so, O Lord, accept our sacrifice and the savior of this our incense, and send unto us from on high in recompense thereof the riches of Your mercy and Your compassion, so that we may become pure from all taint of our sins.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

ወረስየነ ድልዋነ ከመ ንትለአክ ቅድመ ውዳሴ ንጽሕከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ በጽድቅ ወበንጽሕ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትነ በትፍሥሕት ወበኀሤት።

ሰውን የምትወድ ሆይ በንጽሕናህ ምስጋና ፊት እናገለግል ዘንድ የበቃን አድርገን ፤ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በእውነትና በንጽሕና በደስታና በኀሤት።

And make us, O Lover of man, meet to minister before Your glorious purity in righteousness and in purity all the days of our life, in joy and in rejoicing.

**ዲይቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

**ዲያቆን (Deacon)**

ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በኀበ እግዚአብሔር።

ሐዋርያት ስለሰበሰቧት በእግዚአብሔር ዘንድ ስለቀናች ፤ ክብርት ስለምትሆን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጸልዩ።

Pray for the peace of the one Holy apostolic church orthodox in the Lord.

ሕዝብ (*People*)

አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሣሃለነ።

አሜን ኪርያላይሶን ጌታ ሆይ ይቅር በለን።

Amen, Kyrie eleision, Lord have mercy upon us.”

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ በእንተ ሊቀ ጳጳስነ አባ .......ወብፁዕ ጳጳስነ አባ........ ወኵሎሙ ኤጲስ ቆጶሳት ፤ ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ርቱዓነ ሃይማኖት።

ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳችን ስለ አባ .......... ስለ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳችን አባ .........ስለ ኤጲስ ቆጶሳቱም ሁሉ ስለ ቀሳውስትና ስለ ዲያቆናም ፤ ሃይማኖታቸው ስለቀና ስለ ክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ጸልዩ።

Pray for our Patriarch Abba... and for our Archbishop Abba ...... bishops, and all the bishops, priest, deacons and all the all the Orthodox Christians.

ሕዝብ (*People*)

አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሣሃለነ።

አሜን ኪርያላይሶን ጌታ ሆይ ይቅር በለን።

Amen, Kyrie eleison, Lord have mercy upon us.”

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ በእንተ ማኅበርነ ወዕቅበተ ለኵልነ።

ስለ አንድነታችን ለሁላችን መጠበቅ ጸልዩ።

Pray for our congregation and for keeping of us all.

ሕዝብ (*People*)

አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሣሃለነ።

አሜን ኪርያላይሶን ጌታ ሆይ ይቅር በለን።

Amen, Kyrie eleison, Lord have mercy upon us.”

ካህን (Priest)

ተፈሣሒ ኦ ዘንስእለኪ ዳኅና ኦ ቅድስት ምልዕተ ክብር ድንግል።

ደኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተሞላሽ ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O You of whom we ask healing, O Holy full of honor ever Virgin.

## ሕዝብ (People)

ተፈሥሒ።

ደስ ይበልሽ።

Rejoice.

<u>ካህን (Priest)</u>

በኵሉ ጊዜ ወላዲተ አምላክ እሙ ለክርስቶስ አዕርጊ ጸሎተነ ዲበ መልዕልት ኀበ ፍቁር ወልድኪ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ሁልጊዜ ድንግል የምትሆኝ አምላክን የወለድሽ የክርስቶስ እናት ሆይ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ወደ ላይ ጸሎታችንን አሳርጊ።

Ever-Virgin, parent of God, mother of Christ, offer up our prayer on high to Your beloved Son that He may forgive us our sin.

**ሕዝብ (*People*)**

ኣሜን።

Amen.

ካህን (Priest)

ተፈሥሒ ኦ ዘወለድኪ ብርሃነ ጽድቅ ዘበአማን ክርስቶስሃ አምላክነ።

በእውነት የጽድቅ ብርሃን የሚሆን አምላካችንን ክርስቶስን የወለድሽልን ንጽሕት ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O You who did bear for us the very light of righteousness, even Christ our God.

**ሕዝብ (People)**

ተፈሥሒ።

ደስ ይበልሽ።

Rejoice

ካህን (Priest)

ኦ ድንግል ንጽሕት ሰአሊ ለነ ኀበ እግዚእነ ከመ ይግበር ምሕረተ ለነፍሳቲነ ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ንጽሕት ድንግል ሆይ ለነፍሳችን ይቅርታን ያደርግ ዘንድ ፤ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ጌታችን ለምኝልን።

O Virgin pure, plead for us unto our Lord that He may have mercy upon our souls and forgive us our sins.

**ሕዝብ (*People*)**

ኣሜን።

Amen.

ካህን (Priest)

ተፈሥሒ ኦ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ቅድስት ወንጽሕት ሰአሊት በአማን በእንተ ዘመደ እጓለ እምሕያው።

በእውነት ለሰው ወገን አማላጅ የምትሆኚ አምላክን የወለድሽ ንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O Virgin Mary, parent of God, Holy and pure, very pleader for the race of mankind.

**ሕዝብ (People)**

ተፈሥሒ።

ደስ ይበልሽ።

Rejoice

**ካህን (Priest)**

ሰአሊ ለነ ቅድመ ክርስቶስ ወልድኪ ከመ ይጸግወነ ሥርየተ ኃጣውኢነ።

የኃጢያታችንን ሥርየት ይሰጠን ዘንድ በልጅሽ በክርስቶስ ፊት ለምኝልን።

Plead for us before Christ Your Son, that He may vouchsafe us remission of our sins.

**ሕዝብ (*People*)**

ኣሜን ፡፡

Amen

## ካህን (Priest)

ተፈሥሒ ኦ ድንግል ንጽሕት ዘበአማን ንግሥት።

በእውነት ንግሥት የምትሆኝ ንጽሕት ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O Virgin pure, very Queen.

**ሕዝብ (People)**

ተፈሥሒ።

ደስ ይበልሽ።

Rejoice

ካህን (Priest)

ተፈሥሒ ኦ ምክሐ ዘመድነ።

የባሕሪያችን መመኪያ ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O pride of our kind.

**ሕዝብ (People)**

ተፈሥሒ።

ደስ ይበልሽ።

Rejoice

ካህን (Priest)

ተፈሥሒ ኦ ዘወልድኪ ለነ አማኑኤልሃ አምላክነ።

አምላካችን አማኑኤልን የወለድሽልን ሆይ ደስ ይበልሽ።

Rejoice, O You that bare for us Emmanuel our God.

**ሕዝብ (People)**

ተፈሥሒ።

ደስ ይበልሽ።

Rejoice

ካህን (Priest)

ንስእለኪ ከመ ትዘከርነ አራቂተ ዘበአማን ቅድመ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይግበር ምሕረተ ለነፍሳቲነ ወይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እውነተኛ አስታራቂ ሆነሽ ታስቢን ዘንድ እንለምንሻለን ፤ ለነፍሳችን ይቅርታን ያደርግልን ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ።

We ask You to remember us, O true Mediator, before our Lord Jesus Christ that He may have mercy upon our souls and forgive us our sins.

## ካህናት (Priests)

ዝውእቱ ጊዜ ባርኮት ወዝ ውእቱ ጊዜ ዕጣን ኅሩይ ጊዜ ሰብሐቱ ለመድኃኒነ መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ።

የማመስገን ጊዜ ይህ ነው። የተመረጠ የዕጣን ጊዜም ይህ ነው። ሰው ወዳጅ መድኃኒታችንን ክርስቶስን ማመስገኛ ነው።

This is the time of blessing; this is the time of chosen incense, the time of the praise of our Savior, lover of man, Christ.

**ሕዝብ (People)**

ዕጣን ይእቲ ማርያም ፤ ዕጣን ውእቱ እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሜዐዝ እምኵሉ ዕጣን ዘወለደቶ መጽአ ወአድኀነነ።

ማርያም ዕጣን ናት። ዕጣን እርሱ ነው ፤ በማኅጸንዋ ያደረው ከተመረጠ ዕጣን ሁሉ የሚሸት ነውና። የወለደችው መጥቶ አዳነን።

Mary is the incense, and the incense is He, because He who was in her womb is more fragrant than all chosen incense. He whom she bare came and saved us.

## ካህናት (Priests)

ዕፍረት ምዑዝ ኢየሱስ ክርስቶስ ንዑ ንስግድ ሎቱ ወንዕቀብ ትእዛዛቲሁ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ያለው ሽቱ ነው። ኑ እንስገድለት ፤ ትእዛዞቹንም እንጠብቅ ፤ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

The fragrant ointment is Jesus Chris. O come let us worship Him and keep His commandments that He may forgive us our sins.

**ሕዝብ (People)**

ተውህበ ምሕረት ለሚካኤል ፤ ወብሥራት ለገብርኤል ፤ ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል።

ለሚካኤል ምሕረት ተሰጠው። ለገብርኤልም ማብሠር ፤ ለድንግል ማርያምም ወደ መንግሥተ ሰማያት የምትገባበት ሀብት ተሰጣት።

To Michael was given mercy, and glad tidings to Gabriel, and a heavenly gift to the Virgin Mary.

## ካህናት (Priests)

ተውህበ ልቡና ለዳዊት ፤ ወጥበብ ለሰሎሞን ፤ ወቀርነ ቅብዕ ለሳሙኤል እስመ ውእቱ ዘይቀብዕ ነገሥተ።

ለዳዊት ልቡና ፤ ለሰሎሞን ጥበብ ፤ ለሳሙኤልም ነገሥታቱን የቀባ እርሱ ነውና የሽቱ ቀንድ ተሰጠው።

To David was given understanding, and wisdom to Solomon, and an horn of oil to Samuel for he was the anointer of kings.

ሕዝብ (People)

ተውህቦ መራኁት ለአቡነ ጴጥሮስ ፤ ወድንግልና ለዮሐንስ ፤ ወመልእክት ለአቡነ ጳውሎስ እስመ ውእቱ ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን።

ለአባታችን ለጴጥሮስ መክፈቻ ፤ ለዮሐንስም ድንግልና ፤ ለአባታችን ለጳውሎስም የቤተ ክርስቲያን ብርሃኗ እርሱ ነውና መልእክት ተሰጠው።

To our father Peter were given the keys, and virginity to John, and apostleship to our father Paul, for he was the light of the church.

## ካህናት (Priests)

ዕፍረት ምዕዝት ይእቲ ማርያም ፤ እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሌዐል እምኵሉ ዕጣን መጽአ ወተሠገወ እምኔሃ።

መዓዛ ያላት ሽቱ ማርያም ናት። በማኅጸንዋ ያለው ከዕጣን ሁሉ የሚበልጥ ነውና መጥቶ ከእርስዋ ሰው ሆነ።

The fragrant ointment is Mary, for He that was in Her womb, who is more fragrant than all incense, came and was incarnate of her.

ሕዝብ (People)

ለማርያም ድንግል ንጽሕት ሠምራ ፤ አብ ወአሠርገዋ ደብተራ ለማኅደረ ፍቁር ወልዱ።

ንጽሕት ድንግል ማርያምን አብ ወደዳት ፤ ለተወደደ ልጁ ማደሪያ ልትሆን በንጽሕና አስጌጣት።

In Mary virgin pure the Father was well-pleased, and He decked her to be a tabernacle for the habitation of his beloved Son.

## ካህናት (Priests)

**ተውህበ ሕግ ለሙሴ ፤ ወክህነት ለአሮን ፤ ተውህበ ዕጣን ኅሩይ ለዘካርያስ ካህን።**

ለሙሴ ሕግ ፤ ለአሮን ክህነት ተሰጠው ፤ ለካህኑ ዘካርያስም የተመረጠ ዕጣን ተሰጠው።

To Moses was given the law, and priesthood to Aaron. To Zacharias the priest was given chosen incense.

**ሕዝብ (People)**

ደብተራ ስምዐ ገብርዋ። በከመ ነገረ እግዚእ ወአሮን ካህን በማእከላ የዐርግ ዕጣነ ኅሩየ።

የምስክር ድንኳን አደረጓት። ጌታ እንደ ተናገረ ካህኑ አሮን በመካከሏ የተመረጠውን ዕጣን ያሳርጋል።

They made a tabernacle of testimony according to the word of God; and Aaron the priest, in the midst thereof made the chosen incense to go up.

## ካህናት (Priests)

ሱራፌል ይሰግዱ ሎቱ ፤ ወኪሩቤል ይሴብሕዎ ይጸርሑ እንዘ ይብሉ።

ሱራፌል ይሰግዱለታል ፤ ኪሩቤልም ያመሰግኑታል። እንዲህም እያሉ እየጠሩት።

The Seraphim worship Him, and Cherubim praise Him and cry saying:

**ሕዝብ (People)**

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በኀበ አእላፍ ወክቡር በውስተ ረበዋት። አንተ ውእቱ ዕጣን ኦ መድኃኒነ እስመ መጻእከ ወአድኃንከነ ተሣሃለነ።

እግዚአብሔር በአእላፍ መላእክት ዘንድ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነው እያሉ ይጮሃሉ። በአለቆችም ዘንድ ክቡር ነው። መድኃኒታችን ሆይ ዕጣን አንተ ነህ መጥተህ አድነኸናልና ፤ ይቅር በለን።

Holy Holy Holy is the Lord among the thousands and honored among the tens of thousands. You are the incense, O our savior, for You did come and save us. Have mercy upon us.

**ካህን (Priest)**

**ቅዱስ።**

Holy

ሕዝብ (People)

እግዚአብሔር ፤ ቅዱስ ኃያል ፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ፤ ዘተወልደ እምማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት ፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ ፤ አቤቱ ይቅር በለን።

God, Holy Mighty, Holy Living Immortal, who was born from the Holy Virgin Mary, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ፤ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ ተሣሃለ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት ፤ በዮርዳኖስ የተጠመቀ ፤ በቅዱስ መስቀል ላይ የተሰቀለ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, Holy Mighty, Holy Living, Immortal, who was baptized in Jordan and crucified on the tree of the cross, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ።

Holy God, Holy Mighty, Holy Living Immortal, who did rise from the dead on the third day,

ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ፤ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ፤ ተሣሃለነ እግዚኦ።

በምስጋና ወደ ሰማይ ወጣ ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ፤ ዳግመኛም በክብር ይመጣል ፤ በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ አቤቱ ይቅር በለን።

ascend into heaven in glory, sit at the right hand of the Father and again wilt come in glory to judge the quick and the dead, have mercy upon us, Lord.

ስብሐት ለአብ ፤ ስብሐት ለወልድ ፤ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

ለአብ ምስጋና ይሁን ፤ ለወልድም ምስጋና ይሁን ፤ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ፤ አሜን ይሁን ይሁን።

Glory be to the Father, glory be to the Son, glory be to the Holy Spirit, both now and ever and world without end. Amen and Amen, so be it, so be it.

**ሕዝብ (People)**

ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ሕያው ተሣሃለነ።

ልዩ ሦስት ሕያው እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለን።

O Holy Trinity, living God have mercy upon us.

## ካህን (Priest)

ፀጋ ዘእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌክሙ።

የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋራ ይሁን።

The grace of God be with you.

## ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

**ካህን (Priest)**

ንሰብሖ ለአምላክነ።

ፈጣሪያችንን እናመስግን።

Let us glory our God.

***ሕዝብ (People)***

ርቱዕ ይደሉ።

እውነት ነው ይገባል።

It is right, it is just.

## ካህን (Priest)

አጽንዑ ሐሊና ልብክሙ።

የልባችሁን አሳብ አጽኑ።

Strengthen the thought of your heart.

## ሕዝብ (*People*)

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት አቡነ ዘበሰማያት ፤ አቡነ ዘበሰማያት ፤ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

ከእግዚአብሔር ዘንድ አለን። አባታችን ሆይ ፤ አባታችን ሆይ ፤ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

We lift them unto the Lord our God. Our Father who are in heaven, Our Father who are in heaven, Our Father who are in heaven, lead us not into temptation.

ሕዝብ (People) ጧት (in the morning)

ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ።

አቤቱ አንተን እናመሰግንሃለን።

Oh, we thank You.

ሕዝብ (People) ከሰዓት በኋላ (in the afternoon)

ንሴብሐከ እግዚኦ።

አቤቱ እናመሰግንሃለን።

Oh, we thank You.

**ሕዝብ (People)**

ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ። ጧት (in the morning)

አቤቱ አንተን እናገንሃለን።

Oh Lord, we praise You.

**ሕዝብ (People)** ከሰዓት በኋላ (in the afternoon)

ንዌድሰከ እግዚኦ።

አቤቱ እናገንሃለን።

Oh Lord, we praise You.

ካህን (Priest) ጧዋት (in the morning)

….እስመ ለከ እግዚአ አምላክነ መንግሥት ቡሩክ።

….አቤቱ አምላካችን ክቡር መንግሥት ያትንተ ነውና።

….for Yours is the blessed kingdom, O Lord our God.

ካህን (Priest) ከሰዓት በኋላ (in the afternoon)

……በእንቲአከ ወበእንተ ፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ዘቦቱ ለከ ስብሐት ወእኂዝ ለዓለመ ዓለም።

……ልጅህ ወዳጅህ ጌታችን ኢየሱስም ስለገለጸልን ምስጋና ጽንዕ ያለው ለዘላለሙ።

…..Your beloved Son, our Lord Jesus, through whom be glory and dominion to You, world without end.

**ሕዝብ (*People*)**

ኣሜን

Amen

# ቡራኬ

# Benediction

ሕዝብ (People)

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ። ትምጻእ መንግሥትከ። ወይኩን ፈቃድከ። በከመ በሰማይ ፤ ከማሁ በምድር።

አባታችን ሆይ ፤ በሰማያት የምትኖር ፤ ስምህ ይቀደስ ፤ መንግሥትህ ትምጣ። ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን።

Our Father who are in heaven, hallowed be Your name, Your kingdom come, Your will be done on earth as it is in heaven;

ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም። ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ፤ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ።

የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ። በደላችንን ይቅር በለን ፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል።

give us this day our daily bread, and forgive us our trespasses as we forgive them that trespass against us,

ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ፤ አላ አድኅነነ። ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ። እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።

አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ፤ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ። መንግሥት ያንተ ናትና ኃይል ክብር ምስጋናም ለዘላለሙ አሜን።

and lead us not into temptation but deliver us and rescue us from all evil; for Yours is the kingdom, the power and the glory for ever and ever.

በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዚእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በሕሊናኪ ፣ ኦ ድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን። በኃሳብሽ ድንግል ነሽ። በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናቱ ሆይ ሰላምታ ለአንቺ ይገባሻል።

Our Lady, Virgin St. Mary! In St. Gabriel's greetings, peace be unto you. You are Virgin in thought and Virgin in body, O mother of the almighty God! Peace be unto You.

ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ። ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ።

ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ። የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበለሽ ፤ ልዑል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና።

Blessed are You amongst women and blessed is the fruit of Your womb. Hail Mary, full of Grace, the Lord is with You,

ሰአሊ ወጸልዩ በእንቲአነ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ አሜን።

ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታንና ምሕረትን ለምኚልን ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ ለዘለዓለሙ አሜን።

Beseech and pray for us for our mercy to Your beloved Son our Lord Jesus Christ that He may forgive us our sins. Amen.

## ሕዝብ (People)

ኦ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ።
ኦ ሥሉስ ቅዱስ መሐከነ።
ኦ ሥሉስ ቅዱስ ተሣሀለነ።

ልዩ ሦስት ሆይ ማረን ።
ልዩ ሦስት ሆይ ራራልን።
ልዩ ሦስት ሆይ ይቅር በለን።

O Holy Trinity, Pity us,
O Holy Trinity, Spare us,
O Holy Trinity, have mercy upon us.

## ካህን (Priest)

ቦአ መልአክ ኀቤሃ ወቆመ ቅድሜሃ ወይቤላ ለድንግል ተፈሥሒ ተፈሥሒ ተፈሥሒ ኦ ማርያም ድንግል ምልዕተ ጸጋ ።

መልአክ ወደርሷ ገብቶ ፤ በፊቷ ቆሞ ፤ ድንግልን ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ፤ ደስ ይበልሽ፤ ደስ ይበልሽ አላት።

The angel went in unto Her and stood in front of Her and said to Virgin : Rejoice, rejoice, rejoice, You that are full of grace.

**ሕዝብ (People)**

እግዚአብሔር ምስሌኪ።

እግዚአብሔር ካንቺ ጋራ ነው።

The Lord is with You.

ካህን (Priest)

ቡርክት አንቲ እም አንስት።

ከሴቶች ሁሉ የተባረክሽ ነሽ።

Blessed are You among women:

ሕዝብ (People)

ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ።

የማኅጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።

And blessed is the fruit of Your womb.

**ካህን (Priest)**

ተንብለ ወሰአለ።

ለምኝልን አማልጂንም።

Pray for us

**ሕዝብ (People)**

ኀበ ፍቁር ወልድኪ።

ከተወደደው ከልጅሽ ዘንድ።

To Your Son.

**ካህን (Priest)**

ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ

Jesus Christ

**ሕዝብ (People)**

ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

To forgive us our sins.

ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ። ይደልዎሙ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ። አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኵሉ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም።

ልዩ ሦስት ለሚሆን ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ሁልጊዜ ክብር ምስጋና ይገባቸዋል ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ ፤ አሜን።

Glory and honor are meet to the Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit at all times, both now and ever and world without end. Amen

**ዲያቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነ ዘትቤሎሙ ለአርዳኢከ ቅዱሳን ወለሐዋርያቲከ ንጹሓን። እስመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን ፈተዉ ይርአዩ ፤

አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀመዛሙርትህንና ንጹሐን ሐዋርያትን እንዲህ ያልሃቸው "እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙ ነቢያት ፤ ጻድቃን ወደዱ ፤

O Lord Jesus Christ, our God, who did say to Your Holy disciples and Your pure apostles: Many prophets and righteous men have desired to see the things which You see

አንትሙ ዘትሬእዩ ወኢርእዩ ፤ ወፈተዉ ይስምዑ አንትሙ ዘትሰምዑ ወኢሰምዑ። ወለክሙሰ ብፁዓት አይንቲክሙ እለ ርእያ ወአእዛኒክሙ እለ ሰምዓ።

አላዩም። እናንተ ዛሬ የምትሰሙትን ይሰሙ ዘንድ ወደዱ ፤ አልሰሙም። የእናንተ ያዩ ዓይኖቻችሁና የሰሙ ጆሮቻችሁ ግን የተመሰገኑ ናቸው።

and have desired to hear the things which you hear and have not heard them, but you, blessed are your eyes that have seen and your ears that have heard,

ወከማሆሙ ለነኒ ረስየነ ድልዋነ ንስማዕ ወንግበር ቃለ ወንጌልከ ቅዱስ በጸሎቶሙ ለቅዱሳን።

እኛንም እንደነሱ የበቃን አድርገን። በቅዱሳን ጸሎት የከበረ ወንጌልን ሰምተን እንሠራ ዘንድ።

Do you make us also like them meet to hear and to do the word of Your Holy Gospel through the prayer of the saints.

**ዲያቆን (Deacon)**

ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ።

ክቡር ስለሚሆን ስለ ወንጌል ጸልዩ።

Pray for the Holy Gospel.

**ሕዝብ (People)**

ይረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱስ።

ቅዱስ ወንጌልን ለመስማት የበቃን ያድርገን።

May He make us meet to hear the Holy Gospel.

ካህን (Priest)

ተዘከር ካዕበ እግዚኦ እለ አውሥኡነ ከመ ንዘከሮሙ ጊዜ ጸሎትነ ወአስተበቍዖትነ እንተ ነኀሥሥ እምኀቤከ።

ዳግመኛ አቤቱ ካንተ ዘንድ የምንሻውን በምንለምንበትና በምንጸልይበት ጊዜ እናስባቸው ዘንድ አስቡን ያሉትን ዳግመኛ አስብ።

Remember again, Lord them that have bidden us to remember them at the time of our prayers and supplications where with we make request of You.

ኦ እግዚአብሔር አምላክነ ለእለ ቀደሙነ ነዊመ አዕርፎሙ ወለዱያንሂ ፍጡነ ፈውሶሙ።

አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ከኛ አስቀድመው የሞቱትን አሳርፋቸው ፤ የታመሙትንም ፈጥነህ አድናቸው።

O Lord our God, give rest to them that have fallen asleep before us, heal speedily them that are sick,

እስመ አንተ ውእቱ ሕይወተ ኵልነ ፤ ወተስፋ ኵልነ ፤ ወባላሔ ኵልነ ፤ ወመንሥኤ ኵልነ ፤ ወለከ ንፌኑ አኰቴተ እስከ አርያም ለዓለመ ዓለም።

የሁላችን ሕይወት ፣ የሁላችን ተስፋ ፣ የሁላችን አዳኝ ፣ የሁላችንም አስነሽ አንተ ነህና። ላንተ ምስጋናን እስከ አርያም ድረስ እንልካለን።

for You are the life of us all, the hope of us all, the deliverer of us all and the raiser of us all, and to You we lift up thanksgiving unto the highest heaven, world without end.

# ምስባክ


ሀቡ አኰቴተ ለእግዚአብሔር።
ሐወጽከኒ ሌሊተ ወፈተንኮ ለልብየ።
ሐወጽካ ለምድር ወአርወይካ።
ለነዳያኒሃኒ አጸግቦሙ እክለ።
ልበ ንጹሐ ፍጥር ሊተ እግዚኦ።
መሐለ እግዚአብሔር ወኢይኔስሕ
መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን።
ምድርኒ ትሁብ ፍሬሃ
ሠረገላቲሁ ለእግዚአብሔር ምዕልፊተ አዕላፍ ፍሡሓን።
ሣህሉ ለእግዚአብሔር መልዐ ምድረ።
ሣህል ወርትዕ ተራከባ።
ስሚዒ ወለትየ ወርእዩ ወእጽምዒ እዝነኪ፡፡
ሶበ ትሬእዮሙ ለጠቢባን ይመውቱ
ርእዩከ ማያት እግዚኦ።
ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል
ቃለ ወሀቡ ደመናት አሕፃከ ይወፅኡ።
ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ።
በልዑ ወጸግቡ ጥቀ።
በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ
ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር።
ብፁዕ ብእሲ ዘአንተ ገሠጽኮ እግዚኦ
ተቀነዩ ለእግዚአብሔር
ተዘከር ማኅበረከ ዘአቅደምከ ፈጢረ
ተዘከር እግዚኦ ከመ መሬት ንሕነ።
ተፅዕነ ላዕለ ኪሩቤል ወሠረረ
ተፈሣሕኩ እስመ ይቤሉኒ እግዚአብሔር ነሐውር።
ተፈሣሕኩ እስመ ይቤሉኒ
ታቦር ወአርሞንኤም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ።
ትሴብሖ ኢየሩሳሌም ለእግዚአብሔር።
ነገሥተ ተርሴስ
ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ።
ንፍሑ ቀርነ በዕለተ ሠርቅ።
ኖላዊሆሙ ለእሥራኤል አጽምዕ
አርውዮ ለትለሚሃ።
ዐርገ እግዚአብሔር በይባቤ።
አንሰ ሰከብኩ ወኖምኩ።
አንተ ፈጠርከ ፀሐየ ወወርኀ።
አንተሰ እግዚእ መሐሪ ወመስተ ሣህል።
አግረረ ለነ አሕዛበ ወሕዝበ ታሕተ እገሪነ።
ዐፀደ ወይን አፍለስከ እምግብፅ።
አፉሁ ለጻድቅ ይትሜሀር ጥበበ
ኢትዝክር ብነ አበሳነ ዘትካት።
ኢትግፈኒ እምቅድመ ገጽከ።
ዓይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ
እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ ዐረብ።
እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ።
እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ።
እስመ ሐረያ እግዚአብሔር
እስመ ኀቤከ እጼሊ እግዚኦ
እስመ መምህረ ሕግ ይሁብ በረከተ።
እስመ ሰበረ ኖኃተ ብርት።
እስመ ቅንዐተ ቤትከ በልዐኒ።
እስመ በእንቲአሁ ይቀትሉነ ኵሎ አሚረ
እስመ ፈተወ ንጉሥ ስነኪ።
እበውእ ቤተከ ምስለ መባእየ
እግዚአብሔር ስቡሕ በምክረ ቅዱሳን።
እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ።
እግዚአብሔር ይረድኦ ውስተ ዐራተ ሕማሙ።
እግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገበረ።
እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም።
እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ።
እግዚኦ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ
እግዚኦ ኰነኔከ ሀቦ ለንጉሥ
ዖፍኒ ረከበት ላቲ ቤተ።
ከመ እንግር ፈቀደከ መከርኵ አምላኪየ።
ኵሎ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር።
ወሐመልማለ ለቅኔ ዕጓለ እመሕያው።
ወሳሙኤልኒ ምስስ እከ ይጼውዑ ስሞ
ወበመንፈስ አዚዝ አጽንዐኒ።
ወተንሥአ፡እግዚአብሔር ከመ ዘንቃህ፡እምንዋም።
ወትሰይመኒ ውስተ ርእሰ ሕዝብ።
ወትቀውም ንግሥት በየማንከ።
ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ
ወአነሂ በኩርየ እሬስዮ።
ወአጽንዖ እግዚኦ ለዝንቱ ዘሠራዕከ ለነ
ወእነግር ስምዐከ በቅድመ ነገሥት ወኢትይኀፈር
ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ።)
ወይሰግዳ ሎቱ አዋልደ ጢሮስ በአምኃ
ወይከውን ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ኀበ ሙሐዘ ማይ።
ወይወስዱ ለንጉሥ ደናግለ ድኅሬሃ
ወድቀት እሳት ወኢርኢክዋ ለፀሐይ
ውስተ ኵሉ ምድር ወፅአ ነገሮሙ
ዘምሩ ለእግዚአብሔር ዘየኀድር ውስተ ጽዮን።
ዘአዘዝከ መድኀኒቶ ለያዕቆ
ዘያበቍል ሣዕረ ለእንሰሳ።
ዘይሁብ ሲሳየ ለኵሉ ዘሥጋ።
ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና።
ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር።
የሐዩ ወይሁብዎ እምወርቅ ዐረብ።
የዐርግ ደመናተ እምአጽናፈ ምድር
ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረዉ ፀሩ።
ይትዓየን መልአከ እግዚአብሔር ዐውዶሙ
ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር።
አልቦ ነገር ወአልቦ ነቢብ ዘኢተሰምዐ ቃሎሙ።
ዐረገ ውስተ አርያም ፄዊወከ ፄዋ
ከነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር
ደቂቀ እጓለ እመሕያው
ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ።
ግበሩ በዓለ በትሥፍሕት በኀበ እለያተሐምምዎ።
ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ
ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ።
ፈኑ እዴከ እምዓርያም።
ፍሬ ፃማከ ተሴሰይ።

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ልዑል ይባርክ ላዕለ ኵልነ። ወይቀድሰነ በኵሉ በረከት መንፈሳዊት። ወይረሲ በአተነ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት።

ልዑል እግዚአብሔር ሁላችንን ይባርክ ፤ በመንፈሳዊም በረከት ሁሉ ያክብረን። ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መግባታችንንም።

O God, most high, bless us all and sanctify us with every spiritual blessing, and bring us into the Holy church

ኅቡረ ምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን እለ ይትቀነዩ ሎቱ በፍርሀት ወበረዓድ ወትረ ወይሴብሕዎ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም። አሜን።

ዘወትር በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከሚያገለግሉት ቅዱሳን መላእክት ጋራ በአንድነት ያድርግ። በየጊዜውና በየሰዓቱም ሁሉ ከሚያመሰግኑት ከቅዱሳን መላእክት ጋራ አንድነት ያድርግ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ። አሜን

to be joined with His Holy angels who serve Him always in fear and trembling, and glorify Him at all times and all hours, both now and ever and world without end. Amen.

ካህን/priest

እግዚአብሔር አምላክነ ወመድኃኒነ ወመፍቀሬ ሰብእ አንተ ውእቱ ዘፈነውኮሙ ለአርዳኢከ ቅዱሳን ወለላእካኒከ ወለሐዋርያቲከ ንጹሓን ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም።

አምላካችንና መድኃታችን ሰውንም የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና አገልጋዮችህን ንጹሓን ሐዋርያትን ወደ ዓለም ሁሉ ዳርቻ የሰደድሃቸው አንተ ነህ።

Lord our God and our Saviour and lover of man, You are He who did send Your Holy disciples and ministers, and Your pure apostles unto all the ends of the world

ከመ ይስብኩ ወይምህሩ ወንጌለ መንግሥትከ ወይፈውሱ ኵሎ ደዌ ወኵሎ ሕማመ ዘውስተ ኵሉ ሕዝብከ ወይዜንዉ ምሥጢረከ ኅቡአ ዘእምቅድመ ዓለም።

የመንግሥትህን ወንጌል ይሰብኩና ያስተምሩ ዘንድ በሕዝብህ ውስጥ ያለውን ደዌውን ሁሉ በሽታውንም ሁሉ ያድኑ ዘንድ ከዓለም አስቀድሞ የነበረውን የተሰወረውን ምሥጢርህንም ያስተምሩ ዘንድ።

to preach and teach the gospel of Your kingdom, and to heal all the diseases and all the sicknesses which are among Your people, and to proclaim the mystery hidden from before the beginning of the world.

ወይእዜኒ እግዚእነ ወአምላክነ ፈኑ ላዕሌነ ብርሃነከ ወጽድቀከ ወአብርህ አዕይንተ አልባቢነ ወሕሊናነ ወረስየነ ድልዋነ ንስማዕ በጥብዓት ቃለ ወንጌልከ ቅዱስ።

አሁንም ጌታችን አምላካችን ሆይ ብርሃንህንና ጽድቅህን ላክልን ያሳባችንና የልቦናችንን ዓይኖች አብራልን። የከበረ የወንጌልን ቃል በመጨከን እንሰማ ዘንድ የበቃን አድርገን።

Now also, our Lord and our God, send upon us Your light and Your righteousness, and enlighten the eyes of our hearts and of our understanding; make us meet to persevere in hearing the word of Your Holy gospel,

አኮ ዘንሰምዕ ባሕቲቱ አላ ንግበር በከመ ሰማዕነ ከመ ይፍረይ ላዕሌነ ፍሬ ሠናየ ህየንተ ፩ ፴ ወ፷ ወ፻ ከመትሥረይ አበሳነ ለሕዝብከ ወንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት።

የምንሰማ ብቻ አይደለም እንደሰማን ልንሠራ ነው እንጂ ስለ አንዱ ፈንታ ሠላሳና ስድሳ መቶም ያማረ ፍሬ በላያችን ያፈራ ዘንድ የወገኖችህን ኃጢአት ታስተሠርይ ዘንድ ለመንግሥተ ሰማያትም የበቃን እንሆን ዘንድ።

and not only to hear but to do according to what we hear, so that is may hear good fruit in us, remaining not one only but increasing thirty, sixty, and a hundredfold; and forgive us our sins, us Your people, so that we maybe worthy of the kingdom of heaven.

## ካህን (Priest)

ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ።

ሁሉን የያዘ እግዚአብሔር አብ ብሩክ ነው።

Blessed be God Almighty Father.

## ካህን ንፍቅ (*Assistant priest*)

አእኵትዎ ለአብ።

አብን አመስግኑት።

Give thanks unto the Father.

**ካህን (Priest)**

**ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።**

**ወልድ ዋሕድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቡሩክ ነው።**

And blessed be the only-begotten Son our Lord Jesus Christ.

**ካህን ንፍቅ (*Assistant priest*)**

**አእኵትዎ ለወልድ።**

**ወልድን አመስግኑት።**

Give thanks unto Son.

**ካህን (Priest)**

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ።

አጽናኝ መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው።

And blessed be the Holy Spirit Paraclete.

**ካህን ንፍቅ (*Assistant priest*)**

አእኵትዎ ለመንፈስ ቅዱስ።

መንፈስ ቅዱስን አመስግኑት።

Give thanks unto Holy Spirit.

ዲያቆን (Deacon)

ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ወንጌለ ቅዱሰ ዜናሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ሃሌ ሉያ ጌታችንና መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱስ ወንጌል ቆማችሁ አድምጡ።

Halleluiah, stand up and hear to the Holy Gospel, the message of our Lord and Savior Jesus Christ.

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ።

እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን።

The Lord be with you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with your Spirit.

ካህን (Priest)

ወንጌል ቅዱስ ፤ ዘዜነወ ማቴዎስ / ማርቆስ / ሉቃስ (ዘሰበከ ዮሐንስ) ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

(ማቴዎስ / ማርቆስ / ሉቃስ ) የተናገረው (ዮሐንስ የሰበከው) የእግዚአብሔር ልጅ ቃል የሚሆን ቅዱስ ወንጌል ይህ ነው።

The Holy gospel which as Matthew / Mark / Luke have proclaimed, (John preached) the Word of the Son of God.

**ሕዝብ (People)**

ስብሐት ለከ ክርስቶስ እግዚእየ ወአምላኪየ ኵሎ ጊዜ።

ጌታዬና አምላኬ ክርስቶስ ሆይ ሁልጊዜ ለአንተ ምስጋና ይገባል።

Glory be to You, Christ my Lord and my God, at all times.

❖ የጾም ወቅት ከሆነ ወደሚቀጥለው ገጽ ተሻገር።
For fasting season, go to the next page

ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ ወየብቡ ለአምላከ ያዕቆብ ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ ከበሮ መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ።

በረዳን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ። የያቆብንም አምላክ አመስግኑ። መዝሙሩን ያዙ ፤ ከበሮውንም ስጡ ፤ ከበገና ጋራ የተስማማ ነው።

Sing aloud unto God our strength: make a joyful noise unto the God of Jacob. Take a psalm, and bring hither the timbrel, the pleasant harp with the psaltery.

## በጾም ጊዜ በ“ተፈስሐ” ፈንታ / replacement of “Sing aloud”

### ሕዝብ (People)

በወንጌል መራህከነ ፤ ወበነቢያት ናዘዝከነ ፤ ዘለሊከ አቅረብከነ ስብሐት ለከ።

በወንጌል መራኸን ፤ በነቢያትም አጸናኸን ፤ ለአቀረብኸን ክብር ምስጋና ይገባል።

You have guided us with the Gospel, comforted us with the prophets, and drawn us nigh unto You. Glory be to You.

**ካህን (Priest)**

ነዋ ወንጌለ መንግሥተ ሰማያት።

ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታገባ ወንጌል እነሆ።

Behold the Gospel of the kingdom of heaven.

***ንፍቅ ካህን (Ass't Priest)***

መንግሥቶ ወጽድቆ ዘአወፈየኒ አወፈይኩከ።

መንግሥቱንና ጽድቁን የሰጠኝን ሰጠሁህ።

His kingdom and His righteousness which He delivered to me: I deliver to you.

ዲያቆን (Deacon)

ነስሐ እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት።

መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ።

For the kingdom of heaven is at hand.

## የማቴዎስ ፥ ማርቆስና ሉቃስ ወንጌል ሲነበብ
## When reading from Matthew, Mark and Luke

ካህን (Priest)

ባርክ እግዚኦ ነገረ ዘእምወንጌለ .... ረድኡ ወሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ሎቱ

የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያውና ደቀ መዝሙሩ ከሚሆን ... ወንጌል የተገኘውን

Bless, O Lord, the portion of the gospel of .... The disciple and apostle of our Lord Jesus Christ the Son of

ስብሐት ወትረ እስከ ለዓለም ዓለም አሜን።

ቃል አቤቱ ባርክ። ምስጋና ዘወትር ገንዘቡ ነው ለዘለዓለሙ አሜን።

the living God ; to Him be glory continually, and unto the ages of ages. Amen.

## ዮሐንስ ወንጌል ሲነበብ - When reading from John


ካህን/priest

ዝ ቃል ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለክብረ መንግሥቱ ስብሐት እስከ ለዓለም።

ለመንግሥቱ እስከ ዘላለም ምስጋና ይግባውና ይህ ቃል የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

This is the word of our Lord and our God and our Saviour Jesus Christ for the honor of His kingdom,

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service



## የማቴዎስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from Mathew)

**ካህን/priest**

ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ ይቤ እግዚእ ለአርዳኢሁ።

ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም አለ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ።

Heaven and earth shall pass away, but My Words, shall not pass away, said the Lord to his disciple.

## የማቴዎስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from Mathew)

### ሕዝብ (People)

ነአምን አበ ዘበአማን ፤ ወነአምን ወልደ ዘበአማን ፤ ወነአምን መንፈሰ ቅዱሰ ዘበአማን ህልወ ሥላሴሆሙ ነአምን።

አብን በእውነት እናምናለን። ወልድንም በእውነት እናምናለን ። መንፈስ ቅዱስንም በእውነት እናምናለን። የማይለወጥ ሦስትነታቸውንም በእውነት እናምናለን።

We believe in the very Father, we believe in the very Son, and we believe in the very Holy spirit, we believe in their unchangeable Trinity.

## የማርቆስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from Mark)

ካህን/priest/

ዘቦ እዝን ሰሚዐ ለይስማዕ።

ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ።

He that has ears to hear, let him hear.

## የማርቆስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from Mark)

### ሕዝብ (People)

እሉ ኪሩቤል ወሱራፌል ያዐርጉ ሎቱ ስብሐተ እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

እሊህ ኪሩቤልና ሱራፌል ፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ እግዚአብሔር ነህ እያሉ ምስጋናን ያቀርቡለታል ።

Those cherubim and seraphim offer to Him glory saying; Holy Holy Holy You are God, Father, Son and the Holy Spirit.

## የሉቃስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from Luke)

### ካህን (Priest)

ይቀልል ኀልፈተ ሰማይ ወምድር እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእምነቢያት።

ከኦሪትና ከነቢያት አንዲቱ ቃል ከምትወድቅ የሰማይና የምድር ማለፍ ይቀላል።

It is easier for heaven and earth to pass, than one little of the Law to fall.

## የሉቃስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from Luke)

### ሕዝብ (People)

መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚኦ አንተ ውእቱ ዘትገብር መንክረ አርአይኮሙ ለሕዝብከ ኃይለከ ወአድኀንኮሙ ለሕዝብከ

አቤቱ ከአማልክት ወገን የሚመስልህ ማነው? ተአምራትን የምታደርግ አንተ ነህ። ለወገኖችህ ኃይልህን አሳየሃቸው።

Who is like unto You, O lord, among the gods? You are the God that does wonders: You have declared your strength among the people. You have with Your arm redeemed the people.

በመዝራዕትከ። ሖርከ ውስተ ሲኦል ወአዕረገ ፄዋ እምህየ ወጸጎከነ ምዕረ ዳግመ ግዕዛነ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ በእንተ ዝንቱ ንሴብሐከ ወንጸርሕ ኀቤከ እንዘ ንብል

ወገኖችህንም በክንድህ አዳንካቸው። ወደ ሲኦል ሄደህ ከዚያ ምርኮን አወጣህ። ዳግመኛም አንድ ጊዜ ነጻነትን ሰጠኸን። መጥተህ አድነኸናልና ስለዚህ እናመሰግንሃለን።

You did go into Hades and the Captives rose up from there, and thou did grant us again to be set free, for You did come and save us. For this cause we glorify You and cry unto You saying,

ቡሩክ አንተ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ።

አቤቱ ኢየሱስ ሆይ ቡሩክ ነህ እያልን እንጮኻለን ፤ መጥተህ አድነኸናልና።

Blessed are You, Lord Jesus Christ, for You did come and save us.

## የዮሐንስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from John)

### ካህን (priest)

ዘየአምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም።

በወልድ ያመነ የዘላለም ሕይወት አለው።

He that believes on the Son has everlasting life.

## የዮሐንስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ (After Reading from John)

### ሕዝብ (People)

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ ፩ዱ ዋሕድ ለአቡሁ።

ቃል በቅድምና ነበር። ይህ ቃል የእግዚአብሔር አብ ቃል ነው። ያ ቃል ሥጋ ሆነ ፤ በእኛም አደረ። ለአባቱ አንደ አንድ ልጅ የሚሆን ክብሩንም አየን።

In the beginning was the Word, the Word was the Word of God: The Word was made flesh, and dwelt among us, and we beheld His glory, the glory as of the only begotten of the Father,

ቃለ አብ ሕያው ወቃል ማሕየዊ ቃለ እግዚአብሔር ተንሥአ ወሥጋሁኒ ኢማሰነ።

የሕያው የአብ ቃል ነው። ያ ቃልም መድኃኒት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ተነሣ። ሥጋውም አልጠፋም።

the Word of the living Father, and the life-giving Word, the Word of God, rose again and His flesh was not corrupted.

ካህን(Priest)

ስብሐት ለከ እግዚአብሔር አምላክነ አኃዜ ኵሉ ዘረሰይከነ ድልዋነ ንስማዕ ቃለ ወንጌልከ ቅዱስ ወከመ ነአምኖ ወንትፈሣሕ ቦቱ።

ክቡር የሚሆን የወንጌልን ቃል እንሰማ ዘንድ ፤ እንሳለመውም ዘንድ ፤ በርሱም ደስ ይለን ዘንድ ለዚህ የበቃን ያደረግኸን ሁሉን የያዝህ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ለአንተ ምስጋና ይገባል።

Glory be to You, O our God, the Almighty, we give thanks to You, for that we may hear and kiss the glorious word of the gospel and we may rejoice in it.

ወካዕበ ንስእል ወናስተበቍዕ ከመ ትጽሐፍ ውስተ አልባቢነ ቃለ ወንጌልከ ቅዱስ። ወተወከፍ ስእለተነ በውስተ ዝንቱ ምሥዋዒከ ኀበ ቦአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ዳግመኛም ክቡር የሚሆን የወንጌልህን ቃል በልቡናችን ትጽፍ ዘንድ እንለምናለን ፤ እንማልዳለንም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገባበት በዚህ በመሠዊያህ ልመናችንን ተቀበል።

Once again, we ask and beseech You to write down the word of Your glorious gospel in our conscience; and accept our prayer on this temple where our Lord Jesus Christ entered.

ወፌኑ ላዕሌነ ወላዕለ ሕዝብነ ሣህለከ ወምሕረተከ። በ፩ ወልድከ እስመ ለከ ስብሐት ወኃይል ለዓለመ ዓለም አሜን።

በእኛም በወገኖቻችንም ላይ ይቅርታህንና ቸርነትህን ላክ። በአንድ ልጅህ ለአንተ ምስጋና ከሃሊነትም ይገባሃልና ለዘለዓለሙ። አሜን።

And send Your compassion upon us and upon Your people, through Your only-begotten Son, for Yours is the glory and power, world without end. Amen.

ዲያቆን (Deacon)

ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን።

የክርስቲያን ታናሾች የሆናችሁ ውጡ።

Go out, You catechumens.

**ዲያቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

**ካህን (Priest)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

**ካህን (Priest)**

ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንስእል ወነኀሥሥ እምነ ኂሩትከ፤ ኦ መፍቀሬ ሰብእ፤

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ፤ ሰው ወዳጅ ሆይ ከቸርነትህ እንሻለን እንለምናለን።

Again we beseech the almighty God, the Father of our Lord and our Saviour, Jesus Christ: we ask and entreat of Your goodness. O lover of man,

ተዘከር እግዚኦ ሰላመ ቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት አሐቲ ጉባኤ እንተ ሐዋርያት እንተ ሀለወት እምጽንፍ እስከ አጽናፈ ዓለም።

አቤቱ ሐዋርያት የሰበሰቧት አንዲት የምትሆን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሰላም አስብ ፤ ከዳርቻ እስከ እስከ ዓለምዳርቻ ድረስ ያለች።

remember Lord, the peace of the one Holy apostolic Church which reaches from one end of the world to the other.

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በኀበ እግዚአብሔር።

ሐዋርያት ስለሰበሰቧት በእግዚአብሔር ዘንድ ስለቀናች ፤ ለአንዲት ክብርት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ።

Pray for the peace of the one Holy apostolic church orthodox in the Lord.

ካህን/priest/

ኵሎ ሕዝበ ወኵሎ መራዕየ ባርኮሙ። ኵሎ ሰላመ እንተ እምሰማያት ፈኑ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ ወሰላመ ወሕይወተነ ጸግወነ ባቲ።

ሕዝቡን ሁሉ መንጋዎችንም ሁሉ ባርካቸው። ከሰማይ የሚገኝ ሰላምን ሁሉ በሁላችን ልቡና አሳድርብን። በርስዋም የሕይወትን ሰላም ስጠን።

All the people and the whole flock bless You, all the peace that is from heaven send You into the hearts of us all, and vouchsafe us the safety of our life therein.

ጸግዋ ሰላመ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ለታዕካሃ ወለሠራዊታ ወለመኳንንታ ወለሕዝባ። ወጉባኤ አግዋርነ ዘአፍአ ወውስጥ አሠርግዎሙ በኵሉ ሰላም፤

ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ለአንድነቷ ለሠራዊቷም ለመኳንንቷም ለሕዝቧም ሰላምን ስጣት። በእዳሪና በውስጥ ያሉትን ጎረቤቶቻችንን ሁሉ በፍጹም ሰላም አስጊጻቸው።

Vouchsafe peace to our country Ethiopia, to her unity, to her armies, to those who rule her people. And to the multitude of our neighbors at home and abroad; adorn them with all peace:

አ ንጉሠ ሰላም ሰላመከ ሀበነ እስመ ኵሎ ወሀብከነ አጥርየነ እግዚአብሔር ወዕሥየነ እስመ ዘእንበሌከ ባዕድ አልቦ ዘነአምር።

የሰላም ንጉሥ ሆይ ሰላምህን ስጠን ፤ ሁሉን ሰጥተኸናልና እግዚአብሔር ሆይ ጥሪት አድርገን ፤ ዋጋችነንም ስጠን ካንተ በቀር ሌላ የምናውቀው የለምና።

O King of peace, grant us Your peace for You have granted us all things. Possess us, O Lord, and requite us, for beside You we know none other;

ስመከ ቅዱሰ ንሰሚ ወንጼውዕ ፤ ከመ ትሕየው ነፍስነ በመንፈስ ቅዱስ ወኢይትኀየል ሞተ ኃጢአት ላዕሌነ ለአግብርቲከ ወለኵሉ ሕዝብከ፤

ቅዱስ የሚሆን ስምህን ፈጽመን እንጠራለን ፤ ነፍሳችን በመንፈስ ቅዱስ ትድን ዘንድ በኃጢአት የመጣ ሞትም በኛ ባገልጋዮችህ ላይ በወገኖችህም ሁሉ እንዳይበረታታ

we make mention of Your Holy name and call upon it, that our souls may live through the Holy Spirit, and that the death of sin may not have dominion over us Your servants and all Your people:

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

በአሐዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ባንድ ልጅህ ከርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Through Your only-begotten Son to whom with You and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end, Amen.

***ሕዝብ (People)***

ኪርያላይሶን።

Kyrie leison.

**ዲያቆናት (Deacons)**

**ተንሥኡ ለጸሎት።**

**ለጸሎት ተነሡ።**

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

**እግዚኦ ተሣሃለነ።**

**አቤቱ ይቅር በለን።**

Lord have mercy upon us.

upon us.

**ካህናት (Priests)**

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

## ካህን ንፍቅ (Asst. priest)

**ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤**

ዳግመኛም ሁሉን የያዘ የጌታችንና የመድኃታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር እንማልዳለን፤

And again we beseech the almighty God, the Father of our Lord and our Saviour Jesus Christ;

በእንተ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አባ......ከመ ዐቂበ ይዕቀቦ ለነ ለብዙኅ ዓመታት ወለመዋዕለ ሰላም እስከ ይፌጽም ዘእምኀቤሁ ሎቱ ዘተአመኖ ለሢመተ ክህነት ዘብዑለ ጸጋ ይጼጉ እግዚአብሔር አምላክነ።

ብፁዕ ስለሚሆን ሊቀ ጳጳሳት ስለ አባ ________ለብዙ ዘመናት ለሰላም ወራት መጠበቅን ይጠብቅልን ዘንድ ብዙ ጸጋን የሚሰጥ አምላካችን እግዚአብሔር ለክህነት ሹመት የታመነለትን ከሱ ዘንድ እስኪጨርስለት ድረስ።

For the blessed Patriarch Abba ....... that he truly preserve him to us for many years and in peaceful days until the Lord our God who is rich in grace grant him to fulfil that which was committed unto him, the office o priesthood.

## ዲያቆን ንፍቅ (Asst. deacon)

ጸልዩ በእንተ ሊቀ ጳጳሳት አባ ......እግዚእነ ርእሰ ኤጲስ ቆጳሳት ዘሀገር ዐባይ ኢትዮጵያ ወዲበ ርዕሰ ሀገረ አበዊነ ብፁዕ ሊቀ

ስለ ሊቀ ጳጳሳቱ ስለ አባ ......የደገኛዪቱ አገር የኢትዮጵያ የኤጲስ ቆጳስ አለቃ ጌታ ስለሚሆን፤ በአባቶቻችን አገርም ብፁዕ ስለሚሆን ስለ አባ .......ሃይማኖታቸው ስለ ቀና ስለ ኤጲስ

Pray for the Patriarch Abba …… lord chief of the bishops of the great nation of Ethiopia and for the blessed Primate of the country of our father Abba. ……..and all the orthodox bishops, priests and deacons.

ጳጳስነ አባ......... ወኵሎሙ ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ርቱዓነ ሃይማኖት።

ቆጶሳቱ ስለ ቀሳውስቱና ስለ ዲያቆናቱ ሁሉ ጸልዩ።

........and all the orthodox bishops, priests and deacons.

## ካህን ንፍቅ (Asst. priest)

እግዚአብሔር አምላክነ ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ በእንተ ብፁእ ጳጳስ አባ.......ከመ ዐቂበ ትዕቀቦ ለነ ለብዙኅ ዓመታት ወለመዋዕለ ሰላም እስከ ይፌጽም ዘእምኀቤከ ሎቱ

ሁሉን የያዝህ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም ፤ ብፁዕ ስለሚሆን ስለ አባ ....... ለብዙ ዘመናት ለሰላምም ወራት መጠበቅን ትጠብቀው ዘንድ፤

Lord our God almighty, we pray and beseech You for our blessed archbishop Abba ...... that You may truly preserve him to us for many years

ዘተአመንኮ ለሢመተ ክህነት ምስለ ኵሎሙ ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ርቱዓነ ሃይማኖት።

ካንተ ዘንድ ለክህነት ሹመት እሱን የመረጥህለትን ሥራ እስኪፈጽም ድረስ ፤ ከኤጲስ ቆጶሳቱ ሁሉ ጋራ ሃይማኖታቸው ከቀና ከቀሳውስቱና ከዲያቆናቱም ጋራ፡

and in peaceful days to fulfill the office of priesthood which You have committed unto him, together with all the orthodox bishops, priests and deacons,

ወምስለ ኵሉ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተ ክርስቲያን ወጸሎተኒ ዘይገብር በእንቲአነ ወበእንተ ኵሉ ሕዝብከ ተወከፎ፤

ከሁሉ በላይ ከምትሆን ከአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከአንድነትዋም ፍጻሜ ሁሉ ስለ እኛ ስለወገኖችህ ሁሉ የሚያደርገውን ጸሎት ተቀበለው።

And all the entire congregation of the one holy universal church; and the prayer which he makes on our behalf and on behalf of all Your people do You accept;

አርኁ ሎቱ መዝገበ በረከትከ ፤ ዓዲ ፈድፋደ ሎቱ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ጸግዎ ፀጋ ፤ ወከዐው ላዕሌሁ እምሰማይ በረከተከ ከመ ይባርክ ሕዝበከ፤

የበረከትህንም መዝገብ ክፈትለት ፤ ዳግመኛ ይልቁን ለእርሱ የመንፈስ ቅዱስን ሀብት ስጠው። ወገኖችህን ይባርክ ዘንድ ከሰማይ በረከትህን በላዩ ላይ አፍስስ።

open to him the treasure-house of your blessing, and especially grant to him abundantly the grace of the Holy Spirit; pour up on him from heaven Your blessing that he may bless Your people;

ወሆሎ እንከ ፀሮ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ አግርር ወቀጥቅጥ ታሕተ እገሪሁ ፍጡነ ፤ ወኪያሁሰ እንከ ዕቀቦ ለነ በጽድቅ ወበሰላም ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት በስብሐት ወበጸሎት።

የሚታየውንና የማይታየውን ጠላቱን ሁሉ ፈጥነህ ከእግሩ በታች አድርገህ ቀጥቅጠህ አስገዛለት። እርሱን ግን በእውነት በሰላም ለክብርት ቤተ ክርስቲያንህ ብለህ በክብር ጠብቅልን።

And all his enemies, visible and invisible, do You subdue and bruise under his feet speedily; but himself do You preserve unto us in righteousness and peace and glory, for Your Holy church;

በ፩ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ ፤ አሜን።

Through Your only-begotten Son through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end, Amen.

## ዲያቆናት (Deacons)

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

## ሕዝብ (People)

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us. upon us.

## ካህናት (Priests)

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

## ሕዝብ (*People*)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን(priest)

ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ንስእል ወነኀሥሥ እምነ ኂሩትከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ።

ዳግመኛም ሁሉን የያዘ የጌታችንና የመድኃታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ፤ ሰው ወዳጅ ሆይ ከቸርነትህ እንሻለን እንለምናለን።

And again we make our supplication to the almighty God, the Father of our Lord and our Saviour Jesus Christ; we ask and entreat of Your goodness, O lover of man:

ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ ባርኮሙ።

አቤቱ አንድነታችንን አስብ ፤ ባርካቸው።

Remember, Lord, our congregation; bless them.

**ዲያቆን (Deacon)**

ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ወማኅበርነ በውስቴታ።

ክብርት ስለምትሆን ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ስለአለ አንድነታችንም ጸልዩ።

Pray for this Holy church and our congregation therein.

**ሕዝብ (People)**

ማኅበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም።

አንድነታችንን ባርክ ፤ በሰላም ጠብቅ።

Bless our congregation and keep them in peace.

ካህን (priest)

ወጸግዎሙ ከመ ይኩኑ ለከ ዘእንበለ ጽርዓት ወኢክልዓት ይግበሩ ፈቃደከ ቅድስተ ወብፅዕተ ቤተ ጸሎት ቤተ ንጽሕ ወቤተ በረከት፤

የተደነቀችና የከበረች ፈቃድህን ያለ ማቋረጥና ያለመከልከል እንዲሠሩ ያንተ ይሆኑ ዘንድ፤ የጸሎትን ቤት ፤ የንጽሕናንም ቤት የበረከትንም ቤት ስጣቸው።

Grant that they maybe Yours that without slothfulness or hindrance they may do Your Holy and blessed will, a house of prayer, a house purity and a house of blessing.

ጸግወነ እግዚኦ ለነኒ ለአግብርቲከ ወለእለ ይመጽኡ እምድኅሬነ እስከ ለዓለም መዋዕለ ጸጉ። ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወይዘረዉ ፀርከ ወይጕየዩ ኵሎሙ እምቅድመ ገጽከ እለ ይጸልዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ።

ለእኛም ለአገልጋዮችህ ከኛም በኋላ ለሚነሡ ፤ አቤቱ ስጠን። እስከ ዘለዓለምም ዘመንን ስጥ። አቤቱ አምላኬ ሆይ ተነሥ ጠላቶችህም ይበተኑ ፤ ቅዱስ ምስጉን የሚሆን ስምህን የሚጠሉ ሁሉም ከፊትህ ይሸሹ።

Give us also, Lord, us Your servants, and to them that shall come after us, vouchsafe us to the end of the world, length of days. Arise, Lord my God, and let Your enemies be scattered, and let them that hate Your Holy and blessed name flee before You.

ወሕዝብከሰ ይኩኑ ቡሩካነ በበረከተ አእላፈ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት እለ ይገብሩ ፈቃደከ ለዝሉፉ በኵሉ ጊዜ።

በጊዜው ሁሉ ፈቃድህን የሚሠሩ ወገኖችህ ግን እልፍ አእላፋት ትእልፊተ አእላፋት በሚሆኑ መላእክት በረከት የተባረኩ ይሁኑ።

But let Your people who do Your will at all times be blessed with blessings a thousand thousands and ten thousand times

በጳጉ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ባንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ፤ ከእርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

ten thousand through Your only-begotten Son through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end, Amen.

ዲያቆን (Deacon)

ንበል ኵልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሃይማኖት።

በእግዚአብሔር ጥበብ ሁነን ሁላችን የሃይማኖት ጸሎት እንበል።

Let us all say, in the wisdom of God, the prayer of faith.

ነአምን በ፩ዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ።

ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን ÷ የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

We Believe in one God the Father almighty, maker of heaven, earth and all things visible and invisible.

ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘሀልው ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ ዘእምአምላክ ዘበአማን።

ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋራ በነበረ የአብ አንድ ልጅ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ፤

And we believe in one Lord Jesus Christ, the only-begotten Son of the Father who was with Him before the creation of the world: Light from light, true God from true God,

ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ በመለኮቱ ፤ ዘቦቱ ኲሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ።

የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል። ሁሉ በርሱ የሆነ ፤ በሰማይ ካለው በምድርም ካለው ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም።

begotten not made, of one essence with His Father: All things were made by Him, and without Him nothing whatsoever was made, in Heavens or on Earth.

ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ ወረደ እምሰማያት። ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ኮነ ብእሴ

ስለእኛ ስለሰው ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ። ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ከቅድስት ድንግል ማርያምም ፈጽሞ ሰው ሆነ።

Who for us men and for our salivation came down from heaven, was made man and was incarnate from the Holy Spirit and from the Holy Virgin Mary. Became man,

ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ። ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት። ዐርገ በስብሐት

ሰው ሆኖ በጴንጤናዊ በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ፤ ታመመ ፤ ሞተ ፤ ተቀበረም። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ አረገ ፤

was crucified for our sakes in the days of Pontius Pilate, suffered, died, was buried and rose from the dead on the third day as was written in the Holy scriptures: Ascended in glory into heaven,

ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።

በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

sat at the right hand of His Father, and will come again in glory to judge the living and the dead; there is no end of His reign.

ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት።

ጌታ ማሕየዊ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋራ በነቢያት የተናገረ።

And we believe in the Holy Spirit, the life- giving God, who proceeds from the Father; we worship and glorify Him with the Father and the Son; who spoke by the prophets;

ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት። ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት።

ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን። ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

And we believe in One Holy, universal, apostolic church; And we believe in One baptism for the remission of sins,

ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም አሜን።

የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን ፤ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።

and wait for the resurrection from the dead and the life to come, world without end. Amen!

## ካህን (Priest)

ዘኮነ ንጹሐ ይንሣእ እምቍርባን ፤ ወዘኢኮነ ንጹሐ ኢይንሣእ ከመ ኢየዐይ በእሳተ መለኮት ዘተደለወ ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ።

ንጹሕ የሆነ ከቍርባኑ ይቀበል ፤ ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል ፤ ለሰይጣንና ለመላክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እዳይቃጠል።

He that is pure let him receive of oblation and he that is not pure let him not receive it, that he may not be consumed by the fire of the godhead which is prepared for the devil and his angles.

ዘቦ ቂም ውስተ ልቡ ወዘቦ ውስቴቱ ሕሊና ነኪር ወዝሙት ኢይቅረብ። በከመ አንጻሕኩ እደውየ እምርስሐት አፋአዊ ከማሁ ንጹሕ አነ እምደመ ኵልክሙ።

በልቡናው ቂምን የያዘ ፤ ልዩ አሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ። እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ እንደዚሁም ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ።

Whosoever has revenge in his heart and who ever has in him strange thoughts and fornication let him not draw near. As I have cleansed my hands from outward pollution, so also I am pure from the blood of you all.

በድፍረትክሙ ለእመ ቀረብክሙ ኀበ ሥጋሁ ወደሙ ለክርስቶስ አልቦ ላዕሌየ ትኀላፍ ለተመጥዎትክሙ እምኔሁ። ንጹሕ አነ እምጌጋይክሙ ዳዕሙ ኃጢአትክሙ ይገብእ ዲበ ርእስክሙ ለእመ በንጹሕ ኢቀረብክሙ።

ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም ፤ ኃጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጅ። በንጽሕና ሆናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ።

If you presumptuously draw near to the body and blood of Christ I will not be responsible for your reception thereof. I am pure of your wickedness, but your sin will return upon yourself if you do not draw nigh in purity.

## ዲያቆን (Deacon)

እመቦ ዘአስተሐቀረ ዘንተ ቃለ ቀሲስ ፤ አው ዘሰሐቀ ወዘተናገረ፤ አው ዘቆመ በእከይ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ለያእምር ወይጠይቅ ከመ አምዕዖ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወአንሰሐስሐ ላዕሌሁ

ይህንን የካህኑን ቃል ያቃለለ ፤ ወይም የሳቀና የተነጋገረ ፤ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክፋት የቆመ ቢኖር ፤ ጌታችንንና መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳሳዘነው ፤

If there is any who disdains this word of the priest or laughs or speaks or stands in the church in an evil manner, let him Know and understand that he is provoking to wraith our Lord Jesus Christ.

ህይንተ ቡራኬ መርገመ ፧ ወህይንተ ሥርየተ ኃጢአት እሳተ ገሃነም ይረክብ እምኀበ እግዚአብሔር።

በርሱም እንደተነሣሣ ይወቅ ይረዳ። ስለ በረከት ፈንታ መርገምን ፧ ስለ ኃጢአት ሥርየት ፈንታም ገሃነመ እሳትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል።

and bringing upon himself a curse instead of a blessing, and will get from God the fire of hell instead of the remission of sin.

ካህን(priest)

ኦ እግዚእየ ወአምላኪየ ገባሬ ሥርዓት ወሃቤ ሰላም ወፍቅር አሰስል እምላዕሌየ ኵሎ ሕሊና እኩየ ቂመ ወቅንዓተ ወኵሎ ፍትወታተ ሥጋውያተ ወክፍለኒ እደመር

አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ሆይ ሥርዓትን የሠራህ ሰላምንና ፍቅርን የምትሰጥ ክፉውን ሕሊና ሁሉ ቂምን ቅንዓትንም ሥጋዊ ፈቃድንም ሁሉ ከኔ አርቅልኝ።

O my Lord and my God, author of the Law, giver of peace and love, take away from me every evil thought, revenge, envy, and all the lusts of the flesh.

ምስለ አግብርቲከ ቅዱሳን እለ አሥመሩከ በሠነ ሕይወቶሙ በመዋዕለ ፍቅር ወሰላም ፤ እስመ አንተ ውእቱ ዘወረድከ እምሰማይ ወገበርከ ሰላመ ምስለ ሰማያውያን ወምድራውያን

በበጎ ሕይወታቸው በሰላምና በፍቅር ወራት ካገለገሉህ ከክቡራን አገልጋዮችህ ጋራ አንድ እንድሆን አድለኝ። ከሰማይ የወረድህ ከሰማያውያንና ከምድራውያን ጋራ ሰላምን ያደረግህ።

Make me meet to be added to Your Holy servants who pleased You by the beauty of their lives in the days of love and peace፡ Because it is You who did come down from heaven and make peace between the inhabitants of heaven and the inhabitants of earth,

ወአስተጋባእኮሙ ለኵሎሙ ሕዝብከ ከመ ይሰብሑ ኪያከ እስመ ለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን።

አንተንም ያመሰግኑ ዘንድ ወገኖችህንም ሁሉ የሰበሰብሃቸው አንተ ነህና ምስጋና የሚገባህ ስለ ሆነ ለዘለዓለሙ አሜን።

and did gather together all Your people to glorify You, for Yours is the glory, world without end. Amen.

# ሥርዓተ ቅዳሴ - Preparatory Service

**ዲይቆን (Deacon)**

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

**ሕዝብ (People)**

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us. upon us.

## ካህን (Priest)

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

## ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

# ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ

## ባስልዮስ የተናገረው የስጦታ ጸሎት

## Prayer of Salutation Basil

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ዐቢይ ዘለዓለም ዘለሐኮ ለሰብእ እንበለ ሙስና።

ለዘላለሙ ገናና የምትሆን እግዚአብሔር ሆይ ፣ ያለጥፋት ሰውን የፈጠርኸው ፤

God, great eternal, Who did form man uncorrupt,

ሞተ ዘቦአ ቀዳሚ በቅንዓተ ሰይጣን አብጠልከ በምጽአቱ ለሕያው ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

አስቀድሞ በሰይጣን ቅንዓት የገባውን ሞት ሕያው በሚሆን ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አጠፋህ።

You did abolish death that came first through the envy of Satan, by the advent of Your living Son our Lord, and our God, and Saviour Jesus Christ,

ወመላዕከ ኲላ ምድረ ሰላመከ እንተ እምሰማያት እንተ ባቲ ሠራዊተ ሰማያት ይሴብሑከ እንዘ ይብሉ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ፤ ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ።

የሰማይ ሠራዊት እንዲህ እያሉ አንተን ያመሰገኑባትን ከሰማይ የተገኘች ሰላምን በምድር ሁሉ መላህ። “በሰማይ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይገባል ፤ በምድርም ሰላም የሰው ፈቃድ።”

and You did fill all the earth with Your peace which is from heaven wherein the armies of heaven glorify You saying : “Glory to God in heaven and on earth peace, His goodwill toward men.”

**ሕዝብ (People)**

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ፤ ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ።

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል። በምድርም ሰላም ፤ የሰው ፈቃድ።

Glory to God in heaven and on earth peace, His goodwill toward men.

ካህን(priest)

ኦ እግዚኦ በሥምረትከ ምላዕ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ ወአንጽሖነ እምኵሉ ደነስ ወእምኵሉ ምርዓት ፤ ወእምኵሉ ቂም ወቅንዓት ፤ ወእምኵሉ ምግባር ሐሱም ወእምተዘክሮ እኪይ እንተ ታለብስ ሞተ።

አቤቱ ፈቃድህን በሁላችን ልቡና ሙላ ፤ ከኃጢአትም ሁሉ ከጽርዓትም ሁሉ አንጻን። ከቂምና ከቅንዓት ሁሉ ፤ ከክፉም ሥራ ሁሉ ሞትን ከምታለብስ ክፉን ነገር ከማሰብ አንጻን።

O Lord, in Your Goodwill fill the hearts of us all and purify us from all corruption and from all excess, and from all revenge and envy, and from all wrongdoing and from the remembrance of ill which clothes with death.

ወረስየነ ለኵልነ ድልዋነ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ በአምኃ ቅድሳት።

በተለየች እማኄ እርስ በርሳችን እጅ እንነሳ ዘንድ ሁላችንንም የበቃን አድርገን።

And make us all meet to salute one another with a Holy salutation.

**ዲያቆን (Deacon)**

ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት ወፍቅር ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት።

ፍጽምት ስለምትሆን ሰላምና ፍቅር ጸልዩ። እርስ በእርሳችሁ በተለየች ሰላምታ እጅ ተነሣሡ።

Pray for the perfect peace and love. Salute one another with a Holy salutation.

**ሕዝብ (People)**

ክርስቶስ አምላክነ ረስየነ ድልዋነ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ በአምኃ ቅድሳት።

አምላካችን ክርስቶስ ሆይ እርስ በርሳችን በተለየች ሰላምታ እጅ እንነሣሣ ዘንድ የበቃን አድርገን።

Christ our God, make us meet to salute one another with Holy salutation.

ካህን (Priest)

ወንትመጠ እንበለ ኰነኔ እምሀብትከ ቅድስት እንተ ይእቲ እንበለ ሞት ሰማያዊት በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ።

ክብርት ከምትሆን ስጦታህ ሳይፈረድብን እንቀበል። ይህችውም የማታልፍ ሰማያዊት ናት።

And to partake, without condemnation, of Your Holy immortal heavenly gift, through Jesus Christ our Lord:

ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ለአንተ ምስጋና ይገባል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

# ቅዳሴ ያዕቆብ ዘሥሩግ ከዚህ ይጀምራል።
# THE ANAPHORA OF ST. JACOB OF SERUGH STARS HERE.

ካህን (Priest)

አኰቴተ ቍርባን ዘቅዱስ ያዕቆብ ኤጲስቆጶስ ዘሥሩግ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቲነ..........ወምስለ ሊቀ ጳጳስነ........... ወምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ወይዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ለዓለመ ዓለም አሜን።

የሥሩግ ኤጲስቆጶስ የቅዱስ ያዕቆብ የቊርባን ምስጋና። ጸሎቱና በረከቱ ከጳጳሳቱ አለቃ ...............ና ከጳጳሳችን.................. ከሁላችንም ጋራ ይኑር ፤ አገራችንን ኢትዮጵያን ይጠብቃት።

The Anaphora of Jacob, Bishop of Serough; may his prayer and blessing be with Patriarch and Our Bishop, and may He watch over Ethiopia, world without end. Amen

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ።

እግዚአብሔር ከሁላችሁም ጋር ይሁን።

The Lord be with you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን (Priest)

አእኰትዎ ለአምላክነ።

አምላካችንን አመስግኑት።

You, give thanks unto our God.

ሕዝብ (People)

ርቱዕ ይደሉ።

እውነት ነው ይገባዋል።

It is right, it is just.

ካህን (Priest)

አልዕሉ አልባቢክሙ።

ልቡናችሁ ሰማያዊ ነገርን ያስብ።

Lift up your hearts.

ሕዝብ (People)

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ።

በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን።

We have lifted them up unto the Lord our God.

# ቡራኬ

# Benediction

ካህን (Priest)

ተንሥኡ በፍርሃተ እግዚአብሔር ከመ ታጽምዑ አርኅዉ መሳክወ እእዛኒክሙ ወአንቅሑ ልበክሙ።

እግዚአብሔርን በመፍራት ተነሡ። ትሰሙ ዘንድ የጆሯችሁን መስኮት ክፈቱ ፤ ልቡናችሁንም አንቁ።

Stand up in the fear of God, open the windows of your ears that you may attend, and awaken your hearts.

አኮ በከመ ዘይከውን ሐልዎትነ ውስተ ዝንቱ መካን እግዚአብሔር ይሬኢ ወይፈትን ለለ አሐዱ አሐዱ እምኔነ።

በዚህ ቦታ ውስጥ መኖራችን ከንቱ የሚሆን አይደለም። ከእኛ ወገን እያንዳንዱን እግዚአብሔር ያያል ፤ ይመረምራልም።

Our being here in this place is not in vain. God sees and examines everyone of us.

ንቅረብ ወንስአሎ ለእግዚአብሔር እንዘ ንዜከሮሙ ለቀደምት አበው እለ አዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት። ወንዌጥን እምሐልዎቱ ለአብ ክቡር ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ..........ወዲበ ሱታፌሁ

በቀናች ሃይማኖት ያረፉትን የቀደሙ አባቶችን እያሰብን ቀርበን እግዚአብሔርን እንለምነው። ክቡር አባት በሚሆን በርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ በአባ...............ና በሚመስለው በጳጳሱ በአባ .........

Let us draw near and offer our prayer to God remembering the ancient fathers who gained their rest in the right faith; and we begin from the present honourable father, the Patriarch Abba ..................and his fellow,

ሊቀ ጳጳስነ አባ ................።

በጳጳሱ በአባ ................ ህልዎት እንጀምራለን።

Archbishop Abba ……..

ዲያቆን (Deacon)

በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ............፤ ወብፁዕ ጳጳስ አባ...............................።

ብፁዕ ቅዱስ ስለሚሆን ስለ ርእሰ ጳጳሳት ስለ አባ..................
ብፁዕም ስለሚሆን ስለ አባ .........

For the sake of the blessed and holy Patriarch Abba ............ and the blessed Archbishop Abba ....................

እንዘ የአኰቴከ በጸሎቶሙ ወበስእለቶሙ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት ዘካርያስ ካህን ወዮሐንስ መጥምቅ።

በጸሎታቸውና በልመናቸው ሲያመሰግኑህ የሰማዕታት መጀመሪያ እስጢፋኖስ። ካህኑ ዘካርያስና መጥምቁ ዮሐንስ

While they yet give thee thanks in their prayer and in their supplication: Stephen the first martyr, Zacharias the priest and John the Baptist.

ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት እለ አዕረፉ በርትዕት በሃይማኖት ማቴዎስ ወማርቆስ ሊቃስ ወዮሐንስ ፬ቱ ወንጌላውያን። ማርያም ወላዲተ አምላክ። .......

በሃይማኖት ስላረፉ ስለ ቅዱሳንና ስለ ሰማዕታት ሁሉ፤ አራቱ ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ ሉቃስና ዮሐንስ፤ አምላክን የወለደች ማርያም።.......

And for the sake of all the saints and martyrs who have gone to their rest in faith Matthew and mark, Luke and John the four Evangelist; Mary the mother of God,.......

ካህን/priest/

ኦ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ባርክ ዲበ ሕዝብከ ፍቁራን ክርስቶሳውያን በበረከተ ሰማያውያን ወምድራውያን ወፈኑ ላዕሌነ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ።

ልዩ ሦስት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ የሚፋቀሩ የክርስቶስ ወገኖች የሚሆኑ ሕዝብህን በሰማያውያንና ምድራዊያን በረከት ባርክ። በእኛ ላይም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክ።

O; Holy Trinity Father and Son and Holy Spirit, bless Your people, Christians beloved, with blessings heavenly and earthly and send upon us the grace of the Holy Spirit

ወረሲ ኆዋኀወ ቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት ርኀዋተ ለነ በምሕረት ወበአሚን ወፈጽም ለነ አሚነ ሥላሴከ ቅድስት እስከ ደኃሪት እስትንፋስ።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንህም ደጆች በምሕረትና በሃይማኖት እንዲከፈቱ አድርግልን እስከ መጨረሻዪቱ ሕቅታም ድረስ ልዩ ሦስትነትህን ማመንን ፈጽምልን።

and make the doors of Your Holy Church open unto us in mercy and in faith; and perfect unto us the faith of Your Holy trinity unto our latest breath .

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐውጽ ሕሙማነ ሕዝብከ ፈውሶሙ ወምርሖሙ ለአበዊነ ወለአኀዊነ እለ ሖሩ ወተአንገዱ ወሚጦሙ ኀበ ማኅደሪሆሙ በሰላም ወበጥዒና ባርክ ነፋሳተ ሰማይ።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የታመሙ ወገኖችህን ጐብኝ የሄዱትንና እንግዶች የሆኑትን አባቶቻችንን ወንድሞቻችንን መርተህ በሰላምና በጤና ወደ ቤታቸው መልሳቸው። የሰማዩን ነፋስ ባርክ።

O my Lord Jesus Christ visit the sick of Your people; heal them; and guide our fathers and our brothers who have gone forth and become strangers bring them back to their dwelling places in peace and in health. Bless the airs of heaven

ወዝናማተ ወፍሬያተ ምድር ዘዛቲ ዓመት በከመ ጸጋከ ወረሲ ፍግዓ ወተድላ ወትረ ዲበ ገጸ ለምድር ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ ሚጥ ልበ ነገሥት አዚዛን ለአሠንዮ ላዕሌነ በኵሉ ጊዜ።

ዝናሙንም በዚህች ዓመት የሚያፈራውን የምድሩን ፍሬ እንደ ቸርነትህ ባርክ ዘወትር ተድላንና ደስታን አድርግ ሰላምህንም አጽናልን ሁልጊዜ ለኛ በጎ ነገርን ሊያደርጉልን ጽኑዓን የሚሆኑ የኃያላኑን ልቡና መልስ።

and the rains and the fruits of the earth of this year, in accordance with Your grace, and make joy and gladness prevail perpetually on the face of the earth And establish for us Your peace. Turn the hearts of mighty kings to deal Kindly with us always.

ጸጉ ሰላመ ለሊቃውንተ ቤተ ክርስቲን እለ ጉቡኣን ውስተ ቤተ ክርስቲን ቅድስት ኵሎ ጊዜ ለኵሉ ለለአሐዱ በበአስማቲሆሙ በቅድመ ኃያላን አምላክነ አንኅ ሎሙ።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ሁል ጊዜ ለሚሰበሰቡ ለቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ፍቅርን ስጥ ለሁሉም ለያንዳንዱ በየስማቸው ኃያላን በሚሆኑ ፊት ሰላምን አብዛላቸው።

Grant peace of the scholars of the church who are continually gathered in Your Holy Church; to all, to each by their own names; in the presence of powerful kings, O our God, increase Your peace,

ወአዕርፍ ነፍሳተ አበዊነ ወአኀዊነ ወአኃቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት።

አምላካችን ሆይ በቀናች ሃይማኖት ሆነው ያንቀላፉትንና ያረፉትን ያባቶቻችንንና የወንድሞቻችንን የእኅቶቻችንንም ነፍስ አሳርፍ።

Rest the souls of our fathers and our brothers and our fathers and our brothers and our sisters who have fallen asleep and gained their rest in the right faith.

ወባርክ ዲበ እለ ያስተነትኑ በዕጣን ወቍርባን ወወይን ወቅብዕ ወዘይት ወመንጠዋልዕ ወመጻሕፍተ ምንባባት ወንዋያተ መቅደስ ከመ ክርስቶስ አምላክነ ይዕሥዮሙ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት።

አምላካችን ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ዋጋቸውን ይከፍላቸው ዘንድ ዕጣንና ቍርባን ወይንና ሜሮን ዘይትም መጋረጃም የንባብ መጽሐፍቶችን የቤተ መቅደስንም ንዋያት በመስጠት የሚያገለግሉትን ባርክ።

And bless those who give gifts of incense and bread and wine, and ointment and lamp oil, and hangings and reading books and vessels for the sanctuary, that Christ our God may give them their reward in the heavenly Jerusalem.

ወለኵሎሙ እለ ተጋብኡ ምስሌነ ይኅሥሡ ምሕረተ ክርስቶስ አምላክነ ተሣሃል ላዕሌሆሙ ወለኵሎሙ እለ አምጽኡ ምጽዋተ በቅድመ መንበርከ መፍርህ ወመደንግፅ ተወከፎሙ።

ይቅርታን ያገኙ ዘንድ ከእኛ ጋራ የተሰበሰቡትን ሁሉ አምላካችን ክርስቶስ ሆይ ይቅር በላቸው በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ በመንበርህ ፊት ምጽዋት ያመጡትንም ሁሉ ተቀበላቸው።

And all them that are assembled with us to entreat for mercy: Christ our God have mercy upon them: and all them that give alms before Your awful and terrifying throne, receive.

ወአንጊ ለኵላ ነፍስ ዕፅብት ወእለ እሡራን በመዋቅሕት ወእለ ሀለዉ ውስተ ስደት ወፂዋዌ ወእለ እኁዛን በቅኔ መሪር አምላክነ አድኅኖሙ በምሕረትከ።

የተጨነቀችዪቱን ነፍስ ሁሉ አሳርፍ በሰንሰለት የታሰሩትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም መሪር በሆነ አገዛዝ የተያዙትንም አምላካችን ሆይ በቸርነትህ አድናቸው።

And comfort every straitened soul, them that are in chains and them that are in exile or captivity. And them that are held in bitter servitude: our God, deliver them in Your mercy.

ኦ ሊቅነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኵሎሙ እለ አዘዙነ ከመ ንዘከሮሙ በጊዜ አስተብቍዖትነ ኀቤከ ተዘከሮሙ በመንግሥትከ ሰማያዊት ወሊተኒ ለኃጥእ ገብርከ ተዘከረኒ።

መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ወዳንተ በምንማልድበት ጊዜ እንድናስባቸው ያዘዙንን ሁሉ በሰማያዊት መንግሥትህ አስባቸው፡፡ ኃጥእ ባርያህን እኔንም አስበኝ።

And all them that have entrusted it to us to remember them in our supplications to You: Our Master Jesus Christ, remember them in Your heavenly kingdom, and remember me, Your sinful servant.

ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ። ረዓዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም።

አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ። ጠብቃቸው እስከ ዘላለምም ከፍ ከፍ አድርጋቸው።

O Lord, save Your people and bless Your inheritance feed them and lift them up for ever.

ዲያቆን (Deacon)

መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት ፤ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን።

አቤቱ የጳጳሳት አለቆችን ፤ ጳጳሳቱንና ኤጲስ ቆጶሳቱን ፣ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን ፤ የክርስቲያን ወገኖችን ሁሉ ማራቸው ፤ ይቅርም በላቸው።

Lord pity and have mercy upon the patriarchs, March bishops, bishops, priest, deacons and all the Christian people.

ካህን (Priest)

ለእሉኒ ወለኵሎሙ እለ ተጸውዐ ስሞሙ ፤ ወእለ ኢተጸውዐ አስማቲሆሙ ፤ ወእለ ተገብረ ሎሙ ዝንቱ ተዝካር ሠናይ በቅድሜከ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣሃሎሙ።

እኝህንና ሁሉንም ስማቸው የተጠራውንና ስማቸው ያልተጠራውን ይህ በጎ መታሰቢያ በፊትህ የተደረገላቸውንም ነፍሳቸውን አሳርፍ ይቅርም በላቸው።

Rest the souls of these and all those whose names have or have not been called, and those on behalf of whom this good memorial has been made before Your, and have mercy upon them

ዘፈኖከ እምሰማይ ወልደከ ውስተ ማኅፀነ ድንግል ይግበር ፈቃደከ።

ፈቃድህን ያድርግ ዘንድ ከሰማይ ወደ ድንግል ማኅፀን ልጅህን የላክ።

You Who sent Your Son from heaven into the womb of the Virgin to fulfill Your will:

ዲያቆን (Dacon)

እለ ትነብሩ ተንሥኡ።

የተቀመጣችሁ ተነሡ።

You, that are sitting, stand up.

ካህን (Priest)

ሎቱ ለወልድከ ፤ አወፈይኮ ፤ ወአሠልጠንኮ ፤ ወወሀብኮ ወአኰነንኮ ኵነኔ ሰማያት ወምድር እንዘ ሥሉጥ ውእቱ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም።

ለእርሱ ለልጅህ ሰጠኸው ፤ አሠለጠንኸውም። ዓለም ሳይፈጠር ሥሉጥ ሲሆን ሰማይንና ምድርን መግዛትን ሰጥተህ አስገዛኸው።

To Him, to Your Son, You did grant authority to judge heaven and earth, even so, He had the authority before the world was created.

ዲያቆን (Deacon)

ውስተ ጽባሕ ነጽሩ።

ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ።

Look to the east.

ካህን (Priest)

ሎቱ ለዋሕድከ ሚመጠን ዕበይ ወክብር ፤ ወትሕትና ፤ ወትዕግሥት ዘምስለ ክሂል።

ለእርሱ ለአንድ ልጅህ ምን ያህል ገናናነትና ክብር ፤ ትሕትና ከኪሂልም ጋራ ትዕግሥት አለው።

How profound is the greatness of Your only One, and of His honour, humility, patience with might.

## ዲያቆን (Deacon)

ንነጽር።

እናስተውል።

Let us give heed.

ካህን (Priest)

ሎቱ ለፍቁርከ ይሰግዱ መላእክት ፣ ወሊቃነ መላእክት ረበዋተ ረበዋት ወኵሉ ስም ዘይሰመይ በታሕተ ሰማይ ወምድር።

ለእርሱ ለወዳጅህ መላእክትና ሊቃነ መላእክት ይሰግዱለታል። የአለቆች አለቆችና ከሰማይና ከምድር በታች የሚጠራም ስም ሁሉ።

To Him, to Your Beloved bow the angels, archangels, ten thousand times ten thousand, and every name under heaven and on earth.

ሠራዊተ ሚካኤል በበነገዶሙ ፤ ወሠራዊተ ገብርኤል በበማኅበሮሙ ፤ ኪሩቤል በግርማሆሙ ፤ ወሱራፌል በቅዳሴሆሙ።

የሚካኤል ሠራዊት በየነገዳቸው ፤ የገብርኤልም ሠራዊት በየማኅበራቸው ፤ ኪሩቤልም በግርማቸው ፤ ሱራፌልም በቅዳሴያቸው።

The hosts of Michael in their tribes, and the hosts of Gabriel in their congregation, the cherubim in their might,

ወኵሎሙ ሠራዊተ መላእክት በበፀታሆሙ ይሴብሕዎ ለእግዚአብሔር ለዘበስብሐተ ቅዱሳን ይሴባሕ።

የመላእክትም ሠራዊት በየወገናቸው በቅዱሳን ምስጋና የሚመሰገን እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል።

and the seraphim in their sanctification, and all the hosts of angels in their ranks glorify God Who is glorified with the glory of the saints.

ዲያቆን (Deacon)

አውሥኡ።

ተሰጥኦውን መልሱ።

You answer.

ሕዝብ (People)

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይ የመላ ነው።

Holy Holy Holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the Holiness of Your Glory.

ካህን/priest/

ወንሕነኒ ንበል ምስሌሆሙ ኅቡረ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አንተ ዘበአማን እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ

እኛም ከርሱ ጋራ በአንድነት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንበል አንተ በእውነት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን

Let us also say together with them, Holy Holy Holy, Lord, You are truly our Lord and our God and our Savior

ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ በቅድሳቲከ ፤ ልዑል በልዕልናከ ፤ ወእኵት በአኰቴትከ ፤ ወስቡሕ አንተ በስብሐተ ቅዱሳን መላእክቲከ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድስናህ የተቀደስህ ፤ በልዕልናህ ከፍ ያልህ፤ በምስጋናህ የተመሰገንህ ፤ በቅዱሳን መላእክት ምስጋና የከበርህ ነህ።

Jesus Christ, Holy in Your holiness, great in Your greatness, praised in Your thanks giving and glorified with the glory of Your Holy angels.

ኦ እግዚኦ ኪያከ ይመስል በአርኣያ ወበፀዳል ዘወለደኮ። ወፍንው አንተ እምኀቤሁ ለአቡከ። ነቅዕ ዘእምነቅዕ ዘውኅዘ እምአርያም ፈትል ነዊኅ ዘኢይትበተክ እምአብ ፈጣሬ ሰማያት ወምድር

አቤቱ የወለደህ(አብ) በመልክና በብርሃን አንተን ይመስላል። አንተም ከአባትህ ዘንድ ተልከሃል። ከአርያም ከፈሰሰ ምንጭ የተገኘ ምንጭ ከአብ የማይለይ ረጅም ፈትል ሰማይና ምድርን የፈጠርህ ፧

O Lord, He who begat You resembles You in image and appearance, You were sent by the Father, and You are a spring, from the spring, sprung from heaven. You are the long cord which will not be severed from the Father; You are the creator of heaven and earth.

እምሰማይ ወረድከ በፈቃድከ ማኅፀነ ድንግል አግመረከ ንስቲት ወለት ወለቶሙ ለነዳያት ጾረተከ ገሊላዊት ሐቀፈተከ። ነፍሳ ቀደስከ ፤ ወሥጋሃ አንጻሕከ አጽናዕከ ፤ ወኢደንገፀት ብከ።

በፈቃድህ ከሰማይ ወረድህ። የድንግል ማኅፀን ወሰነህ የድሆች ልጅ ትንሽ ብላቴና ገሊላዊት አቀፈችህ። ነፍስዋን አከበርህ ፤ ሥጋዋንም አነጻህ አጸናሃት ፤ ባንተ አልደነገጠችም።

You did come down from heaven by Your will. The womb of the virgin contained You. A little daughter, who was the daughter of the poor, carried You. The Galilean embraced You. You did sanctify Her soul, purify Her body and strengthen Her and she was not afraid of You.

በቤተልሔም ተወለድከ። ወከመ ሰብእ አስተርአይከ። እምኀበ ዮሐንስ ተጠመቀ ወዲበ ባሕር ሖርከ። ነፋሳተ ገሠፅከ ወነፍሳተ አሕዮከ።

በቤተ ልሔም ተወልደህ። እንደ ሰውም ታየህ። ከዮሐንስ ዘንድ ተጠምቀህ በባሕር ላይም ሄድህ። ነፋሳትን ገሠጽህ ነፍሳትንም አዳንህ።

You were born at Bethlehem and You did appear like a man. You were baptized by John; did walk on the sea; did rebuke the winds and quicken souls.

ሆሣዕና ምስለ አርዳኢከ ዖድከ። እምኃ ኅብስት በድማሬ መለኮትከ ወእም፪ኤ ዓሣ ብዙኃነ ሰብአ አጽገብከ።

ሆሣዕና ከደቀ መዛሙርትህ ጋራ ዞርህ። በጌትነትህ አንድነት ከአምስት ኅብስት ከሁለት ዓሣም ብዙ ሰዎች አጠገብክ።

You did join Your disciples in the celebration of Hosanna; did satisfy much people with five loaves and two fishes through the power of the divinity.

ኦ እግዚኦ ዘኢትደፈር ይሁዳ ደፈረከ። እምኀበ ሐና ተጽዕልከ። ወእምኀበ ቀያፋ ተመነንከ። ወእምኀበ ጲላጦስ ተትሕትከ ፤ ወምስለ ጊጉያን ተኈለቄ።

አቤቱ የማትደፈረውን ይሁዳ ደፈረህ። በሐና ዘንድ ተሰደብህ በቀያፋም ዘንድ ተናቅህ። በጲላጦስም ዘንድ ተዋረድህ ፤ ከወንበዴዎችም ጋራ ተቈጠርህ።

O Lord who cannot be affronted, You were affronted by Judas, You were reviled by Annas, disdained by Caiaphas, examined by Pilate and were numbered with the sinners.

ዓርብ አሜሃ አኩያን አይሁድ ዲበ ዕፅ ሰቀሉከ። በአምሳለ ዝንቱ ትእምርተ መስቀል ዘንገብሮ ንሕነ እንዘ ናነሥእ እደዊነ በዲበ ዛቲ ጠረጴዛ።

ያን ጊዜ ዓርብ ክፉዎች አይሁድ በዕንጨት ላይ ሰቀሉህ። እኛ በዚህች ጠረጴዛ ላይ እጆቻችንን አንሥተን በምናደርገው በዚህ ትምህርተ መስቀል አምሳል።

At the time on Friday the Evil Jews crucified You on the tree of the cross in the likeness of this sign of the cross which we make raising our hands over this tale.

ኦ እግዚኦ በእደ ገብር ተጸፋዕከ በበትረ ህለት ተኰራዕከ ፤ ወበኲናት ተረገዝከ ፤ ሐሞተ መሪረ ወብሒአ አስተዩከ ፤

አቤቱ በባሪያ እጅ ተጸፋህ ፤ በዘንግ በትርም (ራስህን) ተመታህ፤ በጦርም ተወጋህ ፤ የመረረ ሐሞትንና መጣጣን አጠጡህ ፤

O Lord, You were struck with the hands of a servant, beaten with sticks, pierced with a spear, and they caused You to drink bitter gall with vinegar.

እንዘ አምላክ አንተ ዘትክል ከሊአ ኢከላእከ ፤ ወተዐገሥከ እስከ ለሞት በጻሕከ ዘንተ ኵሎ በእንተ ፍቅረ ሰብእ ኮንከ።

አንተ መከልከል የሚቻልህ አምላክ ስትሆን አልከለከልህም። እስከ ሞት ደርሰህ ታገስህ ስለ ሰው ፍቅር ይህን ሁሉ ሆንህ።

While You were God, able to prevent them, You did not prevent them, You did become patient even to death; all this You did accept for the love of man.

እሙታን ተንሣእከ ፤ ወሙታነ አንሣእከ። ዔዋ ዔወውከ አምኃ ለአቡከ በልብሰተ ሥጋ ምስለ ኃይለ መለኮት ሰማያት ዐረገ ኀበ ዘትካት ህላዌከ።

ከሙታን ተለይተህ ተነሣህ ፤ ሙታንንም አነሣህ። ለአባትህ እጅ መንሻ ምርኮን ማረክህ ሥጋን በመልበስህ በመለኮት ኃይል ወደ ቀድሞ አነዋወርህ ወደ ሰማይ ዐረግህ።

You did rise from the dead and raise the dead, You did lead captivity captive to be presented to Your Father. Being clothed in flesh You did ascend to heaven, Your previous position, through the power of divinity.

ኦ እግዚኦ ሕዝበከ መሐር ኪዳነከ ተዘከር። በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ወይስሐቅ ቁልዔከ ፤ ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ ዘሰመይካሁ በስምከ።

አቤቱ ህዝብህን ማር ኪዳንህንም አስብ። ስለ ወዳጅህ ስለ አብርሃምና ስለ ወዳጅህ ስለ ይስሐቅ ፤ በስምህ ስለ ጠራኸው ስለ ቅዱስህ ስለ እስራኤልም።

O Lord, pity Your people and remember Your covenant for the sake of Your beloved Abraham, Your servant Isaac and Your Holy Israel whom You did call in Your name:

ኦ እግዚኦ በእንተ ነቢያት ቅዱሳን ወበእንተ ሐዋርያት ሰባክያን በእንተ ካህናት ሥዩማን ወበእንተ ሰማዕታት መዋዕያን ፤ ወበ እንተ ጻድቃን ቡሩካን ፤ ወበእንተ ደናግል ወመነኰሳት መስተዓግሣን።

አቤቱ ስለ ቅዱሳን ነቢያትና ስላስተማሩ ሐዋርያት ፤ ስለተሾሙ ካህናትና ድል ስለነሱ ሰማዕታት ፤ ስለ ተባረኩ ጻድቃን ፤ ስለ ደናግልና ስለ ትዕግስተኞች መነኰሳትም።

O Lord, for the sake of the Holy prophets, for the sake of the apostles, preachers, for the sake of the ordained priests, for the sake of the victorious martyrs, for the sake of the priest virgins and monks.

ኦ እግዚኦ በእንተ እሉ ፬ቱ ወንጌላውያን አምሳሊሆሙ ለእለ በሰማያት ሠረገላተ መናብርት። ማቴዎስ በአምሳለ ብእሲ ዘዜነወ ልደተከ እምዘርዐ ዳዊት በሥጋ እንዘ ይዌጥን እምበኵረ አበው ቀደምት።

አቤቱ በሰማያት ያሉ የመናብርት ሠረገላዎችን ስለሚመስሉ ስለ አራቱ ወንጌላዊያን። ከቀደሙ አባቶች በኵር ጀምሮ ከዳዊት ዘር በሥጋ መወለድህን የተናገረ ማቴዎስ በሰው የተመሰለ ነው።

O Lord, for the sake of these four Evangelists, the likeness of the chariots of the thrones in heaven: Matthew in the likeness of the man, who preached Your birth in flesh from the seed of David starting from the patriarch of the ancient fathers:

ማርቆስ በአምሳለ አንበሳ ዘይጥኅር ዘአንኀ ስብከተከ ለአለ በግብጽ በርትዕት ሃይማኖት።

በቀናች ሃይማኖት በግብፅ ላሉት ስብከትህን ያረዘመ ማርቆስ በሚያገሳ አንበሳ የተመሰለ ነው።

Mark in the likeness of a roaring lion, who propagated Your preaching to the Egyptians in the orthodox faith.

ሉቃስ በአምሳለ ላህም ዘሰበከ ትህትናከ ፤ ማእከለ አድግ ወላህም ሰኪቦተከ ፤ ወበአፅርቅት ጥብላሌከ ፤ ዘምስለ ድንግል እምከ በውስተ ጎል ህላዌከ።

ትሕትናህን ፤ በአህያና በላም መካከል መተኛትህን ፤ በጨርቅም መጠቅለልህን ፤ ከእናትህ ከድንግል ጋራ በበረት መኖርህን የተናገረ ሉቃስ በላህም የተመሰለ ነው።

Luke in the likeness of an ox, who preached Your humility, Your lying among asses and oxen, Your being wrapped in swaddling clothes and Your dwelling in a stable with the Virgin, Your mother.

ዮሐንስ በአምሳለ ንስር ዘልዑለ ይሠርር ወልዑለ ይጸርሕ ህሉና መለኮት ይፌክር ባሕረ ጥበባት ወዕመቀ ትንቢት። አንተ ውእቱ ዘኀረይካሁ እምአብያጺሁ ወአሠርገውኮ በቅድስና ወአቅነትኮ

ከፍ ብሎ የሚወጣ ከፍ ብሎም የሚጮህ የመለኮትን አናንዋር የሚተረጒም የጥበብ ባሕር የትንቢት ጥልቅ ዮሐንስ በንስር የተመሰለ ነው። ከወንድሞቹ ለይተህ የመረጥኸው አንተ ነህ።

John in the likeness of an eagle flying high and crying aloud, who interprets the Nature of the Deity, and who is the sea of wisdom and the depth of prophecy. It is You who did choose him from among his fellows

በዘዚአነ ቅናተ ድንግልና አምሳለ መላእክት ይኩን ዘአልቦቱ ጥልቀት ኦ እግዚኦ አይ አፍ ወአይ ከናፍር ወአይ ልሳን ዘይክል ወድሶ ልዕልናከ።

በቅድስና ያስጌጥኸው እንደ መላእክት ኃጢአት የሌለበት ይሆን ዘንድ አቤቱ ልዕልናህን ማመስገን የሚቻለው ምን አፍ ነው ምንስ ከንፈር ነው ምንስ አንደበት ነው።

and did decorate him with holiness and did gird him with Your girdle of virginity to be blameless like the angels. O Lord, what mouth, what lips, what tongue can praise Your exaltation?

ሕዝብ (People)

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ። ተዘከረነ እግዚኦ ኦ ሊቅነ በውስተ መንግሥትከ። ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ።

አቤቱ በመንግሥትህ አስበን። ሊቅ ሆይ አቤቱ በመንግሥትህ አስበን። አቤቱ በመንግሥትህ አስበን።

Remember us, Lord, in Your kingdom; remember us, Lord, Master, in Your kingdom; remember us, Lord, in Your kingdom,

በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ።

ቅዱስ በሚሆን በዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ ፈያታዊ ዘየማንን እንዳሰብከው አቤቱ በመንግሥትህ አስበን።

as You did remember the thief on the right hand when You were on the tree of the Holy Cross.

ካህን/priest/

ስብሐት ለከ ፤ አኰቴት ለመንግሥትከ ፤ ኃይል ለአቡከ ፤ ክብር ወስብሐት ምስለ እዘዝ ለመንፈስ ቅዱስ ዘእሩይ ምስሌከ ወምስለ ዘወለደከ ዘኢየሐጽጽ ለዓለመ ዓለም።

ለአንተ ምስጋና ፤ ለመንግሥትህም ምስጋና ፤ ለአባትህ ኃይል ፤ ክብርና ምስጋና ከጽንዕ ጋራ ከአንተና ከወለደህ ከአባትህ ጋራ ለሚተካከል ሕፀፅ ለሌለበት መንፈስ ቅዱስ ይገባል ለዘለዓለሙ።

Glory be to You thanksgiving to Your kingdom, power to Your Father, honor and glory with dominion to the Holy Spirit who is equal with and not inferior to You, and to Him who begat You, world without end.

ዲይቆን (Deacon)

አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት።

ቀስውስት እጆቻችሁን አንሡ።

Priests, raise up your hands.

ካህን (Priest)

ነሣእከ ኅብስተ በእደዊከ ቅዱሳት ከመ ተሀቦሙ ለአርዳኢከ ንጹሐን።

ቅዱሳት በሚሆኑ በእጆችህ ኅብስትን ያዝህ። ለንጹሐን ደቀ መዛሙርትህ ትሰጣቸው ዘንድ።

You did take bread in Your Holy hands to give to Your pure disciples.

ሕዝብ (People)

ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

ይህ እንደ ሆነ በእውነት እናምናለን።

We believe that this is He, truly we believe.

ካህን (Priest)

ዘአሜሃ ባረከ ዘምስለ በረከት ባርኮ ይእዜኒ ለዝንቱ ኅብስት። ዘአሜሃ ፈተትከ ዘምስለ አኰቴት ፈትቶ ይእዜኒ ለዝንቱ ኅብስት።

ከበረከት ጋራ ያን ጊዜ እንደ ባረክህ አሁንም ይህን ኅብስት ባርከው። ያን ጊዜ ከማመስገን ጋራ የቈርስህ አሁንም ይህን ኅብስት ቍረሰው።

O You Who did bless at that time, now bless this bread with blessing. O You Who did break at that time with thanksgiving, now break this bread.

ሕዝብ (People)

አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ። ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

አሜን አሜን እናምናለን ፤ እንታመናለን። ጌታችንና አምላክችን እናመሰግንሃለን ፤ ይህ እርሱ እንደሆነ በእውነት እናምናለን።

Amen amen amen: We believe and confess, we glorify Your, O our Lord and our God; that this is He we truly believe.

ካህን (Priest)

ወካዕበ ቶሳሕከ ጽዋዐ ወይን ምስለ ማይ ከመ ተሀቦሙ ለሐዋርያቲከ ንጹሓን። ዘአሜሃ ቀደስከ ቀድሶ ይእዜኒ ለዝንቱ ጽዋዕ። ዘአሜሃ መጦከ መጥዎ ይእዜኒ ለዝንቱ ጽዋዕ።

ዳግመኛም የወይኑን ጽዋ ከውኃ ጋራ ቀላቅለህ ለንጹሐን ሐዋርያትህ ትሰጣቸው ዘንድ። ያን ጊዜ ያከበርህ አሁንም ይህን ጽዋ አክብረው። ያን ጊዜ የሰጠህ አሁንም ይህን ጽዋ ስጠው።

You also mixed the cup of wine with water to give to Your pure disciples. O You Who sanctified at that time , now sanctify this cup. O You Who did grant at that time, now grant this cup.

ሕዝብ (People)

አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ። ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

አሜን አሜን እናምናለን ፤ እንታመናለን። ጌታችንና አምላካችን እናመሰግንሃለን ፤ ይህ እርሱ እንደሆነ በእውነት እናምናለን።

Amen amen amen: We believe and confess, we glorify You, O our Lord and our God; that this is He we truly believe.

ካህን (Priest)

ዘአሜሃ ደመርከ ደምሮ ይእዜኒ ለዝንቱ ኅብስት ምስለ ዝንቱ ጽዋዕ ይኩን ሥጋከ ወደመከ በዝየ።

ያን ጊዜ አንድ ያደረግህ ዛሬም ሥጋህን ደምህን ይሆን ዘንድ ይህን ኅብስት ከዚህ ጽዋ ጋራ አንድ አድርገው።

O You Who did unite at that time, now unite this bread with this cup to be Your body and Your blood.

ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ። ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ። ንሴብሐከ ወንትአምነከ። ንስእለከ ወናስተበቍአከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ።

አቤቱ ሞትህንና ቅድስት ትንሣኤህን እንናገራለን። ዕርገትህን ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን። እናመሰግንሃለን ፤ እናምንሃለንም። ጌታችንና አምላካችን ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም።

We proclaim Your death, Lord, and Your Holy resurrection; we believe in Your ascension and Your second advent. We glorify You, and confess You, we offer our prayer unto You and supplicate You, O our Lord and our God.

ዲያቆን (Deacon)

በሰማይ የሃሉ ልብክሙ

ልቡናችሁ በሰማይ ይኑር።

Let your heart be in heaven.

ሕዝብ (People)

በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ። (፫ ጊዜ )

አምላካችን ሆይ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን። (3 ጊዜ)

According to Your mercy, our God, and not according to our sins. (three times)

ካህን (Priest)

ይትቀፈጽ ኆኅተ ብርሃን ፤ ወይትረኀው አናቅጸ ስብሐት ፤ ወይትቀላዕ መንጦላዕት ዘቅድመ ገጹ ለአብ ፤ ወይረድ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር።

የብርሃን ደጅ ይገለጥ ፤ የምስጋና በርም ይከፈት። በአብ ፊት ያለ መጋረጃም ይገለጥ። የእግዚአብሔር በግዑ እነሆ ይውረድ።

Let the gate of light be opened and the doors of glory be unlocked and the curtain before the face of the Father be withdrawn, and let the Lamb of God

ወይነብር ዲበ ዝንቱ ማዕደ ክህነት ዘሥሩዕ በቅድሜየ ለገብርከ። ወይትፌኖ ሜሎስ ሰይፈ እሳት መደንግፅ ፤ ወያስተርኢ ዲበ ዝንቱ ኅብስት ወጽዋዐ። ከመ ይፌጽም ዘንተ አኰቴተ።

በእኔ በባርያህ ፊት በተዘጋጀ በዚህ በክህነት ማዕድ ላይ ይቀመጥ። የሚያስደነግጥ የእሳት ሰይፍ ሜሎስ ይላክ። በዚህ ኅብስትና ጽዋ ላይም ይገለጥ። ይህን አኰቴት ፍጹም ያደርግ ዘንድ።

descend and sit on this holy table prepared before me, Your servant. Let "Melos," the fearful sword of fire be sent and appear over this bread and cup: to fulfill this offering.

ሕዝብ (People)

አሜን እግዚኦ መሐረነ ፤ እግዚኦ መሐከነ ፤ እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ማረን ፤ አቤቱ ራራልን ፤ አቤቱ ይቅር በለን።

Amen; Lord have pity upon us, Lord spare us, Lord have mercy upon us.

ዲያቆን (Deacon)

በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ።

ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት ይሰጠን ዘንድ በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንማልደው።

With all the heart let us beseech the Lord our God that He grant unto us good communion of the Holy Spirit.

ሕዝብ (People)

በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም።

በፊት እንደነበረ ለዘለዓለሙ ለልጅ ልጁ ይኖራል።

As it was, is and shall be unto generations of generations, world without end.

ካህን (Priest)

ደሚረከ ተሀቦሙ ለኵሎሙ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ ይኩኖሙ ለሕይወት ወለሥርየተ ኃጢአት ለዓለመ ዓለም

ከእርሱ ለሚቀበሉ ሁሉ አንድ አድርገህ ስጣቸው። ለሕይወትና ለኃጢአት ማስተሥርያ ይሆናቸው ዘንድ ለዘለዓለሙ።

Grant it together unto all them that take of it, that it may be unto them for life and for remission of sin.

ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ፤ ወፈውሰነ ፤ በዝንቱ ቍርስፎራ ፤ ከመ ብከ ንሕየው ዘለዓለሙ ዓለም ፤ ወለዓለመ ዓለም።

የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ መሆንን ስጠን። በዚሁም በሥጋው በደሙ አድነን። ለዓለሙ ሁሉ በምትሆን በአንተ ለዘለዓለሙ ሕያው እንሆን ዘንድ።

Grant us to be united through Your Holy Spirit, and heal us by this oblation that we may live in You for ever.

ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር። ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር። ወይትባረክ ፤ ስመ ስብሐቲሁ ፤ ለይኩን ፤ ለይኩን ፤ ቡሩከ ለይኩን። ፈኑ ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ።

የእግዚአብሔር ስሙ ምስጉን ነው። በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውም ምስጉን ነው ፤ ጌትነቱም ይመስገን ይሁን ይመስገን ይሁን። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን ላክልን።

Blessed be the name of the Lord, and blessed be He that cometh in the name of the Lord, and Let the name of His Glory be blessed. So be it, so be it, so be it blessed. Send the grace of the Holy Spirit upon us.

## ዲያቆን (Deacon)

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

## ሕዝብ (People)

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

ካህን (Priest)

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with your spirit.

# ጸሎተ ፈትቶ

## የመፈተት ጸሎት

## " Prayer Of Fraction"

ካህን (Priest)

ወካዕበ ናስተበቍዕ ኦ መፍቀሬ ሰብእ ወንገኒ ለከ በኵሉ ወበውስተ ኵሉ ወኢለፎ እምኔነ ኢይስክየነ ሥጋከ ወደምከ በእንተ ዘኢኮነ ንጹሐ ነፍስነ ወሥጋነ።

ዳግመኛ ሰውን የምትወድ ሆይ እንማልድሃለን። በሁሉ በሁሉም ዘንድ እንገዛልሃለን። ነፍሳችንና ሥጋችን ንጹሕ ስላልሆነ ሥጋህና ደምህ ከእኛ ወገን አንዱን እንኳን አይክሰሰን።

Again we supplicate You, O Lover of man, and we serve You in all things and for all things, and let not Your body and blood accuse anyone of us because of the impurity of our soul and body.

በከመ ተንጦልዐ ሥጋከ ዲበ ዕፀ መስቀል ላዕለ ወታሕተ ፤ የማነ ወጸጋመ በከመ መዓዝኒሃ ለምድር ለሕይወተ ኵሉ ዓለም። ወከማሁ ንሕነኒ ንእኅዝ ወናሬኢ እምዝንቱ ኀብስት ኪያሁ

ሥጋህ ለዓለም ሁሉ ሕይወት ለመሆን እንደ ምድር ማዕዘን ወደላይና ወደ ታች ወደ ቀኝና ወደ ግራ በዕፀ መስቀል ላይ እንደተዘረጋ እኛም እንዲሁ ከዚህ ኅብስት ይህን ትእምርተ

As Your body was stretched on the cross up and down, right and left, like the comers of the earth, for the life of all the world, so also we hold and see this sign of

ትዕምርተ መስቀል። ወለኵሉ ዘይነሥእ እምኔሁ ኢይኩኖ ለቅስት ወኢለኀጕል። ሚኬ እግዚኦ ዘተአምር እበዲሁ ለሰብእ

መስቀል ይዘን እናሳያለን። ከርሱ ለሚቀበለውም ሁሉ ለወቀሳ ወይም ለጥፋት አይሁንበት። አቤቱ የሰውን ስንፍናውን የምታውቅ ምን ያህል ነው።

the cross on this bread; and let it not be for accusation and destruction to anyone who partakes of it. O Lord, how clearly You knows the foolishness of man,

አልቦ ዘተረክበ ዘኢኀደጎ ለሥርዓትከ እም ቀዳሚ አዳም እስከ ይእዜ መዋዕል። እስመ አንተ ውእቱ ርሑቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት ወጻድቅ እግዚአብሔር አምላክነ።

ከቀደመው አዳም ጀምሮ እስከ ዛሬ ዘመን ድረስ ሥርዓትህን ሳያፈርስ የተገኘ የለም። መዓትህ የራቀ ፤ ምሕረትህ የበዛ እውነተኛም እግዚአብሔር አምላካችን አንተ ነህ እኮ።

none has been found who has not transgressed Your commandment from the first Adam till the present days, because You, Lord our God, are far from anger, plenteous in mercy, and righteous.

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ።

ጸልዩ።

You pray.

ሕዝብ (People)

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ። ትምጻእ መንግሥትከ። ወይኩን ፈቃድከ። በከመ በሰማይ ፤ ከማሁ በምድር።

አባታችን ሆይ ፤ በሰማያት የምትኖር ፤ ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ። ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን።

Our Father who are in heaven, hallowed be Your name, Your kingdom come, Your will be done on earth as it is in heaven;

ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም። ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ፤ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ።

የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ። በደላችንን ይቅር በለን ፤ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል።

give us this day our daily bread, and forgive us our trespasses as we forgive them that trespass against us,

ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ፤ አላ አድኅነነ። ወባልሐነ እምኲሉ እኩይ። እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።

አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ፤ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ። መንግሥት ያንተ ናትና ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።

and lead us not into temptation but deliver us and rescue us from all evil; for Yours is the kingdom, the power and the glory for ever and ever.

ካህን (Priest)

እወ እጼሊ በከመ ቀዳሚ ሥርዓት ዘተአዘዘ እምኀበ እግዚአብሔር ከመ ይጸልዩ በእንተ ሕዝብከ ወርስትከ ሙሴ ወአሮን ካህናት።

ካህናቱ ሙሴና አሮን ስለ ሕዝብህና ስለ ርስትህ ይጸልዩ ዘንድ ከእግዚአብሔር እንደታዘዘው እንደ ቀደመው ሥርዓት በእውነት እጸልያለሁ።

Truly, I offer prayer according to the first order given by God that Moses and Aaron, the priests, might pray on behalf of Your people and inheritance.

ወከማሆሙ እጼሊ ኀቤከ በእንተ ሕዝብከ ወርስትከ እለ መጽኡ ውስተ ቤተ ክርስቲያንከ ካህናት ወዲያቆናት ወእለ በአፍአ ሕዝብከ ወርስትከ።

እንደነርሱ ወደ አንተ እጸልያለሁ። ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ስለ መጡት ካህናትና ዲያቆናት በውጭም ስላሉ ስለ ሕዝብህና ስለ ርስትህ።

Like them I pray unto You on behalf of Your people and inheritance who have come into Your church, priests and deacons, and on behalf of Your people and inheritance who are outside.

ወለእመቦ እምዝየ እምካህናት ወእምህየኒ እምሕዝባውያን ዘርሕቀ ሕሊናሁ እምኔከ ረሲ ይሠጠም ኀበ ዘዚአከ ፈቃድ።

ከዚህ ከካህናት ወገን ከወዲያም ከሕዝባውያን ወገን አሳቡ ከአንተ የራቀ ቢኖር ወደ አንተ ፈቃድ እንዲሠጥም አድርገው።

If there is here anyone of the priests or the people whose mind is far from You, let Your will overwhelm him.

በከመ አስጋባእካ ለዛቲ ኅብስት እንዘ ዝሩት ይእቲ ማእከለ አድባር ወአውግር ወውስተ ገዳም ወቈላት ወተጋቢኣ ኮነት አሐተ ጽርስፎራ።

ይህችን ኅብስት በተራራና በኮረብታ ፤ በበረሃና በቈላ የተበተነች ስትሆን እንደ ሰበሰብሃት ተሰብስባም አንድ ኅብስት እንደ ሆነች።

As Your have gathered this bread which had been scattered on the mountains and the little hills, in the forests and the valleys, and being gathered together, it became one bread for oblation.

ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም። ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም።

የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮች የሚሆኑ የመላእክት ሠራዊት በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ።

The hosts of the angels of the Savior of the world, stand before the Savior of the world and encircle the Savior of the world.

ወይኬልልዎ መላእክት ዘእሳት መንጦላዕቱ ለመድኃኔ ዓለም። በእንተ ሥጋሁ ቅዱስ ወበእንተ ደሙ ክቡር።

መጋረጃው እሳት የሆነ መድኃኔዓለምን መላእክት ያመሰግኑታል። ስለ ቅዱስ ሥጋውና ደሙ።

and the angels encircle the Saviour of the world, Whose curtain is fire for the sake of His Holy body and His precious blood.

ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ከመ ንባእ ውስተ ጽርሐ ቅድሳቱ ለመድኃኔዓለም። አሚነነ ኪያሁ ተወኪለነ ቦቱ ነሐዩ።

እርሱን አምነን ወደ መድኃኔ ዓለም መመስገኛ አዳራሽ እንገባ ዘንድ ከፊቱ እንድረስ። በእርሱ አምነን እንድናለን።

Let us draw near before His face to enter into the house of the holiness of the Saviour of the world and to live believing in Him and trusting in Him.

ንፍቅ ዲያቆን (Ass't Deacon)

አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት።

መኳንንት ደጆችን ክፈቱ።

Open the gates, princes.

ዲያቆን Deacon

እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ።

የቆማችሁ ሰዎች ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ።

You, who are standing, bow your heads.

ካህን (Priest)

እወ ናቴሕት ወንገኒ ለከ ዘትነብር ውስተ ጽርሕከ አርያም ኀበ ኢይበጽሖ ሕሊና ሰብእ ወኢዘመላእክት አእምሮ።

በእውነት ዝቅ ዝቅ እናደርጋለን። የሰው ሕሊና ፣ የመላእክትም አእምሮ በማይደርስበት በልዕልና አዳራሽህ ለምትኖር ለአንተም እንገዛለን።

Truly we bow and serve You Who sits in the highest heaven which neither the mind of man nor the knowledge of angels can reach.

ናስተበቍዕ ኂሩተ ሠናያቲከ በእንተ ሕዝብከ ወርስትከ እለ መጽኡ ውስተ ቤተ መቅደስከ በዛቲ ዕለት ካህናት ወዲያቆናት እለ አድነኑ ርእሶሙ ቅድመ ዕበየ ልዕልናከ ከመ ይንሥኡ

የበጎነትህን ቸርነት እንማልዳለን ፤ ስለ ሕዝብህና ስለ ርስትህ በዚህች ዕለት ወደ ቤተ መቅደስህ ስለመጡ። መጠኔና አገባቤ ሳይሆን ችግረኛም ሳለሁ በጸጋህ በጠራኸኝ በእኔ በባርያህ እጅ

We supplicate the kindness of Your goodness on behalf of Your people and Your inheritance who have today come unto Your sanctuary, the priests and deacons who have bowed their heads before Your majesty,

ሥጋከ ወደመከ በእደ ዚአየ ዘጸዋዕከኒ በጸጋ ዚአከ ዘኢመጠንየ ወኢድልወትየ ወምስኪነትየኒ ሊተ ለገብርከ።

ሥጋህንና ደምህን ይቀበሉ ዘንድ በልዕልናህ ገናንነት ፊት ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ ስላደረጉ ካህናትና ዲያቆናት።

to receive Your body and Your blood by the hand of me, Your servant, whom You have called through Your grace, though unfit, unworthy and pitiable.

ዝኬ ውእቱ ኪዳነ ቃልከ ዘታወሥኦሙ ለካህናት እንዘ ትብል ጼው ለምድር። ዘትቤሎሙ ለካህናት ብርሃኑ ለዓለም። ዘትቤሎሙ ለካህናት አዕይንተ ቤተ እግዚአብሔር።

ለካህናት የነገርሃቸው የቃልህ ኪዳን ይህ ነው። የምድር ጨው ናችሁ ብለህ። ካህናትን የዓለሙ ብርሃን ናችሁ ያልሃቸው። ካህናትን የቤተ እግዚአብሔር ዓይኖች ናቸው ያልሃቸው።

This is the covenant of Your word which You uttered to the priests saying, “you are the salt of the earth;" You said to the priests, “you are the light of the world; You said to the priests, “you are the eyes of the house of God."

ዘትቤሎሙ ለካህናት ማኀቶተ ቤተ ክርስቲያን። ዘትቤሎሙ ለካህናት አምሳለ መላእክት። ነዓኬ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ትባርክ ሕዝበከ ወርስተከ ለዓለም ዓለም።

ካህናትን የቤተ ክርስቲያን መብራት ናችሁ ያልሃቸው። ካህናትን የመላእክት ምሳሌ ናችሁ ያልሃቸው። ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሕዝብህንና ርስትህን ለዘላለሙ ትባርክ ዘንድ ና።

You said to the priests, “you are the candles of the church;" You said to the priests, “you are the likeness of the angels." Come, O High Priest Jesus Christ, to bless Your people and Your inheritance, unto the ages of ages.

ዲያቆን Deacon

ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት።

Worship the Lord with fear.

ሕዝብ (People)

ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ።

አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን እናመሰግንሃለንም።

Before You, Lord, we worship, and we do glorify You.

ጸሎተ ንስሓ።

የንስሓ ጸሎት።

"Prayer of Pentence”

እግዚእ እግዚኦ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አንተ ውእቱ ዘትፌውስ ቍስለ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ እስመ አንተ ትቤ በአፈ ዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፤

አቤቱ ዓለሙን ሁሉ የያዝህ ጌታችን እግዚአብሔር አብ የነፍሳችንንና የሥጋችንን የደመ ነፍሳችንንም ቍስል የምታድን አንተ ነህ ባንድ ልጅህ በጌታችንና በመድኃታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አፍ ተናግረሃልና፤

O Lord God, the Father almighty, it is You that heal the wounds of our soul and our spirit, Because You have said, with the mouth of your only-begotten Son, our Lord and our God and our Savior Jesus Christ,

ዘይቤሎ ለአቡነ ጴጥሮስ አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ ቅድስት ወኢክልዋ አናቅጸ ሲኦል አማስኖታ ወአንቀልቅሎታ

ለአባታችን ለጴጥሮስ እንዲህ ብሎ የተናገረውን "አንተ አለት መሠረት ነህ በዚችም አለት መሠረት ላይ ክብርት ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ የሲኦልም ደጆች ሊያጠፏትና ሊያነዋውጧት አይችሉም።

that which He said to our father Peter, "you are a rock I will build My Holy Church and the gates of hell shall not prevail against it,

ወለከ እሁበከ መራኁተ ዘመንግሥተ ሰማያት ዘአሠርከ በምድር ይኩን እሡረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕከ በምድር ይኩን ፍቱሐ በሰማያት።

ለአንተም የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሠርኸው በሰማይ የታሠረ ይሆን ዘንድ በምድር የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆን ዘንድ።”

and unto you I give the keys of the Kingdom of heaven; what you have bound on earth shall be bound in heaven, and what you have loosed on earth shall be loosed in heaven:”

ወይኩኑ ፍቱሓነ ወግዑዛነ ኵሎሙ አግብርቲከ በበአስማቲሆሙ በአፉሁ ለመንፈስ ቅዱስ ወበአፈ ዚአየኒ አነ ገብርከ እገሌ ኃጥእ ወአባሲ እመሂ በአእምሮ አው በኢያእምሮ ገብሩ፡፡

ወንዶችም ሴቶችም ባሮችህ ሁሉ በየስማቸው የተፈቱ ነጻም የወጡ ይሁኑ በመንፈስ ቅዱስ ቃል ኃጥእ በደለኛ በምሆን በኔም በባሪያህ ቃል፤በማወቅ ወይም ባለማወቅ ቢሠሩ::

Let us all Your servants and Your handmaids, according to their several names, be absolved and set free out of the mouth of the Holy Spirit, and out of the mouth of me also Your sinful and guilty servant….. whether they have wrought wittingly or unwittingly

ወዓዲ ለትሕትና ዚአየኒ አነ ገብርከ ኃጥእ ወአባሲ ፍትሐኒ ወይኩኑ ፍቱሓነ ወግዑዛነ እምአፈ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወእምአፈ ዚአየኒ አነ ገብርከ ኃጥእ ወአባሲ።

ዳግመኛም ኃጥእ በደለኛም የምሆን እኔንም ወራዳነቴን አይተህ ፍታኝ ልዩ ሦስት በሚሆኑ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ቃል የተፈቱ ነጻ የወጡ ይሁኑ ኃጥእ በደለኛ በምሆን በኔም በባሪያህ ቃል።

And absolve them and set them free out of the mouth of the Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit, and out of the mouth of me Your sinful and unrighteous servant.

ኦ መሐሪ ወመስተሣህል ወመፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር አምላክነ ዘታአትት ኃጢአተ ዓለም ተወከፍ ንስሓሆሙ ለአግብርቲከ ወለአእማቲከ ወአሥርቅ ላዕሌሆሙ።

መሐሪ ይቅር ባይ ሰውንም የምትወድ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ የዓለሙን ኃጢአት የምታቅ የወንዶቹንና የሴቶቹን ባሮችህን ንስሓቸውን ተቀበል።

O pitiful, merciful and lover of man, Lord our God, that take away the sin of the world, accept the penitence of Your servants and Your handmaids,

ብርሃነ ሕይወት ዘለዓለም ወሥረይ ሎሙ እግዚኦ ኵሎ ኃጢአቶሙ እስመ ኄር አንተ ወመፍቀሬ ሰብእ ኦ እግዚአብሔር አምላክነ ወመስተሣህል

የዘላለም ደኅንነት የሚሆን ብርሃንንም ግለጽላቸው፤ አቤቱ ኃጢአታቸውንም ሁሉ ይቅር በላቸው ቸር ሰውንም የምትወድ አንተ ነህና ይቅር ባይ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ

and shine upon them with the light of ever lasting life, and forgive them, Lord, all their sins; for You are good and the lover of man.

ርኁቀ መዓት ወብዙኃ ምሕረት ወጻድቅ ሥረይ ሊተ ኃጢአትየወለኵሎሙ አግብርቲከ ወአእማቲከ አድኅኖሙ እምኵሉ አበሳ ወመርገም።

መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ እውነተኛም የምትሆን የኔን ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ ወንዶችና ሴቶችን ባሮችህን ሁሉ ከበደልም ከመርገምም ሁሉ አድናቸው፡፡

O Lord our God, merciful, slow to anger, plenteous in mercy and righteous, forgive my sins; And deliver all Your servants and hand-maids from all transgression and curse

ለእመ አበስነ ለከ እግዚኦ እመሂ በቃልነ ወእመሂ በምግባርነ ወእመሂ በሕሊናነ ኅድግ ወሥረይ ወአናሕሲ ወተሣሃል እስመ ኄር አንተ ወመፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር አምላክነ።

በቃላችንም ቢሆን በሥራችንም ቢሆን በአሳባችንም ቢሆን አቤቱ አንተን ብንበድል ተውልን አስተሥርይ አቃልልን ይቅርም በለን አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ አንተ ቸር ሰውን ወዳጅ ነህና።

If we have transgressed against you, Lord, whether in our word or in our deed or in our thought, release, remit, pardon and have mercy, for You are good and the lover of man, Lord our God.

ኦ እግዚኦ ረሥየነ ፍቱሓነ ወግዑዛነ ወለኵሎሙ ሕዝብከ ፍትሖሙ ወሊተኒ ለኃጥእ ገብርከ ፍትሐኒ ተዘከሮ እግዚኦ ለአብ ክቡር ሊቃነ ጳጳሳት አባ ........

አቤቱ የተፈታን ነፃም የወጣን አድርገን ወገኖችህንም ሁሉ ፍታቸው፤ ኃጥእ የምሆን እኔንም ባርያህን ፍታኝ ክቡር የሚሆን የጳጳሳቱን አለቃ አባ ........ አስበው፤

O Lord, absolve us and set us free, and absolve all Your people, and absolve me Your sinful servant. Remember, Lord, the honorable father, our Patriarch Abba .......

ወብፁዕ ጳጳስነ አባ ........አምላክነ ዐቂበ ዕቀቦሙ ለነ ዓመታተ ብዙኀ ወመዋዕለ ነዊኀ በጽድቅ ወበሰላም። ተዘከራ እግዚኦ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ወዕቀባ በጽድቅ ወበሰላም አግርር ፀራ ወጸላዕታ ፍጡነ።

ብፁዕ የሚሆን አባ....... አስበው። አምላካችን ሆይ ለብዙ ዘመናት ለረጅም ወራት በእውነትና በሰላም መጠበቅን ጠብቅልን አቤቱ ሀገራችንን ኢትዮጵያን አስባት የሚጣሏትንና ጠላቶቿን ፈጥነህ አስገዛላት።

and the blessed Archbishop Abba ...... Our God, keep them for us many years and length of days in righteousness and peace. Remember, O Lord, our country Ethiopia. Subdue her adversaries and her enemies under her feet speedily.

ተዘከር እግዚኦ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳተ ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት አናጕንስጢሳውያነ ወመዘምራነ ደናግለ ወመነኰሳተ ዕቤራተ ወእጓለ ማውታ እደ ወአንስተ አእሩገ ወሕፃናተ

የጳጳሳቱን አለቆች ጳጳሳቱንና ኤጲስ ቆሳቱን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱንአንባቢዎችንና መዘምራኑን ደናግሉንና መነኰሳቱን ባልቴቶቹንና አባት እናት የሞቱባቸውን ወንዶቹንና ሴቶቹን ሽማግሌዎቹንና ልጆቹን

Remember, Lord, the patriarchs, archbishops, bishops, priests and deacons, anagunsts(readers) and singers, virgins and monks, widows and orphans, men and women, aged and children;

ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን እለ ሀለዉ ወቆሙ ውስተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አጽንዖሙ በሃይማኖተ ክርስቶስ ፤ ተዘከሮሙ እግዚኦ ለኵሎሙ አበዊነ ወአኀዊነ ወአኃቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት።

ክብርት በምትሆን በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያሉትን የቆሙትንም የክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ክርስቶስን በማመን አጽናቸው አቤቱ በቀናች ሃይማኖት ሁነው የሞቱትንና ያረፉትን አባቶቻችንንና ወንድሞቻችንን እኅቶቻችንን ሁሉ አስባቸው።

and all Christian people that are standing in this Holy church; strengthen them in the faith of Christ. Remember, Lord, all our fathers, brothers and sisters that are asleep and resting in the orthodox faith,

ወደምር ነፍሳቲሆሙ ውስተ ሕፅነ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ወለነኒ አድኅነነ እምኵሉ አበሳ ወመረወገም ወእምኵሉ ጌጋይ ወእምኵሉ ክሕደት ወእምኵሉ መሐላ በሐሰት ወእምኵሉ ግዘት።

ነፍሶቻቸውንም በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብም አጠገብ አኑር እኛን ከኃጢአት ሁሉ ከመርገምም ከበደልም ሁሉ ከክህደትም ሁሉ በሐሰትም ከመማል ሁሉ ከመገዘትም ሁሉ አድነን።

and lay their souls in the bosom of Abraham, Isaac and Jacob. and as for us, deliver us from every transgression and curse and from all wickedness and from all rebellion and from all false swearing and from all anathemas

ወእምተደምሮ በዕልወት ወርኵስ ምስለ ዓላውያን ወአረማውያን ጸግወነ እንዚኦ ጥበበ ወኃይለ ልበ ወልቡና ወአእምሮ፤

በክህደትና በርኵሰት ከዓላማውያንና ከአረማውያን ጋራ አንድ ከመሆን አድነን አቤቱ ጥበብንና ኃይልን ልብንና ልቦናን ዕውቀትንም ስጠን።

and from all perjury and from mingling with heretics and gentiles in error and defilement. Grant us, Lord, wisdom and power and reason and understanding and knowledge

ከመ ንርሐቅ ወንጕየይ እንከ እስከ ለዝሉፉ እምኵሉ ምግባራቲሁ ለሰይጣን ዘያሜክር ሀበነ እግዚኦ ንግበር ፈቃደከ ወሥምረተከ በኵሉ ጊዜ ወጸሐፍ አስማቲነ ውስተ መጽሐፈ ሕይወት በመንግሥተ ሰማያት

እንግዲህ ከሚፈታተነን ከሠይጣን ሥራ ሁሉ እስከ ዘላለሙ እንርቅ እንሸሽም ዘንድ አቤቱ ሁል ጊዜ ፈቃድህን ውድህንም እንሠራ ዘንድ ስጠን ስማችንንም በመንግሥተ ሰማያት በሕይወት መጽሐፍ

that we may depart and flee for evermore from all works of Satan the tempter. Grant us, Lord, to do Your will and Your good pleasure at all times, and write our names in the book of life in the kingdom of heaven

ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ከቅዱሳንና ከሰማዕታት ሁሉ ጋራ ጻፍ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

with all saints and martyrs, through Jesus Christ our Lord, through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን (Deacon)

ነጽር።

አስተውል።

Give heed.

ካህን

ቅድሳት ለቅዱሳን።

ቅድሳት ለቅዱሳን።

Holy things for the Holy.

## ሕዝብ (People)

አሐዱ አብ ቅዱስ።
አሐዱ ወልድ ቅዱስ።
አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

አንዱ ቅዱስ አብ ነው።
አንዱ ቅዱስ ወልድ ነው።
አንዱ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ነው።

One is the Holy Father,
one is the Holy Son,
one is the Holy Spirit.

**ካህን (Priest)**

እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ።

ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

The Lord be with you all.

**ሕዝብ (People)**

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

*ካህኑን በመከተል ደግመን እንበል። / Repeat after the priest.*

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

Lord have compassion upon us O! Christ!

ዲያቆን (Deacon)

እለ ውስተ ንስሓ ሀለውክሙ አትሕቱ ርእሰክሙ።

በንስሓ ወስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ።

You, that are penitent, bow your heads.

ካህን/priest/

እግዚአብሔር አምላክነ ነጽር ዲበ ሕዝበከ እለ ውስተ ንስሐ ሀለዉ ወተሣሃሎሙ በከመ ዕበየ ሣህልከ ወበከመ ብዝኀ ምሕረትከ ደምስስ አበሳሆሙ ክድኖሙ ወዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ።

አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በንስሐ ውስጥ ስላሉት ወገኖችህ ተመልከት እንደ ይቅርታህም ብዛት ይቅር በላቸው እንደ ቸርነትህም ብዛት በደላቸውን አጥፋላቸው ከክፉ ነገርም ሁሉ ጠብቃቸው ሰውራቸውም።

Lord our God, look upon Your people that are penitent, and according to Your great mercy have mercy upon them and according to the multitude of Your compassion blot out their iniquity, cover them and keep them from all evil.

ወቤዙ ነፍሳቲሆሙ በሰላም አኀጺረከ ዘቀዳሚ ምግባሮሙ ደምሮሙ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት በሞገሱ ወበምሕረቱ ለዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

የቀደመ ሥራቸውን ይቅር ብለህ በሰላም ነፍሳቸውን አድን ከቅድስት ቤተ ክርስትያንህ አንድ አድርጋቸው ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው በአንድ ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ ፤

And redeem their souls in peace, forgive their former works. Join them with Your Holy church: through the grace and compassion of Your only-begotten Son our Lord and our God and our Savior Jesus Christ,

ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በይቅርታውና በምሕረቱ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ጨምራቸው በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

through whom to You with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

## ዲያቆን (Deacon)

ተንሥኡ ለጸሎት።

ለጸሎት ተነሡ።

Stand up for prayer.

## ሕዝብ (People)

እግዚኦ ተሣሃለነ።

አቤቱ ይቅር በለን።

Lord have mercy upon us.

ካህን (Priest)

ሰላም ለኵልክሙ።

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

Peace be unto you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ካህን (Priest)

ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን ዝውእቱ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ በአሚን።

በእውነት ክቡር የሚሆን የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ይህ ነው። አምነው ከእርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተሥረያም ሊሆን የሚሰጥ።

This is the true holy body of our Lord, God, and Saviour Jesus Christ, that is given for life, salvation, remission of sin unto them that receive of it in faith.

ሕዝብ / People

አሜን

Amen.

ካህን (Priest)

ደም ክቡር ዘበአማን ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይትሜጠው እምኔሁ በአሚን።

በእውነት አምነው ከእርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት ÷ የኃጢአት ማሥተሪያም ሊሆን የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ ነው።

This is the true precious blood of our Lord, God, and Saviour Jesus Christ, which is given for life, salvation, and remission of sins into those who drink of it in faith.

ሕዝብ / People

አሜን

Amen.

(Priest) Priest)

እስመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን።

በእውነት የአምላካችን የአማኑኤል ሥጋውና ደሙ ይህ ነው።

For this is the body and blood of Emmanuel our very God.

ሕዝብ People

አሜን

Amen.

ካህን (Priest)

አአምን አአምን አአምን ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ።

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ እስከ መጨረሻይቱም እስትንፋስ እታመናለሁ።

I believe, I believe, I believe and I confess, unto my last breath,

ከመዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ እምእግዝእትነ ኵልነ ቅድስ ድንግል በክልኤ ማርያም።

በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ይህ እንደሆነ።

that this is the body and blood of our Lord, God, and Saviour Jesus Christ, which He took from the Lady of us all, the holy Mary of twofold virginity,

ወረሰዮ አሐደ ምስለ መለኮቱ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ ወኮነ ሰማዕተ በስምዐ ሠናይ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ወመጠዎ በእንቲአነ ወበእንተ ሕይወት ኵልነ።

ያለመቀላቀልና ያለትድምርት ፥ ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋራ አንድ ያደረገው በጴንጤናዊ ጲላጦስም ዘመን በአማረ ምስክርነት ምስክር የሆነ ስለ እኛና ስለ ሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው።

and made it one with His godhead without mixture or confusion, without division or alteration; and He verily confessed with a good testimony in the days of Pontius Pilate, and this body He gave up for our sakes and for the life of us all.

ሕዝብ People

አሜን

Amen.

ካህን (Priest)

አአምን አአምን አአምን ወእትአመን ከመ ኢፈልጠ መለኮቱ እምትስብእቱ ኢአሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅጽበት ዓይን

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ መለኮቱ ከሰውነቱ አንዲት ሰዓት እንኳን እንደ ዓይን ቅጽበት እንኳ እንዳልተለየም እታመናለሁ።

I believe, I believe, I believe and I confess that His godhead was not separated from His manhood, not for an hour nor for the twinkling of an eye,

አላ መጠዎ በእንቲአነ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን።

ስለ እኛ ሰጠው እንጂ ለሕይወትና ለመድኃኒት ለኃጢአትም ማስተሥረያ ሊሆን አምነው ለሚቀበሉ ሰዎች ስለ እኛ አሳልፎ ሰጠው እንጂ።

but He gave it up for our sakes for life, salvation, and remission of sin unto them that partake of it in faith.

ሕዝብ / People

አሜን

Amen.

ካህን (Priest)

አአምን አአምን አአምን ወእትአመን ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ይህ እንደሆነ እታመናለሁ።

I believe, I believe, I believe and I confess that this is the body and blood of our Lord, God, and Saviour Jesus Christ, and that to Him are rightly due honour and

ዝውእቱ ዘሎቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወስግደት ምስለ አቡሁ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

ክብርና ምስጋና ስግደትም ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባቱ ጋራ የሚገባው ይህ ነው ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

glory and adoration with His kind heavenly Father and the Holy Spirit, the life-giver, both now and ever and unto the ages of ages. Amen.

ቁርባኑን ከመቀበል አስቀድሞ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉ ሁሉ የሚከተለውን ይበሉ።

Before receiving the Holy communion, all communicant shall say the following.

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አኮ ዘይደልወኒ ትባእ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ ርኵስት እስመ አነ አስተቈጣዕኩከ፤

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ፣ ርኵስት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለም እኔ አሳዝኜሃለሁና፤

O my Lord Jesus Christ, I am not worthy for You to come under the roof of my polluted house, for I have provoked You to wrath,

ወገበርኩ እኩየ በቅድሜከ ወአርኰስኩ ነፍስየ ወሥጋየ ዘፈጠርከ በአርአያከ ወበአምሳሊከ በዐሊወ ትእዛዝከ ፤ ወአ ልብየ ምግባር ወኢ.ምንትኒ።

በፊትህም ክፉ ሥራ ሠርቻለሁና ፤ በአርአያህና በአምሳልህ የፈጠርኸው ሥጋዬንና ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌያለሁና ፤ ሥራም ምንም ምን የለኝምና።

and have done evil in Your sight, and through the transgression of Your commandment have polluted my soul and my body which You did create after Your image and Your likeness, and in me dwells no good thing.

ወባሕቱ በእንተ ተኬንዎትከ ወበእንተ ትስብእትከ በእንተ መድኃኒትየ ወበእንተ መስቀልከ ክቡር ወበእንተ ሞትከ ማሕየዊት፤

ነገር ግን ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለ መሆንህ ፣ ስለ ክቡር መስቀልህም ፣ ማሕየዊት ስለምትሆን ስለ ሞትህ፣

But for the sake of Your contrivance and Your incarnation for my salvation, for the sake of Your precious cross and Your life-giving death,.

ወበእንተ ትንሣኤከ በሣልስት ዕለት እስእለከ ወአስተበቍዐከ ኦ እግዚእየ ከመ ታንጽሐኒ እምኲሉ አበሳ ወመርገም ወእምኲሉ ኃጢአት ወርኵስ።

በሦስተኛው ቀን ስለ መነሣትህም ጌታዬ ሆይ ከበደልና ከመርገም ሁሉ ከኃጢአ ትና ከርኵሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምን ሃለሁ፣ እማልድሃለሁም።

for the sake of Your resurrection on the third day, I pray You and beseech You, O my Lord, that You would purge me from all guilt and curse and from all sin and defilement

ወሶበ እትሜጦዎ ለምሥጢረ ቅድሳቲከ ኢይኩነኒ ለቅስት ወኢለኰነኔ ፤ አላ መሐረኒ ወተሣሃለኒ ፤ ወሀበኒ ቦቱ ሥርየተ ኃጢአትየ ወሕይወተ ነፍስየ፤

የቅድስናህንም ምሥጢር በተቀበልሁት ጊዜ ለወቀሳ ለመፈራረጃ አይሁንብኝ ፤ ማረኝ ይቅርም በለኝ እንጂ፣ የዓለም ሕይወት ሆይ፣ በርሱ የኃጢአቴን ሥርየት የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ፣

When I received Your holy mystery let it not be unto me for judgment nor for condemnation, but have compassion upon me and have mercy upon me; and through it grant me remission of my sin and life for my soul,

ኦ ሕይወተ ዓለም በስእለታ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በ፪ኤ ማርያም ወላዲትከ ወዮሐንስ መጥምቅ ፤ ወበጸሎተ ኵሎሙ ቅዱሳን መላእክት ወኵሎሙ ሰማዕት ወጻድቃን መስተጋድላን

በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ማርያም በመጥምቁ በዮሐንስም አማላጅነት ክቡራን በሚሆኑ በመላእክትም በሰማዕታትና ለበጎ ነገር በሚጋደሉ

O life of the world, through the petition of our Lady, the Holy Mary of twofold virginity Your mother, and of John the Baptist, and through the prayer of all the Holy angels

ለሠናይ እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

በጻድቃንም ሁሉ ጸሎት እስከ ዘለዓለሙ ድረስ አሜን።

And all the martyrs and righteous who have fought for the good, world without end. Amen.



ካህናትና ሕዝብ በመቀባበል / Priests and people in succession.

ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ፣
ማርያም እምነ ናስተበቍዓኪ።

ሰላም ላንቺ ይሁን እያልን እንሰግዳለን። እናታችን ማርያም ሆይ እንማልድሻለን።

Peace be unto You, while bowing unto You, our mother Mary, we as for Your prayers.

እምአርዌ ነአዊ ተምኅጸነ ብኪ፣
በእንተ ሐና እምኪ ፧ ወኢያቄም አቡኪ፣
ማኅበረነ ዮም ድንግል ባርኪ።

ከአዳኝ አውሬ ታድኝን ዘንድ ተማጽነንብሻል። ስለ እናትሽ ሐና ስለ አባትሽም ኢያቄም ድንግል ሆይ አንድነታችንን ዛሬ ባርኪልን።

Protect us from evil animals. For the sake of thy mother, Hanna, and Your father, Iyakem, O! Virgin bless this day.

ናዛዚትነ እምኃዘን ወኃይለ ውርዙትነ እምርስዓን፤ በማኅጸንኪ ተፀውረ ብሉየ መዋዕል ሕፃን።

ከሀዘናችን የምታረጋጊን እና ከእርጅና ይልቅ የወጣትነታችን ኃይል የሆንሽ ሆይ ፤ ዘመን የማይቆጠርለት ሕፃን በማኅፀንሽ አደረ።

O You, who is the strength of our youthfulness rather than our aging and who calms us from our grief, The Baby who lives forever has been conceived in Your womb.

ኦ ማርያም ተስፋ ለቅቡጻን፤
በጊዜ ጸሎት ወዕጣን ወበቅዱስ ቍርባን፤
ለናዝዞትነ ንዒ ውስተ ዝ መካን።

ተስፋ ለቆረጡ ተስፋ የሆንሽ ማርያም ሆይ በጸሎት፤ በዕጣንና ቅዱስ ቁርባንም ጊዜ እኛን ለማረጋጋት ወደዚህ ቦት ነዪ።

O Mary, the hope of those who are in despair, come here to calm us when we pray, burn incense and during the Eucharist.

ወላዲተ አምላክ ማርያም እንበለ ሰብሳብ ወሩካቤ፣
በይነ ዘአቅረብኩ ለኪ ንስቲተ ቃለ ይባቤ።

ፈጽሞ ያለጋብቻ አምላክን የወለድሽ ማርያም ሆይ
ስላቀረብኩልሽ ትንሽ የደስታ ቃል

Little happy words I have given You, O Mary, who gave birth to God without marriage

ፈትቲ እሙ በረከተ አፉኪ መዓዛ ከርቤ፣
ለነዳይ ብእሲ ወለዘረከቦ ምንዳቤ፣
ኀብስተከ ፈትት ኢሳይያስ ይቤ።

የከርቤ መፍሰሻ የሆነው የአፍሽን በረከት ለእኔ ቁረሽልኝ። ምክንያቱም ነቢዩ ኢሳይያስ ለደሀና ችግር ለደረሰበት ሰው እንጀራህን ቁረስለት ይላልና።

Because of the prophet Isaiah says, “break your bread for the poor and afflicted.”, break Your blessing to me from Your mouth which is the myrrh’s flowing.

ይወርድ መንፈስ ቅዱስ በላዕለ ኅብስቱ ወወይኑ፣
ሶበ ይብል ካህን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ፈኑ።

ካህኑ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ላክ ባለ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና በወይኑ ላይ ይወርዳል።

As the priest says let the Holy Spirit descend, on this revered Holy of Holies.

ማዕከለ ዛቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ፣
ይዌልጦሙ በቅጽበት አባላተ ክርስቶስ ይኩኑ፣
በኃይለ ጥበቡ መንክር ወዕፁብ ኪኑ።

አስደናቂ በሚሆን የጥበቡ ኃይልና በአስገራሚ ብልሃቱ በቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ መካከል የክርስቶስ አባሎች ይሆኑ ዘንድ በቅጽበት ይለውጣቸዋል።

The Holy Spirit will descend upon the bread and wine and towards the Flesh and Blood. His special Spirit will transform them in an instant with His wisdom.

ሰላም ለክሙ ጻድቃን ወሰማዕት፣
እለ አዕረፍክሙ በሃይማኖት።

በሃይማኖት ያረፋችሁ ጻድቃንና ሰማእታት ሰላም ለእናንተ ይሁን።

Peace be unto you, blessed and martyrs, who have died for the faith.

መዋእያነ ዓለም አንትሙ በብዙኅ ትዕግሥት፣
ሰአሉ ቅድመ ፈጣሪ በኵሉ ሰዓት፤
እንበለ ንስሓ ኪያነ ኢይንሥአ ሞት።

በብዙ ትዕግሥት ዓለምን ድል የነሣችሁ እናንተ ፣ ለንስሓ ሳንበቃ ሞት እንዳይወስደን በየሰዓቱ በፈጣሪ ፊት ቆማችሁ ለምኑልን።

You who have conquered the world b patience, pray for us day and night standing in front of our Creator, so that death will not take us before we have repented.

ሰላም ለክሙ ጻድቃነ ዛቲ ዕለት ኵልክሙ፣
ዕድ ወአንስት በበአስማቲክሙ።

ጻድቃን ወንዶችም ሴቶችም ሁላችሁ በየስማችሁ በዚህ ዕለት ሰላም ለናንተ ይሁን።

Peace be unto you, all those blessed on this day, men and women according to your name.

ቅዱሳነ ሰማይ ወምድር ማኅበረ ሥላሴ አንትሙ፣
ዝክሩነ በጸሎትክሙ በእንተ ማርያም እሙ፣
ተማኅጸነ በክርስቶስ በሥጋሁ ወበደሙ።

በሰማይና በምድር የከበራችሁ የሥላሴ ወገኖች ስለ እናቱ ማርያም ብላችሁ በጸሎታችሁ አስቡን ፤ በክርስቶስ ሥጋና ደም ተማጸንባችሁ።

You that are glorified in heaven and on earth,friends of the Holy Trinity; remember us in your prayers for the sake of Mary and for the sake of Christ’s flesh and blood, we beseech you.

እግዚኦ ሰላመከ ሀባ ለሀገር ወጽድቀከኒ ለቤተክርስቲያን።

አቤቱ ጌታ ሆይ ሰላምህን ለሀገር ፤ እውነትህንም ለቤተ ክርስቲያን ስጥ።

O Lord! Grant Your peace to the country and your truth to the church.

አግርር ፀራ ታሕተ እገሪሃ ፤ ዕቀብ ሕዝባ ወሃይማኖታ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ።

ለሀገራችን ኢትዮጵያ ጠላቶቿን በእግሮቿ ሥር ጣልላት ፤ ሕዝቧንና ሃይማኖቷን ጠብቅላት።

For our country Ethiopia, O Lord bring her enemies under her feet and protect her people and religion.

❖ ካህኑን በመከተል እንበል / repeat after priest.

ካህን (Priest)

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ (፫ ጊዜ)

አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን

Lord have compassion upon us O! Christ, Lord. (3 times)

❖ ካህኑን በመከተል እንበል / repeat after priest.

በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ (፫ ጊዜ)

ክርስቶስ ሆይ ስለ ማርያም ብለህ ማረን።

For the sake of Mary, have compassion upon us, O! Christ, Lord (3 times)

ሰአሊ ለነ ማርያም ወልድኪ ሣህሎ ይክፍለነ።

ማርያም ሆይ! ይቅርታውን ያደርግልን ዘንድ የልጅሽን ምሕረት ለምኝልን።

O Mary, pray for our mercy, so that He may forgive us.

ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ በእንቲአነ ወበእንተ ኵሎሙ ክርስቲያን እለ ይቤሉነ ግበሩ ተዝካሮሙ በሰላም ፤ ወበፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብሑ ወዘምሩ።

ስለ እኛና አስቡን ስላሉን ስለ ክርስቲያኖች ሁሉ ጸልዩ። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር አመስግኑ ፤ ዘምሩም።

Pray You for us and for all Christians who bade us to make mention of them. Praise you and sing in the peace and love of Jesus Christ.

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር ፣ ሀበኒ ከመ እንሣዕ ለሕይወት ዘንተ ሥጋ ወደመ ዘእንበለ ኵነኔ።

የማይነገር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሦስት የምትሆን ይህንን ሥጋና ደም ሕይወት ሊሆነኝ ሳይፈረድብኝ እቀበል ዘንድ ስጠኝ።

Holy! Holy! Holy! Trinity ineffable, grant me to receive this Body and this Blood for life and not for condemnation.

ሀበኒ እግበር ፍሬ ዘያሠምረከ ከመ አስተርኢ በስብሐቲከ ወእሕየው ለከ እንዘ እገብር ዘዚአከ ፈቃደ።

በጌትነትህ እንድገለጽ ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ እሠራ ዘንድ ስጠኝ። የአንተንም ፈቃድ እየሠራሁ እኖርልህ ዘንድ ስጠኝ።

Grant me to bring forth fruit that shall be well pleasing unto You, to the end that I may appear in Your glory and live unto You doing Your will.

በተአምኖ እጼውዐከ አብ ወእጼውዕ መንግሥተከ ይትቀደስ እግዚኦ ስምከ በላዕሌነ ፤ እስመ ኃያል አንተ እሡት ወስቡሕ ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም።

በማመን አባት ብዬ እጠራሃለሁ። አቤቱ ስምህ በእኛ ላይ ይመስገን። ምስጉን ክቡር የምትሆን ኃያል አንተ ነህና ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘለዓለሙ።

In faith, I call upon You, Father, and call upon Your Kingdom; hallowed, Lord, be Your name upon us, for mighty are You, praised and glorious, and to You be glory, world without end.

እስመ ኃያል አንተ እሙት ወስቡሕ ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም።

ኃያል አንተ ነህና ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘለዓለሙ።

praised and glorious, and to You be Glory, for ever and ever.

ዲያቆን (Deacon)

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውሰ።

ለነፍሳችን አነዋወር መድኃኒት ይሆነን ዘንድ ሥጋውንና ደሙን ተቀበልን ፤ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።

We thank God for that we have partaken of His Holy things;

ዘተመጦነ ንስእል ወንትመሐፀን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላክነ።

የተቀበልን እኛ አምላካችንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን እንለምናለን ፤ አደራም እንላለን።

we pray and trust that which we have received may be healing for the life of the soul while we glorify the Lord our God.

ካህን (Priest)

አሌዕለከ ንጉሥየ ወአምላኪየ ወእባርክ ለስምከ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ንጉሤና ፈጣሪዬ ሆይ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ። ቅዱስ ስምህንም ለዘለዓለም አመሰግናለሁ።

I will extol You, my King and my God, and I will bless Your Holy name for ever and ever.

## ሕዝብ (People)

አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

Our Father You are in heaven, lead us not, Lord, into temptation.

ዲያቆን (Deacon)

ተመጠነ እምሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ።

ከክርስቶስ ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ተቀበልን።

We have received of the Holy Body and the precious Blood of Christ.

ካህን (Priest)

ኵሎ አሚረ እባርከከ ወእሴብሕ ለስምከ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ዘወትር አከብርሃለሁ። ቅዱስ ስምህንም ለዘለዓለሙ አመሰግናለሁ።

Every day will I bless You, and I will praise Your name for ever and ever..

## ሕዝብ (People)

አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

Our Father You are in heaven, lead us not, Lord, into temptation.

ዲያቆን (Deacon)

ወናእኵቶ ይደልወነ ከመ ንሳተፍ ምስጢረ ክብርተ ወቅድስተ።

ክብርት ቅድስት የምትሆን ምስጢርን እንሳተፍ ዘንድ ስላበቃን ልናመሰግነው ይገባል።

And let us give thanks unto him that make us meet to communicate in the precious and Holy mystery.

ካህን (Priest)

ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ፤ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

አንደበቴ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል። የሥጋ ፍጥረትም ሁሉ ቅዱስ የሚሆን ስሙን ያመሰግናል ለዘለዓለሙ።

My mouth shall speak the praise of the Lord, and let all flesh bless His Holy name for ever and ever.

ሕዝብ (People)

አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

Our Father You are in heaven, lead us not, Lord, into temptation.

## ኀዳፌ ነፍስ - *Pilot of the Soul*

**ካህን (Priest)**

ኦ ገባሬ ብርሃናት ዘደፍዖ ለጽልመት ፤ ወሠዐሮ ለጣዖት ዘበሞቱ ደምሰሶ ለሞት።

የብርሃናት ፈጣሪ ሆይ ጨለማን የደፋው ፤ ጣዖትንም የሻረው በሞቱ ሞትን ያጠፋው።

O Creator of lights, Who did cast away the darkness and degrade the idols and destroyed death through Your death.

ናስተበቍዕ ኂሩተ ሠናያቲከ በእንተ ሕዝብከ ወርስትከ እለ መጽኡ ውስተ ቤተ መቅደስ ከመ ይንሥኡ ሥጋከ ወደመከ እምክብርት ማዕድከ እንተ ይእቲ ተስፋሆሙ ለኃጥኣን።

ተስፋቸው ከምትሆን ከክብርት ማዕድህ ሥጋህንና ደምህን ይቀበሉ ዘንድ ወደ ቤተ መቅደስህ ስለ መጡ ስለ ሕዝብህና ስለ ርስትህ የበጎነትህን ቸርነት እንማልዳለን።

We supplicate the kindness of Your goodness on behalf of Your people and Your inheritance who have come unto Your sanctuary to receive Your body and Your blood from Your honorable table which is the hope of sinners.

መዓልተ ዕቀቦሙ እምጌግዮ ወስሒት በመልክእ ወበመለያልይ በንጻሬ ወበራእይ ሌሊተ ተኖልዎሙ ትግህታተ ከንቱ ኢይምጽኦሙ እንተ ይኢቲ አማሳኒሃ ለነፍስ።

በቀን በመልክና በሕዋሳት በማየትም በራእይም ከመበደልና ከመሳት ጠብቃቸው ፤ በሌሊት ለከንቱ ነገር መትጋት እንዳይመጣባቸው ጠብቃቸው ይህችውም ነፍስን የምታጠፋ ናት።

Keep them, by day, from trespassing and from error of sight and of the members of the body, and keep them by night that the vain thoughts thereof which destroy the soul may not come unto them.

ወለእመኒ ኖሙ ረሲ አክናፈ መላእክት ይክድኖሙ ክበደ ንዋም ኢያሥጥሞሙ ዘውእቱ አምሳሊሁ ለሞት

ቢተኙም የመላእክት ክንፍ እንዲያለብሳቸው አድርግ የእንቅልፍ ጽናት እንዳያሠጥማቸው ይኸውም የሞት ምሳሌ ነው

When they sleep let the wings of the angels cover them in order that oversleeping, which is the likeness of death, may not overwhelm them.

አንቅሖሙ እግዚኦ በፍቅርከ ከመ ይሰብሑ ለስምከ ክቡር ወአዚዝ አንተ አኃዜ ዓለም እግዚአብሔር አምላክነ።

አቤቱ በፍቅርህ አንቃቸው ክቡር ጽኑ የሚሆን ስምህን ያመሰግኑ ዘንድ ዓለምን የያዝህ አንተ እግዚአብሔር አምላካችን።

O Lord, awaken them through Your love to glorify Your honorable and strong name, almighty Lord our God.

## ዲያቆን (Deacon)

ጸልዩ።

ጸልዩ።

Pray.

ካህን/priest/

አኮ ለነ እግዚኦ አኮ ለነ ለክርስቲያን ሕዝብከ ዝንቱ ዓለም ተስፋ ዘይበሊ ወዘይማስን ፤

አቤቱ የሚያረጅ የሚጠፋ ይህ የተስፋ ዓለም ለእኛ ለክርስቲያን ወገኖችህ አይደለም ፤

O Lord, this corruptible and transient world of hoping is not for us, Your Christian people;

አላ ዘይመጽእ ንሴፎ ወንጸንሕ ፤ እስመ አንተ ትቤ ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ።

የሚመጣውን ተስፋ እናደርጋለን ደጅም እንጠናለን እንጂ ፤ አንተ ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም ብልሃልና።

but we hope and wait for that which is to come. Because You did say, Heaven and earth shall pass away, but My words shall not pass away.

ወካዕበ ትቤ ይከውን ንፍሐተ ቀርን ፫ተ ጊዜ ዘውእቱ መንቅሔ ሙታን ፤ በቀዳሚ ንፍሐተ ቀርን ይትጋባእ ጸበለ ሥጋ ዘተዘርወ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም።

ዳግመኛም ሦስት ጊዜ የመለከት መነፋት ይሆናል ብልሃልና ፤ ይኸውም ሙታን የሚያነቃ ነው ፤ በመጀመሪያው አዋጅ በዓለም ዳርቻ ሁሉ የተበተነ የሥጋ ትቢያ ይሰበሰባል።

You also did say, the horn will be blown three times to awaken the dead. At the first blowing of the horn there will be gathered the dust of bodies scattered through all the ends of the world,

ዘሀሎ መልዕልተ ወዘሀሎ መትሕተ ዘሀሎ በባሕር ወዘሀሎ በየብስ ወዘሀሎ ውስተ ከርሦሙ ለአራዊት ዘበልየ ወዘማሰነ በዘዚአሁ ሞት ወዘወድቀ ቅርፍተ ሥጋ ዲበ ምድር ይትጋባእ ኀበ ዘትካት

በላይ ያለውና በታች ያለው በባህር ያለውና በየብስ ያለው በአራዊትም ሆድ ያለው በልዩ ልዩ ሞት ፈጽሞ ያረጀና የጠፋ በምድር ላይ የወደቀ የሥጋ ቅርፊትም ሁሉ ወደ ቀደመ

above and beneath, in the sea and on the land, that which is in the stomachs of the beasts and that which waxed old and perished after death, and the piece of the body, fallen on earth, will be gathered in their

ምዕላዲሁ። ወበዳግም ንፍሐተ ቀርን ይሰፈያ አዕፅምት ምስለ ሥጋ ወደም ወይከውን በድነ ፍጹመ ዘእንበለ አንሰሐስሖ ወኢተሐውሶ እስከ ጊዜሁ።

መገናኛው ይሰበሰባል። በሁለተኛውም አዋጅ አጥንቶች ከሥጋና ከደም ጋራ ይያያዛሉ ያለ መንቀሳቀስ ያለ መናወጥም እስከ ጊዜው ድረስ ፍጹም በድን ይሆናል።

previous position. At the second blowing of the horn the bones will be joined with the flesh and blood and they will be perfect dead bodies without movement until the appointed time.

ወበሣልስ ንፍሐተ ቀርን ይትነሥኡ ሙታን ከመ ቅጽበተ ዓይን ጻድቃን ወኃጥኣን እንዘ ይጸውሩ ምግባራቲሆሙ እምዲበ ምድር ዘተለዎሙ ዘገብሩ በኵሉ መዋዕለ ሕይወቶሙ እመሂ ሠናየ

በሦስተኛውም አዋጅ ሙታን እንደ ዓይን ጥቅሻ ይነሣሉ ጻድቃንና ኃጥኣን ክፉም ቢሆን በጎም ቢሆን በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ የሠሩትን ከምድር የተከተላቸውን ሥራቸውን ተሸክመው ይነሣሉ

At the third blowing of the horn the dead will rise in the twinkling of an eye, the righteous and the sinners, carrying their works which followed them from the earth and which they did in all the days of their life,

ወእመሂ እኩየ ወታቀውም ጻድቃነ በየማንከ ወኃጥኣነ በጸጋምከ። ወታወሥኦሙ ለኅሩያንከ በቃለ ብፁዓን እንዘ ትብል ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ ትረሱ መንግሥተ ሰማያት ዘድልው ለክሙ

ጻድቃንን በቀኝህ ኃጥኣንን በግራህ ታቆማለህ። ለመረጥሃቸው እንዲህ ብለህ በምስጋና ቃል ትናገራቸዋለህ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያትን

good or bad. You will make the righteous to stand at Your right You will answer Your elect with the word of blessing saying: Come to me, you blessed of My Father, inherit the kingdom of heaven prepared for you from the

እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። እስመ ርብኀኩ ወአብላዕክሙኒ። ጸማዕኩ ወአስተይክሙኒ።

ትወርሱ ዘንድ ወደ እኔ ኑ። ብራብ አብልታችሁኛልና። ብጠማ አጠጥታችሁኛልና።

foundation of the world: hand, and the sinners at Your left hand. For I was an hungered, and you gave Me food: I was thirsty, and you gave Me drink:

ነግደ ኮንኩ ወአኀደርክሙኒ። ዕረቁ ወአልበስክሙኒ። ደወይኩ ወሐወፅክሙኒ። ተሞቃሕኩ ወመጻእክሙ ወነበብክሙኒ።

እንግዳ ብሆን አሳድራችሁኛልና። ብታረዝ አልብሳችሁኛልና። ብታመም ጎብኝታችሁኛልና። ብታሠር መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና።

I was stranger, and you took Me in: I was naked, and you clothed Me: I was sick, and you visited Me: I was in prison, and you came unto Me and spoke on My behalf.

ወእምዝ ትትመየጥ መንገለ ጸጋምከ ወትገንሖሙ ለኃጥአን በቃለ ስክየት እንዘ ትብል ሑሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም ዘድልው ለሰይጣን ወለመላእክቲሁ።

ከዚህም በኋላ ወደ ግራህ ተመልሰህ ኃጥኣንን በወቀሳ ቃል እንዲህ ብለህ ትቆጣቸዋለህ እናንተ እርጉማን ከእኔ ወግዱ ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ።

Afterwards You will turn to Your left hand and rebuke the sinners with the word of accusation saying: Depart from Me, you cursed, into everlasting fire prepared for the Devil and his angels:

እስመ ርኅብኩ ወኢያብላዕክሙኒ። ጸማዕኩ ወኢያስተይክሙኒ። ነግደ ኮንኩ ወኢኀደርክሙኒ። ዐረቁ ወኢያልበስክሙኒ። ደወይኩ ወኢሐወፅክሙኒ። ተሞቃሕኩ ወኢየነበብክሙኒ።

ብራብ አላበላችሁኝምና። ብጠማ አላጠጣችሁኝምና። እንግዳ ብሆን አላሳደራችሁኝምና። ብራቆት አላለበሳችሁኝምና። ብታመም አልጎበኛችሁኝምና። ብታሠር አልጠየቃችሁኝምና።

For I was an hungered, and you gave Me no food: I was thirsty, and you gave Me no drink: I was a stranger, and you took Me not in: I was naked, and you did not clothe Me: I was sick, and you did not visit Me. I was in prison, and you did not speak on My behalf.

አሜሃ ይትፌጸም ኵሉ አፍ ወልሳን ዘይነብብ ዓመፃ ወጽልሑተ። አሜሃ ይከውን ኀዘን ዘኢይበቍዕ ኀዘን። አሜሃ ይከውን ክላሕ ዘኢይበቍዕ ክላሕ።

ያን ጊዜ አመፅንና ሽንገላን ይናገር የነበረ አፍና አንደበት ሁሉ ይዘጋል። ያን ጊዜ ኀዘን ይደረጋል የማይጠቅም ኃዘን ነው። ያን ጊዜ ጩኸት ይሆናል የማይጠቅም ጩኸት ነው።

At that time every mouth and tongue which spoke mischief and deceit will be stopped. At that time there will be sorrow but vain sorrow. At that time there will be a cry but a vain cry:

አሜሃ ይከውን አውያት ዘኢይበቊዕ አውያት። አሜሃ ይከውን ገዓር ዘኢይበቊዕ ገዓር። አሜሃ ይውኅዝ አንብዕ ከመ ማየ ክረምት ዘአልቦ ማኅለቅት ወኢተፍጻሜት።

ያን ጊዜ ፍጅት ይሆናል የማይጠቅም ፍጅት ነው። ያን ጊዜ ለቅሶ ሆናል የማይጠቅም ለቅሶ ነው። ያን ጊዜ ፍጻሜ ማኅለቅት እንደሌለው እንደክረምት ውኃ ዕንባ ይፈሳል።

at that time there will be wailing but vain wailing. At that time there will be lamentation but vain lamentation; at that time tears will be shed like the water of winter which has not end and does not stop.

ወይትፌኖ ኀቤሆሙ መብረቅ መዛጢ ወቃለ ነጐድጓድ መደንግፅ ወፀዓዕ ኃያል ዘይሰይፍ ወይከፍል ወይሌሊ ዘውእቱ መክፈልቶሙ ለኃጥኣን።

ነጣቂ መብረቅ የሚስደነግጥ የነጐድጓድም ቃልም የሚቈርጥና የሚከፍል የሚለይ ብርቱ ብልጭልጭታም ወደነርሱ ይላካል ይኸውም የኃጥኣን ዕድላቸው ነው።

There will be sent to them swift lightening and a fearful sound of thunder and a powerful sound of thunder and a powerful flash which cuts, separates and divides this is portion of sinners.

አሜሃ ምድር ታገብእ ማኅፀንታ ወኢትሰምዕ እም አውያተ ወለታ። አሜሃ ይትከሠት ምግባሪ ለነፍስ ዘገብረት በኵሉ መዋዕለ ሕይወታ።

ያን ጊዜ ምድር አደራዋን ትመልሳለች ፤ እናትም የሴት ልጇን ጩኸት አትሰማም። ያን ጊዜ በሕይወትዋ ዘመን የሠራችው የነፍስ ሥራዋ ይገለጻል።

At that time the earth will restore that which was entrusted to it and the mother will not hear the cry of her daughter. At that time there will be revealed the work of the soul which she did during all the days of her life.

አሜሃ ከመ ትምሐረነ ወትሣሃለነ ተማኅፀነ በዘበላዕነ ሥጋከ ወበዘሰተይነ ደምከ። እስመ አንተ ትቤ ዘበልዐ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለዓለም።

በዚያን ጊዜ ትምረን ይቅርም ትለን ዘንድ በበላነው ሥጋህ በጠጣነው ደምህ ተማፅነናል። አንተ ሥጋዬን ለበላ ደሜንም ለጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው ብለሃልና።

We have trusted on Your body which we have eaten and Your blood which we have drunk that You at that time may have compassion and mercy upon us, because You did say, whosoever eats My flesh, and drinks My blood, has eternal life.

ወካዕበ ተማኅፀነ በማርያም እምከ። አንተ ይእቲ እግዝእትነ ወትምክሕተ ዘመድነ በወሊዶተ ዚአከ። እስመ አንተ ትቤላ ዘገብረ ተዝካረኪ ወዘጸውዐ ስመኪ ሕይወት ዘለዓለም የሐዩ።

ዳግመኛም በእናትህ በማርያም ተማፅነናል። ይህችውም አንተን በመውለድ እመቤታችንና የባሕሪያችን መመኪያ ናት። አንተ መታሰቢያሽን ያደረገ ስምሽንም የጠራ የዘላለም ደኅንነትን ይድናል ብለሃታልና።

We have also trusted on Your mother our Lady Mary, the shield of our race in giving birth to You, because You did say to Her, He who remembers You and calls upon Your name will have eternal life.

ወካዕበ ተማኅፀነ በርእሶሙ ለመላእክት ፤ ወበስደቶሙ ለነቢያት ወበስብከቶሙ ለሐዋርያት ፤ በየማኖሙ ለካህናት ፤ ወበደሞሙ ለሰማዕታት ፤ ወበትዕግሥቶሙ ለወራዙት ወደናግል ወመነኰሳት

ዳግመኛም በመላእክት አለቆችና በነቢያት ስደት፤በሐዋርያትም ስብከትና በካህናት ሥልጣን ፤ በሰማዕታትም በደማቸው በወራዙትና በደናግል በመነኰሳትም ትዕግሥት ፤

We have also trusted on the archangels, the prophets, the preaching of the apostles, the right hand of the priests, the blood of the martyrs, the patience of the young men, virgins and monks,

ወበእምነቶሙ ለመሃይምናን ወመሃይምናት። አሜሃ መሐረነ ወመሐከነ ወተሣሃለነ።

በወንዶችም በሴቶችም ምዕመናን እምነት ተማፅነናል። ያን ጊዜ ማረን አራራልንም ይቅርም በለን።

and on the faith of the faithful men and women. At that time have compassion, pity and mercy upon us.

ስብሐት ለአብ ፈናዊ ፤ አኰቴት ለወልድ ተፈናዊ ፤ ክብር ወስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ማኀየዊ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም።

ልጁን ለላከ ለአብ ምስጋና ይገባል ፤ ለተላከ ለወልድም ምስጋና ይገባል ፤ ማሕየዊ ለሚሆን ለመንፈስ ቅዱስም ክብር ምስጋና ይገባል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ።

Glory be to the Father who sent, thanksgiving be to the Son who was sent, and honor and glory be to the life giving Holy Spirit, both now and ever and world without end.

ሕዝብ / People

አሜን።

Amen.

ቡራኬ

Benediction

ሕዝብ/People/

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም ኀድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እነደሆነ እንዲሁም በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንንም ይቅር በለን፤

Our Father who are in heaven Hallowed be Your name. Your kingdom come Your will be done on earth as it is in heaven Give us this day our daily bread, and forgive us our trespasses

ንኅድግ ለዘ አበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኲሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።

እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል ፤ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይል ክብር ምስጋና ለዘለዓለሙ አሜን።

as we forgive those who trespass against us and lead us not into temptation but deliver us from evil. For Yours is the kingdom, and the power, and the glory, for ever and ever, Amen.

በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ ድንግል በሕሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን በሃሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ ፤ የአሸናፊ እግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል

By the salutation of the Saint Angel Gabriel, oh my Lady Mary I salute You, You are Virgin in thought, And Virgin in body, the mother of God Tsabaot (The Lord of Host) salutation to You.

ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ሰአሊ ወጸልዪ

ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ልዑል እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን

Blessed are You among women and blessed is the fruit of Your womb Jesus. Rejoice, You who are hailed, O graceful God is with You. Beseech and pray for our

ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን ኃጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

mercy to Your beloved son Jesus Christ that He may forgive us our sins. Amen.

ኦ ንጉሠ ሰላም ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመከ ሀበነ ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ ወሥረይ ለነ ኃውኢነ ወረስየነ ድልዋነ ከመ ንሑር ወንእቱ ውስተ አብያቲነ በሰላም።

የፍቅር ባለቤት የሰላም ንጉሥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰላምህን ስጠን ሰላምህን አጽናልን ኃጢአታችንንም ይቅር በለን በሰላም ወደ ቤታችን ሂደን እንገባ ዘንድ የበቃን አድርገን፡፡

O peaceful king of peace, Jesus Christ, grant us Your peace and confirm unto us Your peace, and forgive us our sins, and make us worthy to go out and enter into our homes in peace.



ዲያቆን (Deacon)

አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርክሙ።

አገልጋይ በሚሆን በካህኑ እጅ ይባርካችሁ ዘንድ ፤ በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ።

Bow your heads in front of the Lord our God, that He may bless you at the hand of His servant the priest.

ሕዝብ (People)

አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ወይሣለሃነ።

አሜን እግዚአብሔር ይባርከን ይቅርም ይበለን።

Amen. May God bless us and forgive us.

ካህን (Priest)

ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ ረዓዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም።

አቤቱ ሕዝብህን አድን ፤ ርስትህንም ባርክ። አቤቱ ሕዝብህን አድን ፤ ርስትህንም ባርክ። እስከ ዘላለሙ ጠብቃቸው ፤ ከፍ ከፍም አድርጋቸው።

O Lord, save You people and bless Your inheritance. Feed them, lift them up for ever,

ወዕቀባ ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት እንተ አጥረይካ ወቤዘውካ በደሙ ክቡር ለዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

በአንድ ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የዋጀሃት ፣ ቤዛም የሆንኻት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ጠብቃት።

and keep Your church which You did purchase and ransom with the precious blood of Your only-begotten Son, our Lord and our God and our Savior Jesus Christ;

ወዘጸዋዕካ ትኩን ማኅደረ ለነገሥት ወለመኳንንት ለዘመድ ንጹሕ ወለሕዝብ ቅዱስ እለ መጻእክሙ ወእለ ተጋባእክሙ ወእለ ጸለይክሙ ውስተ ዛቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን።

ለነገሥታትና ለመኳንንት ፣ ለንጹሕ ወገንና ቅዱስ ለሆነ ሕዝብ ማደሪያ ትሆን ዘንድ የጠራሃት። በዚች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መጥታችሁ ተሰብስባችሁ የጸለያችሁ ፤

And which You have called to be a dwelling-place for kings and rulers, for pure kindred and Holy people, You who have come and gathered and prayed in His Holy church,

እለ በላዕክሙ ሥጋሁ ቅዱሰ ወእለ ሰተይክሙ ደሞ ክቡረ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሥረይ ለክሙ ኃጢአተክሙ ዘገበርክሙ እመሂ በአእምሮ አው በኢያእምሮ።

የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን የበላችሁ ፤ ክቡር ደሙንም የጠጣችሁ ፤ በማወቅ ወይም ባለማወቅ የሠራችሁትን ኃጢአታችሁን ይቅር ይበላችሁ፡፡

and You who have eaten the Holy body and drunk the precious blood of our Lord Jesus Christ. May He forgive Your sins which You have committed wittingly or unwittingly .

በዘኀለፈ ይምሐርክሙ ወበዘይመጽእ ይዕቀብክሙ በእንተ ሥጋሁ ሥጋ መለኮት ወበእንተ ደሙ ደመ ሕግ ወሥርዓት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ጸባዖት

ሥጋ መለኮት ስለሚባል ሥጋው የሕግና የሥርዓት ደም ስለሚሆን ደሙ የአሸናፊ የእግዚአብሔር ልጅ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ሕሊናም ኅትምት የምትሆን የማርያም ልጅ

May He forgive you your past sins and keep you from future ones, for the sake of His body, the divine body, and for the sake of His blood, the blood of the covenant of Jesus Christ the Son of the Lord of hosts,

ወወልደ ማርያም ንጽሕት በድንግልና ሕሊና ወበድንግልና ሥጋ ኅትምት ለዓለመ ዓለም አሜን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፈው ይቅር ይበላችሁ ፤ በሚመጣውም ይጠብቃችሁ። ለዘላለሙ አሜን።

and the Son of pure Mary, who has sealed the Vrginity of Her conscience and body, world without end. Amen.

ቡራኬ

Benediction

ካህን (Priest)

እግዚአብሔር የሀሉ ምስለ ኵልክሙ።

እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

The Lord be with you all.

ሕዝብ (People)

ምስለ መንፈስከ።

ከመንፈስህ ጋራ።

And with Your spirit.

ሕዝብ (People)

አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ለአግብርቲሁ በሰላም ሥርየተ ይኩነነ። ዘተመጦነ ሥጋከ ወደመከ አብሐነ በመንፈስ ንኪድ ኵሉ ኃይሎ ለጸላዒ።

አሜን እግዚአብሔር እኛን አገልጋዩቹን በሰላም ይባርክ ፤ የተቀበልነውን ሥጋህና ደምህ ለሥርየት ይሁነን ፤ የጠላትን ኃይል ሁሉ በመንፈስ እንረግጥ ዘንድ አሰልጥነን።

Amen. May God bless us, His servants, in peace. Remission be unto us who have received Your body and Your blood. Enable us by the Spirit to tread upon all the power of the enemy.

በረከተ እዴከ ቅድስት እንተ ምልዕተ ምሕረት ኪያሃ ንሴፎ ኵልነ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አግኅሠነ ወውስተ ኵሉ ምግባረ ሠናይ ደምረነ። ቡሩክ ዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ።

ምሕረትን የተሞላች ክብርት የምትሆን የእጅህን በረከት ሁላችን ተስፋ እናደርጋለን። ከክፉ ሁሉ አርቀን። በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን። ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙንም የሰጠን ብሩክ ነው።

We all hope for the blessing of Your Holy hand which is full of mercy. From all evil works keep us apart, and in all good works unite us. Blessed be He that has given us His Holy body and His precious blood.

ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ኪያከ እግዚኦ ነአኵት ነሢአነ ጸጋ ዘመንፈስ ቅዱስ።

ጸጋን ተቀበልን ፤ ደኅንነትንም በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል አገኘን። አቤቱ ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ ጸጋን ተቀበልን ፤ አንተን እናመሰግንሃለን።

We have received grace and we have found life by the power of the cross of Jesus Christ. Unto You, Lord, do we give thanks, for that we have received grace from the Holy Spirit.

ዲያቆን (Deacon)

እትዉ በሰላም።

በሰላም ግቡ።

You, go in peace.

ሕዝብ(People)

አሜን

Amen

ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ።
አሜን።

ምሥጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅድስ ለአንድ አምላክ።
አሜን።

Glory to the Father, to the Son, and to the Holy Spirit, One God.
Amen.

ምንጭና ዋቢ

- መጽሐፈ ቅዳሴ - ዘደብረ ዓባይ
- መጽሐፈ ቅዳሴ - በፊደል አሳታሚ
- መጽሐፈ ሰዓታት ከነምልክቱ
- መጽሐፈ ግጻዌ
- መዝሙረ ዳዊት
- ethiopianorthodox.org website (ዋና ምንጭ)
- google translate
- በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ቅዳሴ (Presentation)

ጌታሁን ተሾመ
ኃይለ ገብርኤል
፳፻፲፮
Columbus, OHIO USA 2024
bereded62@gmail.com
www.mytewahdo.org
የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፋይሎች (Facebook)

# ኑ እንቅረብ መከራ ሳይመጣ

ኑ እንቅረብ መከራ ሳይመጣ፤
ሥጋውን እንብላ ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ።

የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው፤
ተሰውቶልናል እንመገበው።

እድፉን ኃጢያታችን በንስሐ አጥበን፤
እንቀበል አምነን በልጅነታችን።

መቅረብ ወደ ጌታ በእውነት የሚገባው፤
በስተእርጅና  አይደለም በወጣትነት ነው።

ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት፤
ከዋክብት ከሰማይ የተነጠፉለት፤
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት።

ቅድስት እናታችን ቤተ ክርስቲያን፤
ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን።

የአማኑኤል ሥጋ  ይኸው ተዘጋጀ፤
ከግብዣው ተጠራን አዋጁ ታወጀ።

ኑ እንቅረብ መከራ ሳይመጣ፤
ሥጋውን እንብላ ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ።

## ይህ ቁርባን ክቡር ነው

ይህ ቁርባን ክቡር ነው ፍጹም ሰማያዊ፤
እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ፤
እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ።

ዋ! ምን አፍ ነው የሚቀበለው፤
ዋ! ምን ጥርስ ነው የሚያላምጠው፤
ዋ! ምን ሆድ ነው የሚሸከመው፤
ነበልባል ያለበት የሚያቃጥል ነው፤
በንጽሕና ሆኖ ላልተቀበለው፤
የሚያፍገመግም የሚጎዳ ነው።

አምላካችን ሆይ አንተ ይቅር ባይ፤
እንደ ቸርነትህ በደልን አትይ፤
እንደ ቸርነትህ በደልን አትይ።

አሜን አሜን ብለን ተቀብለናል፤
በድፍረትም ሳይሆን በፍርሃት ቀርበናል፤
በድፍረትም ሳይሆን በፍርሃት ቀርበናል።

ማክበር ይገባናል በንጽሕና ሆነን፤
ደፍረን አናቃለው እንዳያቃጥለን፤
ደፍረን አናቃለው እንዳያቃጥለን።

እንደምታዩትም ይህ ቁርባን ፈራጅ ነው፤
እንደሌላው ሳይሆን የተቀደሰ ነው፤
እንደሌላው ሳይሆን የተቀደሰ ነው።

ይህ ቁርባን ክቡር ነው ፍጹም ሰማያዊ፤
እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ፤
እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ።

ሱራፌል ኪሩቤል ጸምርተ መንበር፤
ሊይዙት ያልቻሉት ፈርተውት በክብር፤
ሊይዙት ያልቻሉት ፈርተውት በክብር።

እኛ ተመገብነው አገኘን ድኅነት፤
በነፍስ በሥጋችን ሆነልን ሕይወት።
በነፍስ በሥጋችን ሆነልን ሕይወት።